መስቀል

የባ/ዳር ካቴድራል መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ሰ/ት/ቤት ገጽ ፔጁን ላይክ በማድረግ መንፈሳዊ እውቀትዎን ያጎልብቱ

1/ (በመስቀል ዙሪያ የሚነሡ ጥያቄዎች)፤ መስቀሉን ስታከብሩ የተሰቀለውን ለምን ትረሳላችሁ?

+++++++ከህሊና በለጠ ተግፊ

ጥያቄ፡- ብዙ ኦርቶዶክሳዊያን የመስቀል ቅርጽ በጣታቸው በማማተብ ወይም የተቀረጸ መስቀልን በአንገታቸው በማድረግ ሲያከብሩት እናያለን። ይህ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ አይደለም። ይህን ማድረግ ታዲያ ለምን ያስፈልጋል? ትእምርተ መስቀል ክርስቶስን የሚያስረሳ በእርሱም ፋንታ እያከበራችሁት ይመስለኛል፤ ይህ ለምን ይሆናል?

በክብረ መስቀል፤ በበዓሉ እና በማዕተብ ዙሪያ በርካታ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። እንደዚኽኛው ጥያቄም የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓተ አምልኮ በመንቀፍ ክርስቶስን የዘነጋች አድርገው የሚያቀርቡም ብዙዎች ናቸው። ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን በበዓለ መስቀል፤ በክብረ መስቀልና በማዕተብ ዙሪያ ለሚነሱት ጥያቄዎች ከላይ የተጠቀሰውን ጥያቄ በመለሰበት ጽሑፉ በሐመር መጽሔት 18ኛ ዓመት ቁጥር 6፤ የመስከረም 2003 ዓ.ም. የመስቀል በዓል ልዩ ጎትም ላይ እንደሚከተለው ምላሽ

ሰጥቷል።

...ትእምርተ መስቀል ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ የሰው ልጆችን ማዳኑን የምናስብበት ምልክት ነው። ክርስቶስን ማሰብ ደግሞ የሚገባ ነው። ራሱ ጌታችን ይህንን ባደረጋችሁ ጊዜ ሞቴን መከራዬን ታስባላችሁ ብሎናል። እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙሩን ጢሞቴዎስን "በወንጌል እንደምሰብከው ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን ከዳዊት ዘር የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስበው" ብሎታል። /2 ጢሞ. 2፡8/። ክርስቶስን ደግሞ በነገር ሁሉ ማሰብ የሚገባ ነው። ለእርሱ ምስጋና ይግባውና እርሱ ከተናገረው ካደረገውም ስለሰው ልጆችም ከሆነውም ሁሉ እርሱ ደስ ለማይሰኝባቸው ነገሮች ምልክት የሆኑ ነገሮች የሉም። ከተናገረው፤ ካደረገውም በላይ ስለኛ የሆነው፤ ይልቁንም ስለኛ የተቀበለው መከራ፤ ውርደትና ሞት ግን ዋጋው ከምንም በላይ ነው። ይህ ለእርሱ ጥበቡም ኃይሉም ፍቅሩም ትሕትናውም የተገለጠበት ነው። "ስለወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ያለ እንደሆነ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር የለም።" /ዮሐ. 15፡13/ ብሎ ጌታችን እንደተናገረ እኛ ወዳጆቹ ሳይሆን ጠላቶቹ ሆነን ሳለ ስለኛ ቤዛ አድርጎ ራሱን ያቀረበበት የመስቀል ሞት ከምንም በላይ የክርስትና ሕይወት መሠረት ነው።

የሃይማኖታችን ማእከል ደግሞ እርሱ ከሆነ ምልክታችንም

ያንን የሚያስታውሰን የመስቀል ምልክት ሊሆን
እንደሚገባው ቤተ ክርስቲያን ታምናለች። ክርስቶስንና
የማዳን ሥራውን የምናስታውስበት ምልክት ደግሞ
የቤተክርስቲያንም ምልክት ነው። እሱ ጌታዋ፤ ራሷ፤ እረኛዋ፤
ተስፋዋ፤ ጠባቂዋ ኃይሏ ነውና።
መስቀል ክርስቶስንና ክርስቶስ ለሰዎች ያደረገውን የፍቅር
ሥራ ከማስታወሱም ሌላ የምንማርበት፤ የምናስተምርበት
ነው። በትእምርተ መስቀል የተሰፋውን ቃል /በነቢያት
የተነገረውን ትንቢት፤ የተመሰለውን ምሳሌ/ መፈጸሙን፤
የክርስቶስን የማዳን ጥበብና ምስጢር የምናስተምርበት
ነው።
ትእምርተ መስቀል ጥሪም ነው። ክርስቲያኖች ክርስቶስን
በማመን በክርስቶስ ስም ስለ እውነት መከራን መቀበልን
ሳይሰቀቁ በጽናት እንዲቆሙ የሚቀርብ የሃይማኖት ጥሪ
ነው።
ትእምርተ መስቀል ምስክርነትም ነው። ጌታችን ለሐዋርያቱ
“ምስክሮቼ ትሆናላችሁ” እንዳለ በትእምርተ መስቀልም
የሰማዕትነት /የምስክርነት/ ተግባርን እንፈጽማለን።
ምስክርነት ደግሞ ከፍተኛው ሐዋርያዊ አገልግሎት ነው።
በመሆኑም ክርስቲያኖች በካዱ በአይሁድ ፊት፤ በማያምኑም
አረማውያን ፊት በክርስቶስ መስቀል፡ ሞትና ትንሣኤ
እንደማያፍሩበት ይመሰክራሉ። ይህ ደግሞ ያለማፈር

እንድንፈጽመው ጌታችን “በሰው ፊት የሚመሰክርልኝን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መላእክቱ ፊት ይመሰክርለታል።” ብሎ የተናገረን ተግባር እንጂ የግብዝነት አካሔድ አይደለም /ሉቃ. 10፡28/። በተለይ በዘመነ ሐዋርያት አይሁድ “እኛ ገርፈን በሰቀልነው ያምናሉ” እያሉ ይዘብቱ ስለነበር፤ “እርሱ ሞቷል እንጂ አልተነሣም” የሚሉ፤ መስቀሉንም “እርሱ የተዋረደበት መቅጫ ነው” የሚሉ፤ እርሱን ዙፋን አድርጎ የሰው ልጆችን ሁሉ ያዳነበት መሆኑን የማያምኑ፤ “በሞት ሞት አይሸነፍም” የሚሉ ዘባኞችና መስተሳልቃን ስለነበሩ የክርስቶስን መከራና ሞት ማሰብ፤ በዚያም መዳናችንን ማመን ሞኝነት የሚመስላቸው ነበሩ። በዚያ የጸኑ ክርስቲያኖችንም ያሳድዱ ነበር። ስለዚህ በመስቀሉ ስላገኘነው ሕይወት በግልጽ መመስከር አስፈላጊ ነው። ለዚያም ነው ቅዱስ ጳውሎስ “የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው” ያለው /1 ቆሮ 1፡18/። በዚህ ቃሉ መሠረት ስለ ነገረ መስቀሉ መመስከር የሰማዕትነት ፍጻሜ ነበር። ስለዚህ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ያላቸውን ፍጹም ፍቅር አይሁድና ተረፈ አይሁድ የሚጠሉትን፤ ነገረ መስቀሉን በሰዎች ሁሉ ፊት ሳናፍር ልንመሰክር የምንችልበትን ትእምርተ መስቀል መጠቀማቸው የሚያስነቅፍ ሊሆን አይችልም። ለዚህም ነው የዓለም ክርስቲያኖች ከዕፅ ወይም ከወርቅ ወይም ከብር

የመስቀል ቅርጽ ሠርተው ክርስቶስን በማያምኑ ወገኖች ፊት
የሚቆሙት።
በተለይ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሁሉም ሊያየው በሚችል
መልክ መስቀልን በአንገታቸው በማንጠልጠል፤ በግንባርና
በእጆቻቸው በመነቀስ፤ በልብሶቻቸው ላይ በመጥለፍ፤
በጣቶቻቸውም በማማተብ፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶ
አድኖናል፤ በዚያም አድኖናል እያሉ በምስክርነት ሕይወት
ውስጥ ጸንተው የምናገኛቸው። በተናጠል ብቻ ሳይሆን
በጋራም ደመራን በመሰሉ የመስቀል በዓላት እንደ ሐዋርያው
“አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን
ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርቶስን እንሰብካለን” እያሉ
በአደባባይ ያከብራሉ /1 ቆሮ. 1፡22/። ስለዚህ ትእምርተ
መስቀልም ይሁን የመስቀል በዓላት ለዚህ አይነት
ሃይማኖታዊ ዓላማ ሚና ያላቸው በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ
መሠረት የላቸውም ማለት አይቻልም። ትእምርትን ወይም
ምልክትን መጠቀምም በራሱ የሚያስነቅፍ አይደለም።
ምልክትን ለመታሰቢያም ለምስክርነትም የእግዚአብሔር
ሕዝብ ሲጠቀም እንደኖረ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ
እናገኛለን። “ኢያሱ ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው ከእስራኤል
ልጆች የታወቁትን በሥራ ሁለት ሰዎች ጠራ። ኢያሱም
አላቸው በኔና በእግዚአብሔር ፊት ወደ ዮርዳኖስ መካከል
ዕለፉ፤ እያንዳንዱ ሰው በዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ቁጥር

በትከሻው ላይ አንድ አንድ ድንጋይ ከዚያ ይሸከም፤ እነዚህ ምልክት ይሆኑላችኋል፤ ልጅህ ነገ እነዚህ ድንጋዮች ምንድናቸው ብሎ በጠየቀህ ጊዜ ልጅህን እንዲህ ትለዋለህ፤ አንተ በምድር ሁሉ ጌታ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት ስንሻገር የዮርዳኖስ ወንዝ ስለደረቀ ነው፤ እነዚህ ድንጋዮች ለእስራኤል ልጆች ለዘላለም መታሰቢያ ይሆናሉ” የሚል ቃል ተጽፏል /ኢያ. 4፡4/። ይህ ምልት የእግዚአብሔርን ሥራና ክብር ያስታውሳል እንጂ ሊያስረሳ የሚችልበት ምንም እድል የለም። እስራኤል ዮርዳኖስን የተሸገሩበት የምስክርነት ምልክት እንዲህ ዋጋ ካለው እኛ ከባሕረ እሳት ወደ ቀደመ ርስታችን ገነት መንግሥተ ሰማያት የተሸገርንበት የክርስቶስ መስቀል ምልክትማ ምን ያህል ዋጋና ክብር ይኖረው!

በኢያሪኮ ስለነበረችው ረዓብም ስናስብ “እኔ ለእናንተ ቸርነት እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ለአባቴ ቤት ቸርነት እንድታደርጉ በእውነት ምልክት ስጡኝ” ማለቷን በመጽሐፍ ተጽፎ እናነባለን። ኢያሱ የላካቸው ጎልማሶችም “እነሆ እኛ ወደ ሀገሩ በገባን ጊዜ ሀን ቀይ ፈትል እኛን ባወረድሽበት መስኮት በኩል እሰሪው” ብለዋት ነበር። “ኢያሱም ምድሪቱን የሰለሉ ሁለቱን ሰዎች ወደ ዘማይቱ ቤት ግቡ፤ ከዚያም ሴቲቱንና ያላትን ሁሉ እንደማላችሁላት አውጡ” አላቸው /ኢያ. 2፡ 12/። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለረዓብ የሰጣት ምልክት

እርሷንና ያላትንም ሁሉ ለማዳን የበቃ እንደሆነ ካየን ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ምልክትማ ምእመናንን አንድ በማድረግ ድኅነታችንንም ለማሰብ፤ እንዴት የከበረ አይሆን! በታሪክ እንደሚታወቀው ከንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመን በፊት ክርስቲያኖች የመስቀልን ምልክት ማሳየት ወይም መጠቀም አይፈቀድላቸውም ነበር። ያንን ሲያደርግ የተገኘም በመስቀል ተሰቅሎ ይቀጣ ነበር። እስከዚያም ዘመን ድረስ መስቀል መቅጫ ሆኖ ያገለግል ነበር። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን ከሆነበት እ.ኤ.አ. ከ 337 ዓ.ም. ጀምሮ ግን ክርስቲያኖች የመስቀልን ምልክት በግልጽ ለምስክርነት የመጠቀም ነፃነት አግኝተዋል። ከዚያን ጊዜም ጀምሮ መስቀል የመቅጫ መሣሪያ መሆኑ ቀረ። በመሆኑም ቅዱስ ጳውሎስ “ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ” የሚለውን ቃሉን እያሰቡ ትእምርተ መስቀልን ያለፍርሃት፤ ያለ ሐፍረት ይጠቀማሉ /ገላ. 6፡14/።

ትእምርት ሐሳብን፤ ድርጊትን፤ ፈቃድን የሚያሳይ የሚመሰክር ነው። በወንጌል እንዲሁም ጌታችን ለፍርድ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ “የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል” ተብሎ ተጽፏል /ማቴ. 24፡30/። ሊቃውንት የሰው ልጅ ምልክት የተባለው መስቀል እንደሆነ ያስተምራሉ። በመሆኑም

ትእምርተ መስቀል ክርስቶስ ለሰዎች የሠራውን መልካም ነገር የሚያስታውስ እንጂ የሚያስረሳ የሚሆንበት ምንም እድል የለም።

መስቀል መከበርም ይገባዋል። የመስቀሉን ምልክት ሰዎች ሲያዩ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልንን የፍቅር ሥራ በሚያዩት ሰዎች ልብ ስለሚሥል ክፉን ሐሳብ ለማራቅ መልካሙንም ለማድረግ ኃይል ይሆናል። ርኩሳን መናፍስትም የዲያቢሎስ ሥልጣኔ የተሻረው ክርስቶስ በመስቀሉ ለሰዎች በሠራው ሥራ መሆኑን ስለሚያውቁ ባዩት ቁጥር ይሸሻሉ፤ ይሸነፋሉ፤ ይቃጠላሉም። ያንን በሚያሳዩ በዚያም በሚመሰክሩ ምእመናን ልቡና ያለው በክርስቶስ የማመን ሐሳብ በእነርሱ ፊት ኃይልን ያደርጋል። ለዚህም ነው "መስቀል ኃይላችን ነው፤ መስቀል መጽናኛችን ነው፤ መስቀል ቤዛችን ነው፤ መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው፤ አይሁድ ይክዱታል እኛ ግን እናምነዋለን" የምንለው። የምናምነውም ኃይል አድርጓል ያደርጋልም። ክርስቶስ ከተሰቀለበት ሌላ የከበረ መስቀል የለም። ስለዚህ መስቀል የተሰቀለውን ክርስቶስን ያሳስበናል እንጂ ሊያስረሳ የሚችልበት መንገድ የለም።

ትእምርተ መስቀል ክርስቶስ ከመሰቀሉም ቀድሞ ኃይልና በረከትን አባቶች ይሰጡበት የነበረ፤ እግዚአብሔርም በዚያ ትእምርት ላይ አድሮ ሲባርክና ኃይልን ሲሰጥ ነበር። ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች በባረከ ጊዜ ያደረገውን ማስታዎስ ይቻላል።

“እስራኤልም ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረው፤ እርሱም ታናሽ ነበረ፤ ግራውንም በምናሴ ራስ ላይ አኖረ፤ እጆቹንም አስተላለፈ /አመሳቀለ/” ተብሎ ተጽፏል። / ዘፍ.48፡13/። ሌላም ተጨማሪ ቃል እንይ፤ ክርስቶስ እጆቹን ዘርግቶ በተሰቀለበት መስቀል አምሳል ወይም ምልክት ሊቀ ነቢያት ሙሴ የእስራኤልን ጠላቶች ድል ያደርግ ነበር። ስለዚህም መጽሐፍ እንዲህ ይላል፣ “ሙሴ እጁን ባነሣ ጊዜ እስራኤል ድል ያደርግ ነበር፤ እጁንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር፤ የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር... አሮንና ሑርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር፤ ፀሐይም እስክትገባ ድረስ እጆቹ ተዘርግተው ነበር” በዚህ ጊዜም ህ ትእምርት ኃይል ነበር። ጠላት የተባለ አማሌቅን ድል አድርጎበት ነበርና /ዘጸ. 10፡7-11/። ያለሑርና አሮን ድጋፍ ብቻውን እጆቹን ዘርግቶ፤ ስለ እስራኤል ብቻ ሳይሆን ስለዓለም ለተሰቀለውና ጠላት የተባለ የዲያቢሎስን ኃይልና ሥልጣን ለሻረበት የክርስቶስ መስቀል ምሳሌ ብቻ ሳይሆን የትእምርቱን ኃይልም የሚመሰክር ነው። ያ ትእምርት እንደዛ ኃይልና ክብር ካለው የክርስቶስ መስቀል ምልክትማ ምን ያህል ይከብር! ምንስ ያህል ኃይልን ያደርግ! የሙሴን ትእምርት አሮንና ሑር እንደዚያ ከተሸከሙት የክርስቶስን መስቀል ምልክትማ ካህናትና ምእመናን በጠላት ፊት ሊሸከሙት እንዴት አይገባ! በመጽሐፍ

“ከባላጋራችን የተነሣ በትእዛዝ የተጻፈውን የእዳችንን ደብዳቤ ደመሰሰልን፤ ከመካከላችንም አራቀው፤ በመስቀሉም ቸነከረው” እንዲል የክርስቶስ መስቀል ጠላት ዲያቢሎስ በእውነት የተሸነፈበት ጥበብና ኃይሉ ነውና /ቆላ 2፡14/። ሙሴ በሰውነቱ የሠራው ትእምርት በጠላቶቹ ፊት ኃይልን እንዳደረገለት ለሚያምኑት ሁሉ ከጠላት ፍላጻ ይድኑ ዘንድ ኃይል የሚሆን ምልክትን እንደሚሰጣቸው ክቡር ዳዊት “ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሀቸው” ሲል ተናግሯል /መዝ. 59፡4/። እርሱም የክርስቶስ የመስቀሉ ምልክት ነው። ያም የሰው ልጅ ምልክት ተብሎ በወንጌል የተጠቀሰው ነው /ማቴ. 24፡ 30/። ስለዚህ የክርስቶስ በሆኑት ነገሮች ሁሉ እንደምንባረክ፤ ኃይልም እንደምናገኝ እናምናለን። ክርስቶስን ከመስቀሉ፤ ክርስቶስን ከእናቱ፤ ክርስቶስን ከነብያቱ ከሐዋርያቱ፤ ወዘተ ነጥሎ ማሰብ እንደሚገባ ቤተ ክርስቲያን ነጥላ ልታስተምር አትችልም። ይሄ የእምነትም ጉዳይ ነው። ሃይማኖታችን ከተራ ፍልስፍና የጸዳ ሊሆን ይገባዋል።

በሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት ልብሱን ብቻ የዳሰሰሁ እንደሆነ እድናለሁ ማለቷን እናስተውል /ማር. 5፡8/። ይህቺ ሴት ያላትን እምነት እናስብ፡ “ክርስቶስ እጆቹን ጭኖብኝ፡ እግሮቹን ዳስሼ” አላለችም፤ “ልብሱን ብቻ” አለች እንጂ። ልብሱ የክርስቶስ ነውና። እርሱ/አካሉ/ ካልሆነ

ኃይልን በእምነት አናገኝም አይባልም። “አካሉን እንጂ ጥላውን አልፈልግም፤ አካሉን እንጂ ልብሱን አልፈልግም፤ የተሰቀለውን እንጂ መስቀሉን አልፈልግም፤ ወልድን እንጂ ወላዲቱን አልፈልግም...” ወዘተ አላለችም። እነዚህ ሁሉ የእርሱ ስለሆኑ ይከብራሉ። ከእርሱም የተነሣ በጸጋ የከበሩ መሆናቸውን እንደዚያች ሴት እናምናለን። ከዚህ በወጣ ለዓለም በሚመች ከንቱ መለፍለፍ ልባችን መድከም አይገባውም። ለምናምን ሰዎች የክርስቶስ በሆነው ነገር ሁሉ በረከት ኃይል እንደምናገኝ እናምናለን። ይህ ማለት የእርሱ የሆኑት ሁሉ እርሱን ናቸው ማለት አይደለም። የእርሱ የሆኑት ግን ከእርሱ የተነሣ የከበሩ መሆናቸውን እናምናለን። አስቀድሞም በትንቢት ስለእርሱ ብቻ ሳይሆን ከእርሱ የተነሣ ስለሚከብሩ ሁሉ ተናግሯል። ስለለበሳቸው ልብሶች እንኳን “ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፣ በቀሚሴም ላይ እጣ ተጣጣሉ” /መዝ.21፡18/ ማለቱን እናነባለን። የተሰቀለበት መስቀልና የመስቀሉ ምልክትም እርሱን የሚያሳይና ስለእርሱ የምንመሰክርበት በመሆኑ የከበረ ነው። አንዳንዶቹ የምታከብሩት ክርስቶስ የተሰቀለበትን ዋናውን መስቀል ሳይሆን ክፋውም ደጉም ሰው የቀረጸውን ምልክቱን በመሆኑ አግባብ አይደለም ሲሉ ይሰማሉ። ለዚህ ግን ብዙ ሳንል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኖዳ ሣልሳዊ ክሌዎፓ ዘሩማኒያ የተባሉ ክርስቲያን በአንድ ወቅት ለዚህ ዓይነት ጥያቄ

የሰጡትን መልስ ይህንን ጥያቄ ላነሡላቸው ወገኖች መልስ
ሲሰጡ የጠቀሱትን ንግግር በዚህ አጋጣሚ እናንሣው፤
ክሌዎፓ ዘሩማኒያ እንዲህ ብለው ነበር “ይህንን በቅዱሳት
መጻሕፍትም ዘንድ እናደርገዋለን፤ በዛሬ ዘመን ቆጥረን
የማንጨርሳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች በዓለም ላይ
አሉን፤ በእናንተ ሐሳብ ከሆነ እነዚህን በክፉዎችም በደጎችም
ማተሚያ ቤቶች ወይም አሳታሚዎች ታትመው የሚሰራጩ
ቅጂዎች በመሆናቸው ማክበር የለብንም ማለት ነው፤
ዋናውን /በነብያት በሐዋርያት እጅ የተጻፉ/ ቅጂ ብቻ
መያዙ /እርሱን ብቻ ማክበር፤ በዚያም ብቻ መባረክ/ አለብን
ማለት ነው። ስለዚህ የቀረበው ይህ አስተሳሰብ ግን
ለምክንያታዊ ሰው የሚያሳምን አይደለም” ብለው ነበር።
በመሆኑም ጠያቂያችን በትእምርተ መስቀል ላይ
ኦርቶዶክሳውያን ያለን እምነት ከላይ ከጠቀስናቸው
የመጻሕፍት ምስጢር የተገኙ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ የሠራልንን የፍቅር ሥራ /ነገረ ድኅነት/ ወይም
ወንጌልን የምንመሰክርበት የምናስተምርበት በዚያም ኃይል
የምናገኝበት በመሆኑ መጽሐፋዊ መሠረት ያለውና
ክርስቶስንም በማሰብ የሚያጸና ነው።

2/ የግማደ መስቀሉ ታሪክ

የግሸን ማርያም ደብር በወሎ ክፍለ ሀገር በአምባሰል አውራጃ ውስጥ የምትገኝ ደብር ናት። ይህች ደብር በሐይቅና በመቅደላ ፣ በደላንታ ፣ በየጁ መካከልና በበሸሎ ወንዝ አዋሳኝ የምትገኝ በሩአ አንድ የሆነ ዙሪያዋን በገደል የተከበበች በመስቀል ቅርጽ የተፈጠረች ልዩ ቦታ ናት። የአለም መድኃኒትን ክርስቶስን አይሁዶች ከስቀሉት በኋላ መስቀሉ ታምራትን በማድረጉ የተበሳጩት አይሁዳዊያን መስቀሉ ከተቀበረበት ቦታ ላይ ቆሻሻ አባራ በመጣል ለ 300 አመታት ያህልታላቅ ተራራ አድርገው ደበቁት። ንግስት እሌኒም በእግዚአብሔር ፈቃድ አስውጥታ ቤተመቅደስ አሰርታ አስቀምጣው ታላላቅ ታምራቶችን አደረገ። ከእስራኤላዊያንም እጅ የፋርስ ንጉስ ማርኮ በወሰደው ጊዜ እስራኤላዊያን የሮማን ንጉስ ሕርቅያልን እርዳታ በመጠየቅ አስመለሱት። ከዚህም በኋላ በኃያላን ነገስታት መካከል መስቀሉን እኔ እወስድ እኔ እወስድ ተጣሉ። የኃይማኖት መሪዎችም ተሰባስበው መስቀሉ በእጣ እንድክፋፈል አደረጉ። ቀኝ እጁ የተቸነከረበትና ያረፈበትም ግማድ መስቀል ለአፍሪቃ በደረሳት ጊዜ የግብጽ (የእስክንድርያ ፓትርያርክ) ተቀብሎ ግብጽ አስቀመጠው። በግብጽም ለብዙ ዘመናት ይህል ኖረ። በኢትዮጵያዊው አፄ ዳዊት ዘመነ መንግስት የግብጽ ክርስቲያኖች ከግብጻዊያን አህዛቦች ዘንድ ስቃይ ደረሰባቸው፤ ለኢትዮጵያዊው ንጉስ ዳዊትም ስቃዩን ያስታግስላቸው ዘንድ ተማፀኑት። ንጉሱም የክርስቶስ ልጆች መከራ ደረሰባቸው ብሎ 20,000 ሰራዊት አስከትሎ ወደ ግብጽ በታላቅ ቁጣ ገሰገሱ በዚህም ግዜ ግብጻዊያን አህዛቦች ፈሩ ተንቀጠቀጡ። ንጉሱም ፈጥነው እርቅ እንድያደርጉ ካልሆነ ግን ግብጻዊያንን በታላቅ ቁጣ

እንደሚያጠፋቸው መልእክት ላከ። ግብጻውያንም ፈጥነው ታረቁ። በዚህም ጊዜ ግብጻዊያን ክርስቲያኖች በንጉሱ ዳዊትና በኢትዮጵያን ክርስቲያን ወገኖች ተደስተው ለንጉሱ 12,000 ወቄት ወርቅ ለንጉሱ የእጅ መንሻ ላኩላቸው ። ንጉሱ ግን ይህንን ስጦታ መልሰው በመላክ ግማደ መስቀሉን እንድሰጧቸው በትህትና አመለከቱ። በዚህም ጊዜ የእስክንድርያ(የግብጽ) ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ተወያይተው መስቀሉን ስናር(ሱዳን) ድረስ በክብር መስከረም 21 ቀን አቀበሏቸው። ንጉሱ አፄ ዳዊትም ተመልሰው ኢትዮጵያ ሳይደርሱ በክብር አረፉ። የእሳቸውም ልጅ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ እንደነገሰ ወደ ስናር ሂዶ ግማደ መስቀሉን አምጥቶ በመናገሻ ከተማቸው በደብረ ብርሃን መቅደስ አሰርተው ለማስቀመጥ ሲደክሙ ሌሊት በራዕይ " አንብር መስቀልየ በድበ መስቀል(መስቀሌን በመስቀልያ ቦታ አስቀምጥ) የሚል ትዕዛዝ ከጌታ ዘንድ መጣ። ይህንም ቦታ ለሚገኝት ብዙ አድባራትን ዞሩ አላገኙምም። ንጉሱ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ እግዚእብሔርን ለመጠየቅ 7 ቀን ሱባኤ ያዙ ፤ በዚህም ግዜ አምደ ብርሃን እየመራ እንደሚወስዳቸው ተነገራቸው። አምደ ብርሃኑም እየመራ በመስቀልያ በተፈጠረች ልዩ ተራራ ግሸን አደረሳቸው መስከረም 21 ቀን ደረሱ። በዚያም ታላቅ ቤተ መቅደስ አሳንጸው መስከረም 21 ቀን በዓሉን አከበሩ። ንጉሱ አፄ ዘርአ ያዕቆብም በዚህ ቀን በጽሁፍ ለምዕመናን አቀረቡ ከዚህም ግዜ ጀምሮ መስከረም 21 ቀን ይከበራል በቦታውም ልዩ ልዩ ታምራቶች ይደረጋሉ። የተራራው አቀማመጥ ከፎቶው እንደምታዩት መስቀልያ ነው። ከእመቤታችን ክብረ በዓል ያሳትፈን አሜን።

Oct 1, 2014 · Public

3/ ቅዱስ መስቀል ፍቅር ነው

ከተለያዩ ምንጮች

የመስቀል በዓል እንጨት ተደምሮ እሳት ተቀጣጥሎ ለምን ይከበራል? ለመስቀሉ መገኘት የሮሙ ንጉስ ቆስጠንጢኖስ እና የንግስት ዕሌኔ ሚና ምን ነበር? ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት መጣ?

ዕሌኒና ተርቢኖስ የሚባሉ ሁለት ደጋግ ክርስቲያኖች ተጋብተው ይኖሩ ነበር። ተርቢኖስና ዕሌኒ ኑሮአቸው ፍቅርና ሰላም የሰፈነበት በመሆኑ ለብዙ ሰዎች እንደ ምሳሌ ሆነውይኖሩ ነበር። ተርቢኖስ ነጋዴ ነበር።ከዕለታትአንድቀን ራቅ ወዳለ ሀገር በመርከብለንግድ ሄደ። ዕሌኒም ባለቤቷ ተርቢኖስ ለንግድ ወጥቶ እስኪመለስ ስለባሏ ከመጸለይና ከማሰብ በቀር ከግቢዋ አትወጣም ነበር። አንድ ጊዜ ተርቢኖስ ለንግድ ሄዶ ብዙ ዓመታትን ቆይቶ ከጓደኞቹ ጋር ወደሀገሩ ሲመለስ ከነጋዴዎች አንዱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ከሽፍታና ከማዕበል ከልዩ ልዩ አደጋ ተርፈን በሰላም ተመልሰን ግን ሚስቶቻችን ሌላ ሳይወዱ ሳይለምዱ እናገኛቸው ይሆን? ብሎጠየቀ። ተርቢኖስ ግን "እንኳን በሰላም አደረሰን እንጂ ሚስቴን በዚህ አልጠረጥራትም" ብሎ ሲመልስ ሌላው ጓደኛው "ያንተሚስት ከማን ትበልጣለችና ነው አሁን ሄጄ ከሚስትህ ጋር ለምዳኝ ወዳኝ ወድጃት ብመጣስ ምን ይቅጣህ?" አለው።

ተርቢኖስም በሚስቱ እሌኒ ተማምኖና ይህንን ብታደርግ ይህን ያህል ዓመት የለፋሁበት ሀብት ከንትርፉ ውሰድ አንተም ብታደርግ እንዲሁ ሀብትህ

ከነትርፉ ለእኔ ይሁን ተባብለው ተወራረዱ።ከዚያም መርከቡ ወደብ ከመድረሱ በፊት ነጋዴው ወደ ዕሌኒ ቤት ደረሰና በሩን አንኳኩቶሠራተኛይቱን ዕሌኒን ማነጋገር እፈልጋለሁና ንገሪልኝ ብሎ ጠየቃት። እሷም እያፈረችየተላከችውን ለዕሌኒ ነገረቻት ዕሌኒም ተቆጥታ ከመች ወዲህ ነው እንግዳ የማነጋግረው ብላ አሳፈረቻት።

ሠራተኛይቱም ለነጋዴው መልሱን ስትነግረው ነጋዴው እንደማይሆንለት ከተረዳበኋላ ሌላ ተንኮል አቀደና ለሠራተኛይቱ ባልና ሚስቱ ብቻ የሚያውቁትን አንድ ነገር ብቻብትሰጪኝ ብዙ ገንዘብ ወርቅ እሰጥሻለሁ ብሎ ወርቅ ሰጣት። ሠራተኛይቱም ሁለቱ ብቻ የሚያውቁትን የእመቤቴ ሀብል አለ ያንን እመጣልሀለሁ መጀመርያ አንተ በከተማው ውስጥ እየዞርህነጋዴዎችን መጡ የብስ ረገጡ እያልክ አስወራ ከዚያም ተመልሰህ እንድትመጣ ብላ ሰደደችው።ነጋዴውም እንደተመከረው የነጋዴዎቹን መምጣት በከተማይቱ እንዳወራ የነጋዴዎቹ ቤተሰቦችነጋዴዎችን ለመቀበል ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ። የዕሌኒም ሰራተኛ እመቤቴ ነጋዴዎች መጡተብሎ ይወራልና። ባለቤትዎ በሰላም ስለመጡ ይዘገጃጁ ገላዎን ይታጠቡ ብላ መከረቻት።ዕሌኒም ገላዋን ስትታጠብ ያንገቷን ሐብል ቁጭ ካደረገችበት ቦታ ሠራተኛይቱ አንስታ ለነጋዴውበተቃጠሩበት ዕለት ሰጣች። ነጋዴውም ለሠራተኛይቱ የውለታዋን ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአት ደስእያለው ወደ ጓደኞቹ ሄደ። ለተርቢኖስ ሚስትህን ለምጃት ወድጃት መጣሁ አለው ተርቢኖስምውሸት ነው ለዚህ ምን ምልክት አለህ ብሎ ጠየቀው። ተንኮለኛውም ነጋዴ ያንን ሐብል አውጥቶይህ ሐብል የሚስትህ አይደለምን ብሎ ሰጠው ተርቢኖስም ደነገጠ የሚናገረውን አጣ።በውርርዱምመሰረት

ሀብቱን ሁሉ አስረከበና ባዶ እጁን ወደቤቱ እያዘነ እየተቆጨ ሔደ።

ባለቤቷንበናፍቆትና በታማኝነት ስትጠብቅ የከረመችው ዕሌኒ በተርቢኖስ ያልተለመደ ሀዘንና ብስጭት ግራተጋብታ ወንድሜ ምን ሆነህል? ለወትሮው እንኳን ይህን ያህል ዘመን ተለያይተን ቀርቶ ለጥቂትቀናት ተለያይተን እንኳ ለጥቂት ቀናት ተለያይተን ስንገናኝ እንነፋፈቃለን። አሁን ግን ከመጣህበትጊዜ ጀምሮ አዝነህ አይህለሁ ብላ ጠየቀችው። ተርቢኖስም ብዙ የደከምኩበትና የለፋሁበት ሀብትንብረቴ እንዳለ ማዕበል አጠፋብኝ እኔ ያላዘንኩ ማን ይዘን አላት። እሌኒም የተማረች ናትናእግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሣ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን እንዳለ ኢዮብን አስበውአንተ እንኳን በሰላም መጣህ እንጂ ሀብቱ ውሎ አድሮ ይመጣል። እያለች አጽናናችው።ተርቢኖስም እንግዲህ በተከበርኩበት ሀገር ተዋርጄ፣ በሰጠሁበት ሀገር ለምኜ ለመኖር አልችልምናወደሌላ ወደማያውቁኝ ሀገር እሔዳለሁ አንቺ ግን ሁሉ ይወድሻል ያከብርሻል ከወደድሽው ጋር ኑሪአላት። ዕሌኒም በደስታ ጊዜ አብሬህ እንደሆንኩ በችግርም ጊዜ ልለይህም የኔንና ያንተን አንድነትችግር አይፈታውም ከአንተ ተለይቼ ወዴት እቀራለሁ ወደምትሄድበት አብሬህ እሄዳለሁ ብላተነሳች።

ሁለቱም ቤታቸውን ጥለው ሲሄዱ በመንገድ ላይ ተርቢኖስ በልቡናው ይዞት የነበረውን ምሥጢርአወጣው "ዕሌኒ ስወድሽ የጠላሽኝ ሳምንሽ የከዳሽኝ ምን አድርጌሽ ነው?" ብሎ ጠየቃት። ዕሌኒምእኔ አንተን አልጠላሁም አልከዳሁምም ይህንን ሐሳብ እንዴት አሰብህ ብትለው ከኪሱ አውጥቶሐብሉን አሳያትና የሆነውን ሁሉ ነገራት። ዕሌኒም ያልጠበቀችው ነገር ስለተፈጸመ አዝና የሆነውንእውነተኛ ታሪክ በሙሉ ነገረችው።

ተርቢኖስ ግን አላመናትም። ከባህር ዳር በደረሱ ጊዜ በቁመቷልክ ሳጥን አሠርቶ ዕሌኒን በውስጡ አስገባትና ብታደርጊውም ባታደርጊውም እንደሥራሽ ሥራሽያውጣሽ ብሎ ወደ ባህሩ ወረወራት። ዕሌኒ ያለችበት ሳጥን በፈቃደ እግዚአብሔር እየተንሳፈፈከወደብ ደረሰ በዚያ ወደብ አካባቢ ምዕራብ ሮምን ያስተዳደር የነበረው ኮስታንዲዮስ /ቁንስጣ/የተባለው ንጉሥ ነበርና ሳጥኑን አይቶ አውጥቶ እንዲከፍቱት ወታደሮችን አዘዘ። ሳጥኑንአውጥተውም ሲከፍቱት እጅግ የተዋበች ሴት ሆና አገኟት ንጉሡም ዕሌኒን ወስዶ ሚስቱአደረጋት። ኮስታንዲዮስ /ቁንስጣ/ የመክስምያኖስ ቄሳር ሆኖ ምዕራብ ሮምን ያስተዳደር ነበር። ንግስት ዕሌኒም በ272 ዓ.ም ታላቁ ቆስጠንጢኖስን ወለደችለት ቆስጠንጢኖስም ገና በወጣትነቱየአባቱ እንደራሴ ሆኖ እንደሠራ አባቱ ሞተ። የአባቱ ባለሟሎችና ህዝቡ ተስማምተው የ18 ዓመቱን ቆስጠንጢኖስን በአባቱ ቦታ ሐምሌ 25 ቀን 316 ዓ.ም በሮም ምዕራብ ክፍል በገላትያአነገሡት። በጦር ሜዳዎች ብዙ የጀግንነት ሥራዎች ስለሰራ በሠራዊቱ ዘንድ ይወደድ ነበር።

ንግሥት ዕሌኒ ልጅዋን ቆስጠንጢኖስን ከልጅነቱ ጀምሮ ስለክርስትና ሃይማኖትና ስለክርስቲያኖችመከራ ታስተምረው ስለነበር በክርስቲያኖች ላይ የነበረው አመለካከት በሮም ከነገሡት ቄሣሮች ሁሉየተሻለ ነበር። በተለይም በ312 ዓ.ም ከጠላቱ ከመክስምያኖስ ጋር ለመዋጋት ምታ ነጋሪት ክተትሠራዊት ብሎ ለዘመቻ እንደተሰለፈ በራዕይ በሰማይ ላይ "በዚህ መስቀል /ምልክት/ ጠላትህን ድልታደርጋለህ" የሚል መስቀልና ጽሑፍ ስላየ ለሠራዊቱ የመስቀል ምልክት በመሳሪያቸው እናበሰንደቅ ዓላማው ላይ

እንዲያደርጉ አዘዘ። ወደያው ጦርነት ቢገጥም በቲቤር ወንዝ ድልድይ ላይጠላቱን ድል ነስቶ በጠቅላላው የሮም መንግስት ግዛቶች ሁሉ ገዥሆነ።

ታላቁ ቆስጠንጢኖስ የሮም ንጉሠ ነገሥት ከሆነ በኋላ በ300 ዓመታት ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜለክርስቲያኖች የነጻነት ዐዋጅ ዐወጀ። ክርስትናም ብሔራዊ ሃይማኖት ተባለች። ንግሥት እሌኒምበተፈጠረላት አመች ሁኔታ በመጠቀም የጌታችን መስቀል ከተቀበረበት ለማውጣት በ327 ዓ.ም ወደኢየሩሳሌም ሔደች። ዕሌኒ ልጅዋ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን ከሆነላት ወደ ኢየሩሳሌም ሔዳመስቀሉን ለመፈለግ እንዲሁም በኢየሩሳሌም ያሉ ቅዱሳት መካናትንና አብያተ ክርስቲያናትንለማሳነጽ ለእግዚአብሔር ተሳለች። ከዚህ በኋላ ቆስጠንጢኖስ አምኖ በ337 ዓ.ም ተጠመቀ። ቅድስት ዕሌኒ ወደ ኢየሩሳሌም ሔደች ከእርሷም ጋር ብዙ ሠራዊት ነበር። እንደደረሰችም ስለከብረ መስቀል መረመረች ጠየቀች። ቦታውን የሚያስረዳት አላገኘችም። የአይሁድ ወገን እንቢቢሉም በኋላ ግን ባደረገችው ጥረት አረጋዊው ኪራኮስ የጎልጎታን ኮረብታ አመለከታት አስቆፍሪውብሎ ነገራት ኪራኮስም ዘመኑ ከመርዘሙ ጋር ተያይዞ እውነተኛው ተራራ ይህ ነው ብሎ ማሳየትባለመቻሉ ከሦስቱ ተራሮች አንዱ ነው ስላላት አይሁድ ተራሮቹን ይቆፍሩ ዘንድ አዘዘቻቸው።የጌታችን ቅዱስ መስቀል ከጌታ ሞት እያመነ በተቸገሩ ግዜ ማንም እንዳያገኘው የኢየሩሳሌም ነዋሪሁሉ የእቤቱን ቆሻሻ የከበረ መስቀል ባለበት ቦታ እንዲጥል አይሁድ አዝዘው ስለነበር ከሁለት መቶዓመት በላይ ጥራጊ ስለጣሉበት ታላቅ ተራራ ሆነ።

ዕሌኒ ተራሮቹን ለማስቆፈር ከሦስቱ ተራሮች የቱ እንደሆነ ለመለየት ደመራ

አስደምራ ብዙእጣንም በመጨመርና በማቃጠል ከአኢየሩሳሌም ወጣብለውያሉትንኮረብቶች አሳያት። የእጣኑ ጢስ ወደ ሰማይ በመውጣት በቀጥታ ተመልሶ መስቀሉ ባለበት ተራራ ላይ በማረፍናበመስገድ መስቀሉ ያለበትን ትክክለኛ ስፍራ አመለከታት። ቅዱስ ያሬድም "ሰገደ ጢስ" ጢሱሰገደ ብሎታል። ከዚያም መስከረም 16 ቀን ቁፋሮው እንዲጀመር አዘዘች። ሰባት ወር ያህልከተቆፈረ በኋላ መጋቢት 10 ቀን ሦስት መስቀሎች በአንድነት ተገኙ። የክብር ባለቤት ጌታችንየተሰቀለበት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ተቸገሩ። የሞተ ሰው አምጥተው በሁለቱ መስቀሎች ላይበተራ ቢያስቀምጡት አልተነሣም። በመጨረሻ በአንዱ መስቀል ላይ ቢያስቀምጡት ያን ጊዜየሞተው ሰው ተነሣ። በዚህም የጌታን መስቀል ለዩት። ዕሌኒም የጌታ መስቀል እንደሆነ አወቃሰገደችለት። ክርስቲያኖች ሁሉ ሰገዱለት። በየሀገሩ ያሉ ክርስትያኖች ሁሉ የመስቀሉን መገኘትበሰሙ ግዜ መብራት አብርተው ደስታቸውን በመግለጥ ለዓለም እንዲታወቅ አደረጉ። በዚህምምክንያት ይህ ታላቅ የድኅነት ምልክት የሆነው መስቀል የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ደመራበመደመር በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች።

በመስቀል ደመራ በዓል ትዕይንት

ንግሥትዕሌኒ መስከረም 16 ቀን 320 ዓ.ምበዕጣን ጢስ ምልክት ቁፋሮ አስጀምራ መጋቢት 10 ቀን አግኝታ በማውጣት ታላቅ ቤተመቅደስ ጎልጎታ ላይ ሠርታ በክብር አስቀመጠችው ይህመስቀልም ከዚያ ዕለት ጀምሮ እንደ ፀሐይ እያበራ ድውይ እየፈወሰ አጋንንት እያባረረ ልዩ ልዩተአምራት እየሰራ ሙት እያነሳ ዕውር እያበራ ተአምራቱን ቀጠለ። ይህንንም ከኃያላን

ነገሥታትመካከል የፋርስ ንጉሥ መስቀሉን ማርኮ ፋርስ ወስዶ አስቀመጠው። በዚህ ጊዜ የአየሩሳሌምምዕመናን የድሉን ዜና ሰምተው ስለነበር የአንድ ቀን መንገድ ያህል ሄደው በመቀበል ካህናቱበዝማሬና በቸብቸቦ ወንዱ በሆታ ሴቱ በእልልታ ሆ! እያሉና ችቦ አብርተው ተቀብለዋቸዋል።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንም ለመስቀል ችቦ እያበሩ በዓሉን በሆታ በእልልታበስብሐተ እግዚአብሔር የምታከብረው ይህንን ታሪካዊ ትውፊት በመከተል ነው። ብዙየቤተክርስቲያን አባቶች እንደሚሉት ንጉሠ ሕርቃል ይህንን ታላቅ ድል ለማግኘትና የጌታን ቅዱስመስቀል ከአሕዛብ /ከፋርሶች/ እጅ ለማስመለስ የቻለው በዚያን ጊዜ አብያተ ክርስቲያንናት ሁሉለአንድ ሳምንት /አንድ ሱባዔ/ ባደረጉት ጾም ጸሎት ነው። ይህንንም ለማስታወስና ጌታንለማመስገን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንና የግብጽ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያንበየዓመቱ የፀቢይ ጾም /የጌታ ጾም/ ከመጀመሩ አስቀድሞ "ጾመ ሕርቃል" ብለው አንድ ሳምንትይጾማሉ።

የጌታ መስቀል ለብዙ ግዜያት ኢየሩሳሌም ከቆየ በኋላ ነገሥታት ይህን መስቀል እኔ ልውሰድ እኔልውሰድ በማለት ጠብ ፈጠሩ። በዚህ ጊዜ የአንጾኪያ፣ የኤፌሶን፣ የአርማንያ፣ የግሪክ፣የእስክንድርያ፣ የመሳሰሉት የሃይማኖት መሪዎች ጠቡን አበረዱት ከዚያም አያይዘው በኢየሩሳሌምየሚገኘውን የክርስቶስን መስቀል ከ4ት ከፍለው በዕጣ አድርገው በስምምነት ተካፍለው ከሌሎችታሪካዊ ንዋያተ ቅዱሳት ጋር በየሀገራቸው ወስደው በክብር አስቀመጡት የቀኝ ክንፉ የደረሰውለአፍሪቃ ስለነበር ከታሪካዊ ንዋየ ቅዱሳት ጋር በግብጽ የሚገኘው የእስክንድርያ

ፓትርያርክ ተረክቦወስዶ በክብር አስቀመጠው።

ግማደ መስቀሉ ወደ ቅድስት ሀገር ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ አገባብ

ግማደ መስቀሉ ለብዙ ዘመን በእስክንድርያ ሲኖሩ በግብጽ ያሉ እስላሞች እየበዙ ኃይላቸውእየጠነከረ ሲሔድ በእስክንድርያ የሚኖሩ ክርስትያኖች ላይ ሥቃይ ያጸኑባቸው ጀመር።ክርስቲያኖቹም አንድ ሆነው መክረው ለኢትዮጵያዊው ዓጼ ዳዊት እንዲህ የሚል መልእክት ላኩ"ንጉሥ ሆይ! በዚህ በግብጽ ያሉ እስላሞች መከራ አጽንተውብናልና ኃይልህን አንሥተህአስታግስልን ብለው ጠየቁት ዳግማዊ ዓጼ ዳዊትም ለመንፈሳዊ ኃይማኖት ቀንተው የክርስቶስ ፍቅርአሰገድዷቸው 20,000 ሠራዊት አስከትለው ወደ ግብጽ ዘመቱ በዚህ ጊዜ በግብጽ ያሉ ኃያላን ፈሩተሸበሩ ንጉሡ ዳግማዊ ዳዊትም እንዲህ የሚል መልዕክት ለእስላሞቹ ላከ በተፈጥሮ ወንድሞቻችሁከሆኑት ክርስቲያኖች ካልታረቃችሁ ሀገራችሁን መጥቼ አጠፋለሁ" የሚል ማስጠንቀቂያ ላከ።የንጉሡ መልዕክትም ለእስላሞቹ እንደደረሳቸው ፈርተው እንደ ጥንቱ በየሃይማታቸው ጸንተውበሰላም እንዲኖሩ ከክርስቲያን ወንድሞቻቸው ጋር ታረቁ። መታረቃቸውን ዓጼ ዳዊት ሰሙበዚህም ጉዳይ ንጉሡ ደስ አላቸው።

እግዚአብሔርንም አመሰገኑ በግብጽ የሚኖሩ ክርስቲያኖችምከ 12,000 ወቄት ወርቅ ጋር ደስታቸውን ለኢትዮጵያዊው ንጉሥ ለዳግማዊ ዳዊት በደብዳቤአድርገው ላኩላቸው። ንጉሡም የደስታውን ደብዳቤ ተመልክተው ደስ አላቸው ወርቁን ግንመልሰው በመላክ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ጻፉ። በግብጽ የምትኖሩ የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ የላካችሁልኝ 12,000 ወቄት ወርቅ መልሼ ልኬላችኋለሁ። የእኔ ዓላማ

ወርቅፍለጋ አይደለም የክርስቶስ ፍቅር አስገድዶኝ በተቻለኝ ችግራችሁን ሁሉ አስወገድኩላችሁ አሁንምየምለምናችሁ በሀገሬ ኢትዮጵያ ረሀብና ቸነፈር ድርቅ ስለወረደብኝ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስየተሰቀለበት ቅዱስ መስቀልና የቅዱሳን አጽም ከሌሎች ክቡራን ዕቃዎች ጋር እንድትልኩልኝ ነውየሚል ነበር።

በእስክንድርያም ያሉ ምዕመናን ይህ መልዕክት እንደደረሳቸው ከሊቃነ ጳጳሳትና ከኤጲስ ቆጶሳቱጋር ውይይት በማድረግ ይህ ንጉሥ ታላቅ ክርስቲያን ነው። ስለዚህ ልቡን ደስ እንዲለውየፈለገውን የጌታችንን ግማደ መስቀል ከቅዱሳን አጽምና ንዋየ ቅዱሳት ጋር አሁን በመለሰው ወቄትወርቅ የብርና የነሐስ የመዳብና የወርቅ ሣጥን አዘጋጅተን እንላክለት ብለው ተስማምተው በክብርበሥነ ሥርዓት በሠረገላና በግመል አስጭነው ስናር ድረስ አምጥተው ባስረከቧቸው ጊዜ በእጃቸውእያጨበጨቡ በእግራቸው እያሸበሸቡ በግንባራቸው እየሰገዱ በክብር በደስታ ተቀበሏቸው።

በዘመኑ ባንኖርም በመልካም ምኞታችን እንደ ኖርን ይቆጠርልን ዘንድ፣ ተጉዘን ቀራንዮ ባንገኝ፣ ርቀት ቢወስነንም ስለመሻታችን እንደተጓዝን ይደረግልን ዘንድ፣ አንድም ባለንበት አምነን ስላከበርነው በረከቱን ያድለን ዘንድ። ኑ ቀራንዮ እንሂድ በእግራችን አይደለም በመንፈስ እንጂ፣ ኑ በበዓላችን ቀን መስቀሉን እንዳሰው በእደ ሥጋ አይደለም በዕደ ጎሊና እንጂ፣ የመስቀሉ ፍቅር ምሥጢር ቀራንዮ እንዲገኝ ዛሬም ያዘጋጀነው ይህ የመስቀል በዓል የቀራንዮ አካል ነው። አንድም ግሸን ደብረ ከርቤ እንሂድ የእውነተኛው መስቀል አካል ከእኛው ዘንድ አለና። ክርስቶስ ተሰቅሎ ዓለምን ያዳነበት፣ ደሙ የነጠበበት እውነተኛው መስቀል ለዓለም ብርሃኑን

ያበራበትን የምናከብርበት ይህ ቀን ነውና። ምክንያቱም፦

• መስቀል የፍቅር ዙፋን ነውና፤ ቅዱስ ዮሐንስ ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ እስከመጨረሻው ሳይለይ የፍቅሩን መጠን ተረድተዋል። ማን ያርዳ የቀበረ እንዲሉ የጌታን ሕማሙን በዚያች ሌሊት የአዳሩንና የውሎውን ለሰው ልጆች ፍቅር ሲል በሰው ልጆች እጅ የተቀበለውን ጽኑ መከራውን አይተዋልና፤ በመልእክቱም "ፍቅርም እንደዚህ ነው፣ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለ ኀጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዝአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም" (1 ዮሐ. 4: 10) ያለው። የሰቀሉትን እንኳ ወደዳቸው፣ ይቅርም አላቸው። በመስቀሉ ዙፋን በፍቅሩም ድነዋልና "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው " እንዲል።

• መስቀል የጥበብ ቤት ነውና፤ ጠቢቡ ሰሎሞን " ጥበብ ቤትዋን ሠራች ... ፍሪዳዋን አረደች ... ማድጋዋን አዘጋጀች ... ሁሉን ጠራች ... ኑ እንጀራዬን ብሉ ... አላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ፣ በማስተዋል መንገድ ሂዱ ... "(ምሳሌ 9፥ 1-10) ሲል፤ በቅዳሴ መጽሐፍ ላይ ጥበብ መድኀኒታችን ነው በማለት የሚሥጢሩን ባለቤትን ያመሠጥራል፤ በመስቀል ላይ ጥበብ የተባለ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ ሆኖ ዓለም ሁሉ ተመግቦት ድኖአልና። ለእኛ በመስቀል ጥበብ ቤት ላይ የተሰቀለው ጥበብ መድኀኔዓለም በዛሬው በምናከብረው የጥበብ ምሥጢር መገኛ በሆነው የመስቀል በዓል ራስ እርሱ ክርስቶስ ነው። በዚህም እርሱን የዓለምን መድኀን እንሰብክበታለንና። "አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፣ የግሪክ ሰዎች ጥበብን ይሻሉ፣ እኛ የተሰቀለውን ክርስቶስን

እንሰብካለን” (1 ቆሮ. 1፥22-23) እንዲል።

• መስቀል የክርስቲያኖች ሁሉ አርማ ነውና፤ በምድራውያን ልማድ የሀገር ነጻነት በሰንደቅ ዓላማ አርማነት መውለብለብ እንዲታወቅ ሁሉ፣ ዛሬ የሰማያውያን ተስፋና የሕይወት አርማ በዓለም ላሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ መውጣት በክርስቶስ የታወጀበት ሰንደቅ ዓላማ መስቀል ነው። በሀገራችን ከአደይ አበባ ውበት ጋር አንድ ሆኖ የሚውለበለብበት መስከረም 16 ና 17 ልዩ ክብረ በዓሉ ነው። ልዩ የሚያደርገው ከአርማ ጋር የእግዚአብሔር ኀይል መሆኑ ነው። ቅዱስ መስቀል ምንኛ ድንቅ ነው? ዕፅነት/መስቀሉ የተቀረጸበት እንጨት/ ከመለኮት ኀይል ጋር አንድነት፣ ድንቅ ተዋሕዶ፣ አጋንንት የሚርዱለት የክርስቲያኖች ቤዛ ልዩ ምልክት፣ ለመረጣቸው ብቻ ኀይልን ያደርጉበት ዘንድ የታደሉት ግርማ ሞገስ ቅዱስ መስቀል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ”የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነው፣ ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው (1 ቆሮ 1፥18) እንዲል።

የመስቀል ፍቅር ሰው፣ ልዩ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ ”ወሶበ ርእዮሙ እግዚእ ኢየሱስ ለእሙ ወለረድኡ ዘያፈቅር ይቀውሙ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወደውን ደቀ መዝሙርና እመቤታችንን ከእግረ መስቀል ቁመው ባያቸው ጊዜ ሲል፣ ድንግል ልብዋ በሀዘን ጦር ተወግቶ 41 41 የልጅዋን መከራ መቻል ጭንቅ በሆነባት ጊዜ ልጅዋ መሪር ሃዘንዋን ተመለከተ፤ እንዲሁም ከአጠገቧ ካሉት በእንባ ከሚራጩት የኢየሩሳሌም ሴቶች ጋር ከወንድ ወገን የሚያጽናናት አንድ ሰው ቅዱስ ዮሐንስን አየው። ወይቤላ ለእሙ ኦ ብእሲቶ ነዋ ወልድኪ፤ አንች ሆይ

ልጅሽ ይርዳሽ ያጽናናሽ አላት። ውሉድኪ ሲል ነው በዮሐንስ እኛን ለእርስዋ መስጠቱ ነውና። ወይቤሎ ለውእቱኒ ረድ ነያ እምከ፣ ደቀ መዝሙሩንም እነኋት እናትህ ታጽናህ አለው እምክሙ ሲል ነው። በዮሐንስ እርስዋን ለእኛ መስጠቱ ነውና"። (ዮሐ.19፥26-27)ብሎዋል። እነሆ ተመልከቱ፣ ለቅዱስ ዮሐንስ የባሕሪያችን መመኪያ የሆነችውን የተወደደች ድንግል እመቤት እናት ትሆነው ዘንድ ከአምላኩ ፈጽሞ ተሰጠችው። ድንግልን ከመስቀሉ ፍቅር ለይቶ ማየት ከቶ አይቻልም።

መስቀል ፍጹም ፍቅር፣ ርኅራሄ፣ የዋህነት እንደሆነ ሁሉ፣ ድንግልም እንዲሁ ፍጹም ፍቅርን የተሞላች የፍጡር ሁሉ ፍቅር ቢደመር የእርስዋን ፍቅር ይደርስ ዘንድ ሊታሰብ አይችልም፤ ርኅራሄዋ እንኳን ለሰው ልጅ ለፍጡር ሁሉ የምታዝን አዛኝት ናት እንጂ፤ በየዋህነትዋ የዋሂት ርግብ የተባለች ፍጹም ናት እንጂ።ድንግል በዚህ ዓለም ሳለች ልጅዋ እንደተሰቀለ ሆኖ በኅሊናዋ ተስሎ፣ ልብዋ በሕማሙ ጦር ተወግቶ፣ ሃዘንዋ ጸንቶ፣ በሰቆቃ ተውጣ፣ እጅዋን ወደ ላይ ዘርግታ አንድም ስለልጅዋ ኀዘን እንባዋን ስታዘራ በሌላም ልጅዋ ይምረን ዘንድ ስለእኛ ስለ ሰው ልጆች ምልጃ ታደርግ ዘንድ ከቀራንዮ ከስቅለቱ ቦታ እንዲሁም ከመቃብሩ ጎልጎታ አንድም ቀን ተለይታ አታውቅም ነበር። ሕማሙን እንደ እርስዋ ማን ተረዳ? ድንግልን የመስቀሉ ፍቅር እንዲገባን አማልጂን ብለን እንማጸናት፣ በአምስቱ ኀዘናትሽ ቃል ኪዳን አስቢን እንላት ዘንድ የዚህ ዓለም ፈተና ግድ ይለናልና። ልጅዋን ወዳጅዋን፣ እስዋንም ደስ እናሰኝ ዘንድ ፍቅርዋን፣ ርኅራሄዋን፣ የዋህነትዋን እንምሰል። ወገኖቼ ቂም በቀል፣ ክፋት፣ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ዘረኝነት፣ወዘተ እንተው፣ ለዚህ ዓለምም ለወዲያኛውም አይጠቅሙምና።

እኛም ዛሬ ቅዱስ ዮሐንስን የመስቀሉ ፍቅር አብነት እናድርገው፣ ይኸውም ልዩ የሚያደርገው መለኮታዊ ፍቅሩን መረዳቱ፣ የመስቀሉ ሥር የፍቅረ ሰው መሆኑ፣ የጌታን የሕማሙን ጥልቀት መጠን ማስተዋሉ፣ ሁል ጊዜ ነገረ መስቀሉን በማሰብ ቁጽረ ገጽ መሆኑ። ከዚህ ዓለም ልዩ በሆነ ፍቅር ጌታውን የመውደዱ፣ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" በማለት አምላክ የሰው ልጅን ከመውደዱ ጋር ሰው ወንድሙን ቢጠላ እግዚአብሔርን እንዳያውቅ በሚለው ጎይለ ቃልና ረቂቅ ምሥጢር ከተግባራዊ ሕይወት ጋር አቅርቦቱን ልብ ልንለው ግድ ይለናል።

በነገረ መስቀሉ አንጻር፣ የድንግል እመቤታችንና የቅዱስ ዮሐንስ ፍቅረ መለኮት ሕይወታቸው ቅድስናን አጎናጽፏቸው ተገኝቷል። እኛም ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ ለሁላችንም "ዓለምንና በዓለም ያሉትን አትውደዱ ... የአባት ፍቅር በውሰጡ የለም፣ ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል" (1ዮሐ. 2፥15.17) በማለት የሕይወቱን ተግባራዊ ትምህርት እንዳስተላለፈልን ሁሉ፤ በዚህ ዓለም ስንኖር ነፍስና ሥጋችንን በፍቅረ መለኮት ተጸምዶ፣ በሕማማተ መስቀል ውስጥ ተገብቶ በፍቅር ውስጥ መኖርን፣ መንፈሳዊ አገልግሎታችን በፍቅረ መስቀል አንጻር ብቻ ሆኖ መሰለፍን፣ መሰባሰባችን በፍቅረ እግዚአብሔር ግብዣ ማድረግን፣ ሥራችንን በፍቅር ውስጥ ማከናወንን ያመለክተናል። ትዳራችን የመስቀል ፍጹም ፍቅር፣ ርኅራሄ፣ የዋህነት የተሞላ ሁል ጊዜ ለይቅርታ ዝግጁ የሆነ በዘለዓለም ሕይወት ተስፋ የተሞላ ሊሆን ይገባዋል። ባጠቃላይም ሕይወታችን በመንፈሳዊ ጎሊና የተዋበና የመስቀሉን ፍቅር የሚያዘክር ይሆን ዘንድ፣እግዚአብሔር እርሱን በመውደድና

በማይዝል በመንፈሳዊ የፍቅር ወላፈን ይጸምደን ዘንድ ፈቃዱ ይሁን። አሜን!!!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር! አሜን!!!

DireTube.com

4/ የዓባይ ወንዝና መስቀሉ ታሪካዊ ትስስር ሲቀጥል!

(መላኩ አላምረው በድሬቲዩብ)

...

የግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አቡነ ታድሮስ ከትናንት በስትያ የመስቀል ደመራ በዓልን በመስቀል አደባባይ አከበሩ።

እንደ መንፈሳዊ አባት ዋናው የመምጣታቸው ዓላማ ሃይመኖታዊ ተልዕኮ፣ የመስቀል በዓልን በማክበር ከበረከቱ ለመሳተፍና ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን ለመጎብኘት ቢሆን ኖሮ... ማለትም የመስቀል በዓልን በመጠቀም በዓባይ ወንዝ (በሕዳሴው ግይድብ ዙሪያ) ላለው ዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ ባይሆን ኖሮ... ምንኛ መልካም ነበር።

ነገር ግን አይደለም። ወደ ሀገራችን የመምጣቱ ነገር ከዓባይ ወንዝ ጋር

ታሪካዊ ትስስር ያለውን የመስቀሉን በዓል ምክንያት በማድረግ ስለ ሕዳሴው ግድብ ለመምከር ነው። እንደሚታወቀው ግማደ መስቀሉ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ የመምጣቱ ምሥጢር የዓባይ ወንዝ ነበር። አፄ ዳዊት የዓባይን ወንዝ እንዳይገድቡ ከግብፅ ለኢትዮጵያ (ለአምላክ ፈቃድ ምክንያት ሆኖ) የተሰጠ ቅዱስ ቅርስ ነው - ግሸን ደብረ ከርቤ የሚገኘው መስቀል።

ዛሬም የመስቀል በዓልን ምክንያት በማድረግ ስለ ዓባይ ወንዝ ሊመክሩ የመጡትና በፓትርያርክ አቡነ ታድሮስ የሚመሩት የግብፅ ሃይማኖታዊ ዲፕሎማቶች እነሆ መስቀል አደባባይ በዓሉን አከበሩ። ይህን ላስተዋለው ልዩ ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ ነው።

ለማንኛውም አመጣጣቸው ምንም ዓይነት ምክንያት ቢኖረው ግን በደማቁ የደመራ በዓል ላይ መገኘታቸው በራሱ መልካም ነው።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

//////////////

የመስቀሉ ተመሳቃዮች ምሥጢር=ፍቅር

...

"የመስቀል አሠራር ከታች ወደ ላይ ወይም ከላይ ወደ ታች እና ከጎን ወደ ጎን (ከግራ ወደ ቀኝ ወይም ከቀኝ ወደ ግራ) በሚያመለክቱ ሁለት እንጨቶች (ብረቶች) የተመሳቀለ መሆኑ ምሥጢር አለው። ከላይ ወደ ታች ወይም ከታች ወደ ላይ የሚያመለክተው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን የፍቅር ግንኙነት ሲያመለክት ከጎን ወደ ጎን የሚያመለክተው ደግሞ በሰውና በሰው መካከል ያለውን የፍቅር ትስስር (ፍቅረ ቢጽ - የወንድማማች መዋደድን) ያሳያል"።

(...ብፁዕ ወቅዱስ ፖፕ ታዋድሮስ ትላንት በደመራ በዓል (መስቀል አደባባይ) ላይ ከተናገሩት የያዝኩት ማስታወሻ።)

...

እነዚህ ሁለቱ ሕጎች ማለትም እግዚአብሔርን እና ሰውን መውደድ/ማፍቀር የሕግጋት ሁሉ ፍፃሜዎች መሆናቸውን ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 22 ከቁጥር 35-40 ላይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮናል።

አንድ ሕግ አዋቂ ኢየሱስን ሊፈትነው...

"መምህር ሆይ፥ ከሕግ ማናቸይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት?" ብሎ ጠየቀው።

ኢየሱስም እንዲህ አለው።

"ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ።

ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።

ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም። ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።

በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት... ነቢያትም ተሰቅለዋል።"

እንግዲህ ልብ እንበል። መስቀል የፍቅር ምልክት ነው። የሕግም ሁሉ ፍፃሜ ፍቅር ነው። ይኸውም የተገለፀው በመስቀል ነው።

...

(መላኩ አላምረው በድሬቲዩብ)

Sep 29 at 3:21am · Public · in Timeline Photos

View Full Size · Send as Message ·

Report

Tigist Asefa and 3,550 others like this.

Write a comment...

Comment

Mention Friends

Mulne Ze Mmgw

ምናለ ነገሩን በበጎ ብንመለከተው?የግብፅና የኢትዮጵያ ግንኙነት ከጥንት የጀመረ ነው። ክፉና ደጉን በዘመን ጅረት አንተ ትብስ እኔ ተባብለው አንዴ በፀብ አንዴም በፍቅር እከክልኝ ልከክልህ እየተባባሉ አባይን ይብላኝ ለምቀኛ በማለት በአንድ ጣሳ፣በአንድ ትንፋሽ እየተጎነጩ ሲኖሩ ረጅም ዘመናት አስቆጥረዋል።በተለይ በ 15 ኛውናበ 16 ኛው መቶ ክ/ ዘመን የነበሩት ደጎቹ ነገስታት በአፄ ዳዊትና ልጃቸው ንጉስ ዘርአ ያእቆብ ዘመን ግንኙነታቸው የጠበቀ ነበር። ታድያ ዛሬ እንደ መንግስታት ፍላጎት ብቻ ሳይሆን እንደ እግዚአብሄር መልካም ፈቃድ ቢሆንስ ቀረቤታቸው? ወደድንም ጠላን አምላክ ግብፅን ወዶአታል ፣ተሰዶባታል።በብዙ ቀጥቶአታል፣ደግሞም ይምራታል። ት.ኢሳይያስ 19,22 እግዚአብሄር ግብፅን ይመታታል፣ይመታታል ይፈውሳትማል፣ወደ እግዚአብሄር ይመለሳሉ፣እርሱም ይለመነቸዋል ይፈውሳቸውማል።ይላል ቃሉ።እንግዲ ሀገራችን ለ 42 አመት አንፃራዊ ሰላም እንደሚኖራት ተነግሮአል ።18 አመት ያክል የሰላም ግዜ ቀርቶናል።እስከዚያው በሰላም በፍቅርና በፀሎት

መኖር ነው ያለብን። በስተመጨረሻም ይህን ልበል - አሁንም ያእቆብሆይ የፈጠረህ እስራኤልም ሆይ የሰራህ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል እኔ የእስራኤል ቅዱስ መድሀኒትህ ነኝ፣ግብፅን ለአንተ ቤዛ አድርጌ ኢትዮጵያንና ሳባንም ለአንተ ፈንታ ሰጥቻለሁ። ት. ኢሳይያስ 43, 3 ።ቸር ይግጠመን።

Like · 58 · Reply · Report · Sep 29 at 4:29am

7 replies

Araya Haile

ኢትዮጵያ የድንግል ማርያም ርስት የኦርተደክስ ክርስትያን ደሴት ስለሆነች ይህን ያክል መጎብኘት ቀለል ኣደለም።

Like · 64 · Reply · Report · Sep 29 at 3:42am

29 replies

Temesgen Ze Nebe

ለአለማዊ ነገሮች እንደ ሰውኛ ብዙ ማለት ይቻላል በመንፈሳዊ አካሔድ ግን አንዳችም ነገር ከአምላክ ፈቃድ ውጭ አልተከናወነም የሳቸው መምጣትመቢሆን

Like · 18 · Reply · Report · Sep 29 at 5:28am

ሄኖክ የኖላዊ ጌር ልጅ

ከግብጽ የሚመጣ አባትም ሆነ ታሪክ አገርንም ቤተክርስቲያንንም አይጠቅምም አጥፊወቻችን ናቸው በበዓል ሰበብ አደንቁረውን ስራ እንዳንሰራ አደርገው የሀይማኖት ቅኝ ገዝተውናል ከዚህ በዋላ ይብቃቸው አቡነ መቃርስ ያሉ የግብጽ መነኮሳት ይማራሉ ያርሳሉ ከብት ያደልባሉ

ሀብታሞች ናቸው የእኛቹ ግን ይለምናሉ ይለምናሉ ይልምናሉ ምርጥ ድሆች ናቸው::

Edited · Like · 14 · Reply · Report · Sep 29 at 8:03am

15 replies

Fikade Derso

በግምት አትቀባጥሩ አስተሳሰባችን ደግሞ posetive መሆን አለበት። እሳቸዉ የመጡት በአሉን ለማክበር እና ሀገራችንን ለመባረክ እንጅ ሌላ ተልእኮ የላቸዉም።

Like · 14 · Reply · Report · Sep 29 at 4:41am

5 replies

Aklilu Fantahun

"ኢትዮጵያ እጆቻን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች"

Like · 15 · Reply · Report · Sep 29 at 4:24am

Yoni Amsal

እና አሁንም ሌላ ግማደ መስቀል ሰተውን አባይን ያስለቅቁት ይሆን??

Like · 12 · Reply · Report · Sep 29 at 3:58am

11 replies

Ashu Habesha Ze-Ethiopia

የመስቀል ደመራ በዓል የአለም ቅርስ ነው

Like · 10 · Reply · Report · Sep 29 at 3:33am

Kibrom Asteraw

40 መንፈሳዊ ጉንጭነታችን ሌላ የሀገራችን ጥቅም እና ክብር ሌላ! ምንም ይዘብን ቢመጡ በሀገራችን ድርድር የለም! በኣንድ እጅ መፃሐፍ ቁዱስ ይዞ በኣንድ ሽጉጥ ይዞ ኣውረፓውያን ኣስተማሩን።

Like · 9 · Reply · Report · Sep 29 at 3:30am

1 reply

Bemnte Lamnre

ሰላም ያለው ኮመንት ማንበብ ነው የናፈቀኝ ውይ እስኪ ከዘር ከሐይማኖት የነፃ ትውልድ ያድርገን አቦ

ኦርቶዶክስ መልስ አላት/Orthodox Have An Answer

5/ † የመስቀል ዓይነቶች †

1. ዕፀ መስቀል፦ የጌታችን መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ

2. የመዖር መስቀል፦ በቅዳሴ ጊዜ ሠራዒ ዲያቆን የሚይዘው

3. ዕርፊ መስቀል፦ ዲያቆናት በቁርባን ጊዜ ለምዕመናን ክቡር ደሙን የሚያቀርቡት

4. የእጅ መስቀል፦ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳትና ካህናት የሚይዙት ምዕመን የሚባትኩት የሚያሳልሙበት

5. የእንገት መስቀል፡- ምዕመን በማተባቸው አስረው በእንገታቸው በሚደረግ ለጌታችን ያላቸውን ፍቅር የሚገልጡበት

6. ቀርነ በግዕ መስቀል፡- በመጽሐፈ ድጉሰት ላይ የሚታይ የበግ ቀንድ የመሰለ ቅርጽ ያለው ቆለፍ ያለ መስቀል በቤተክርስቲያን ብዙ ዓይነት የመስቀል ማዘጋጃ /መሥሪያ ቁስ/ አለ እርሱም የእንጨር፣ የወርቅ፣ የነሐስ፣ የብረት ናቸው።

† የእንጨት መስቀል፡- ጌታችን የተሰቀለበት ስለሆነ

† የወርቅ መስቀል፡- ወርቅ ንጹሕ እንደሆነ ጌታችንም ንጽሐ ባህርይ አምላክ ስለሆነ

† የብር መስቀል፡- የአስቆሮቱ ይሁዳ በብር ሠላሳ መሸጡን ለማስታወስ፣

† የነሐስ መስቀል፡- የብሩህነቱ

† የመዳብ መስቀል፡- የአማናዊ ደሙ

† የብረት መስቀል፡- የተቸነከረበትና ጎኑ የተወጋበት

የመስቀል ዓይነቶች /ቅርጻቸው/

1. ቀራንዮ ሐዋርያ መስቀል
2. ቀርነ በግዕ መስቀል
3. አርዌ ብርት መስቀል
4. ልሳነ ከለባት መስቀል
5. ትእምርተ ንትፈት መስቀል
6. ሐረገወይን መስቀል
7. ዕፀ ሳቤቅ መስቀል
8. ዕፀ ሳርናይ መስቀል

9. ጽጌ ደንጉላ መስቀል

10. ዓመደ ዓለም መስቀል

11. ትእምርተ ከዋክብት መስቀል

12. እሳት ገቡእ መስቀል

13. ለንጊኖስ መስቀል

"በስመ ሥላሴ"

6/ መስቀል በብሉይና በሐዲስ ኪዳን|

መስቀል ማለት የፍቅር ፍፃሜ የሰላም ማረጋገጫ የአንድነት ዙፋን እንዲሁም መከራ ማለት ነው። ይኸውም ክርስቶስ ስለሰው ልጆች ፍቅር የተቀበለው መከራ ክርስቲያኖች ስለክርስቶስ ፍቅር የተቀበለው መከራና ክርስቶስ የተሰቀለበት የክብር ዙፋን መስቀል ነው። መስቀል በዘመነ ኦሪትና በዘመነ ሐዲስ የነበረው ትርጉም ይለያያል ይህም ለማየት ይረዳን ዘንድ በሁለቱም ዘመን የነበረውን ምሥጢር እንመልከት።

መስቀል በብሉይ ኪዳን

ከጌታ ልደት በፊት መስቀል ከፍተኛ ጥፋት ያጠፉ ሰዎች መቀጫ ነበር። በተለይም ሰውን መስቀል የተጀመረው በፋርስ /ኢራን/ ነው። በዘመኑ የነበረው ታሪክ ፀሐፊ ግሮዶቱስ የተባለ ሊቅ ዳርዮስ 322-486 ቅ/ል/ክ 3 ሺህ ነዋሪዎች በስቅላት መቅጣቱን ጽፏል። የመሬት አምላክ ነበራቸው

ወንጀለኛ በሀገራችው ሲገኝ ቅጣቱን በመሬት ላይ የተቀበለ እንደሆነ የመሬት አምላካቸው እንዳይረክስ ወንጀለኛውን በሀገራችን ሲገን ቅጣቱን በመሬት ላይ የተቀበለ እንደሆነ የመሬት አምላካቸው እንዳይረክስ ወንጀለኛውን ሁሉ በመስቀል ይሰቅሉት ነበር። ይህ ድርጊት እንደልማድ ሆኖ በሮማ ግዛት ሁሉ የተለመደ ሕግ ሆነ ሲሰሩ የተባለው ሮማዊ መንግሥት ስቅላትን የመጨረሻ ቅጣት በማለት ይጠራዋል። በኦሪት ሥርዓት በመስቀል በስቅላት የሚቀጡ ሁሉ ርጉማን ውጉዛን ነበሩ። በኦሪት ህግ መሠረት ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ኃጢያት ቢሠራ እንዲሞትም ቢፈረድበት በእንጨትም ላይ ብትሰቅለው በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ሬሳው እንዳትረክስ በእግርጥ በዚያው ቀን ቅበረው። ዘጸ 21÷22-23 የሚል ተጽፏል። በእርግጥ እስራኤላውያን ወንጀለኛን ይቀጡት የነበረው በድንጋይ በመውገር ነበር። በስቅላት መቅጣት የጀመሩት ከ 267 ቅ/ል/ክ በኋላ መሆኑ ታውቋል። የሐሰሞናውያን ሥርወ መንግሥት 267-37 ቅ/ል/ክ አይሁድን ሲገዛ ሰዱቃዊው ሊቀ ካህናት ኢያንዮስ 103-76 ቅ/ል/ክ 600 ፈሪሳዊያንን በስቅላት እንዲቀጣ ይታወቃል።

መስቀል በብሉይ ኪዳን ብዙ ምሳሌ አለው። እስራኤል ከባርነት ነፃ ከወጡ በኋላ ወደ ከነዓን በመጓዝ ላይ ሳሉ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ከማጉረምረማቸው የተነሳ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ። ሕዝቡን ነደፈ ተጸጽተው ወደ እግዚአብሔር በተመለሱ ጊዜ የናስ እባቡን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈው ሁሉ ሲያዩት በሕይወት ይኖራሉ

በማለት እግዚአብሔር አዘዘ። የናስ እባቡን እስራኤላውያን ከመጣው መቅሰፍት የመዳን ምክንያት ሆነ።

ይህ ምሳሌ የሐዲስ ኪዳን ትርጉምና ትንቢት ነው። ባልበደለው የናስ እባብ ስለሕዝቡ ኃጢአት ፈንታ ተገብቶ እንደተሰቀለ በኋላ ዘመን በሐዲስ ኪዳን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባህሪው ንፁህ ሲሆን ያለበደሉ ስለ አዳም ልጆች ብሎ መስቀሉ በእስራኤል በደል የመጣው ተናዳፊው መርዛም እባብ ነበር። መድኃኒት እንዲሆን የተሰቀለው የናስ እባብ ግን ንጹሕ ነው። በአዳም ምክንያት የመጣው ሞት ሁሉን ነድፎ የሚጥል መርዛም ነበር ዘፍ.3÷17 ለእኛ ብሎ የተሰቀለልን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክርስቶስ ግን ንጹሕ ባሕርይ ነው የናሱ እባብ በዓላማ ላይ እንደተሰቀለ ጌታችንም በዛ ዘመን የናሱን እባብ የቻሉ አይተው ያልቻሉ ደግሞ ድምጹን ሰምተው እንዲድኑ ጌታችንንም ዕድል ገጥሟቸው መልኩን ተአምራቱን አይተው የኋላ ዘመን ሰዎች ደግሞ በእርሱ አምነው ትምህርቱን ሰምተው ይድናሉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሴ በምድረ በዳ የተሰቀለው የናስ እባብ የርሱ ምሳሌ በመሆን ሲያስተምር ሙሴም በምድረ በዳ የናሱን እባብ እንደ ሰቀለ እንዲሁ በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖራቸው እንጂ እንዳይጠፉ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል። የሐ.3÷4 ሌላው የኖኅ መርከብ የተሠራችበት እንጨት ሙሴ የፈርኦንን መሰግላን /ጠንቋዮች/ ድል ያደረገበት በትር ከአማሌቃውያን ጋር ሲዋጉ ሙሴ እጁን ሲዘረጋ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር።

ዘፀ 17÷8 ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ የመስቀል ምሳሌዎች ናቸው።

መስቀል በሐዲስ ኪዳን፣ መስቀል በሐዲስ ኪዳን በሰውና በእግዚአብሔር መካካል የነበረው የጥል ግድግዳ የተናደበት ተወስዶ ሰላም የተመለሰበት ነው። የመጀመሪያው ሰው አዳም በተድላ ገነት ነግሥና ደስ ብሎት ሕግን አፈረሰ መላው የአዳም ዘር በመጀመሪያ በደል ረክሶ በውርስ የሞት ባለ እዳ ሆነ። ገደብ የለሽ ኃጢአትና ሞት በሰው ልጅ ላይ ሰለሠለጠነ ባሕርይውም ጎሰቆለ። ቆሰለ። ሰው የቀደመ ክብሩና ጸጋው ይመለስ ዘንድ የቆሰለና የጎሰቆለ ባሕርይው ሊታደስ የረከሰ ሰውነቱ የሚያነፃ ያስፈልገው ነበር። በበደሉ ያጣውን ሰላም ነፃነትና ድኅነት ሊያነኝ በመከራ ግዘት እየተንገላታ በናፍቆት ይዋትት ነበር።

እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ሰንቆ ቆጥሮ የመከራውን እንጀራ በእንባው እየወራረዱ ዕለቱን በተስፋ ሲጠባበቅ ኖረ። ቃሉ የማይታበል አምላክ የቀጠሮው ሰዓት በደረሰ ጊዜ በማይመረመርና በማይነገር ጥበቡ የዓለም የድኅነት ምክንያት አድርጎ ካዘጋጀት ንጽሕት ዘር ከቅድስተ ቅዱሳን ከንጽሕተ ንጹሐን ድንግል ማርያም በምሥጢረ ተዋሕዶ ተወልዶ በሥጋ ተገለጠ። ገላ 4÷9 1ጴጥ 6÷20

ከባህርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ ከሰማያት ወርዶ በመስቀል ተሰቅሎ ንጽሕ መስዋዕት ሆነ። በነቢዩ ኢሳይያስ በእውነት ደዌአችንን ተቀበለ ሕማማችንን ተሸክሚል። ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችን ደቀቀ የድህንነታችን ተግሳጽ በእርሱ ስለኛ በመስጠት መድኃኒት ይሆነን ዘንድ በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቀለ ሞተልን ኃጢአታችንን

ስለማስተሰረይ ለእኛ የሚገባ ሞትን ያጠፋ ዘንድ ሞተ ሃይማኖት አበው ዘአትናቴዎስ 23÷10 የተስፋው ቃል እውን መሆን የትንቢቱ መፈጸም ፍፃሜ ጌታችን በዚያ በቀራንዮ አምባ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቅሎ ተፈፀመ አለ አንድም በእርግማን ለበደለኞች መቀጫ የነበረው መስቀል በክርስቶስ መቀጫ የነበረው መስቀል በክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ ክቡር ደም ተቀደሰ የበደለኞች መቀጫነቱ ቀርቶ ቅዱሳን ሰዎች የሚሰቀሉበትና የሚቀደስበት የድል አክሊል የሚቀዳጁበት ቅዱስ መስቀል ሆነ። የሐ. 19÷30

ስለዚህ የሐድስ ኪዳን መስቀል

ሰውና እግዚአብሔር ዕርቅ የተፈጸመበት ዙፋን ‹‹በመስቀሉ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀናል ሰላምንም አግኝተናል። ቆላ 1÷20››

መስቀል የመላእክት የስብከታቸው መሠረት ነው። ቅዱሳን መላእክት የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት ባበሰሩት ጊዜ ሁሉ ‹‹የተሰቀለው ኢየሱስ›› ይሉ ነበር ማቴ 28÷5

መስቀል የሐዋርያት የስብከታቸው ማዕከል ነው። ሐዋርያትም ለስብከታቸው ‹‹እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን›› የሚል ነው። 1ኛ ቆሮ 1÷23

መስቀል መመኪያችን ነው። ‹‹ከክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ›› ገላ 6÷9

መስቀል ኃይላችን ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። 1ኛ ቆሮ 1÷18››

ዕፀ መስቀል ሰማያዊና ምድራዊ ዙፋን ነው። ሰማያዊ አምላክ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋውን የቆረሰበት ደሙን ያፈሰሰበት ገነት የተከፈተበት አዳምን ከሞት ዕዳ ያዳነበት ነፍስ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ትገባ ዘንድ መንገዱን የከፈተበት ዙፋን ነው ዮሐ. 14÷21

መስቀል ምስክራችን ነው። መስቀል ለክርስቲያኖች ምልክት /ግርማ/ ነው። ‹‹ለሚፈሩህም ምልክትን ሰጠኃቸው›› መዝ 59÷4

ከመስቀሉ በረከት ይክፈለን አሜን !!!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር

7/ መስቀል ምንድነው ?

መስቀል በቤተ ክርስቲያናችን ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል ም/ቱም ጌታችን እርግማናችንንና ሀጥያታችንን ያስወገደልን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ስለሆነ ነው ።ጌታችንም ለመስቀል ታላቅ ትኩረት ሰጥቷል። ይህንንም ሲገልፅ፦ "መስቀሉን የማይዝ በኃላዬም የማይከተለኝ የእኔ ሊሆን አይገባውም" /ማቴ

10:38/ እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር እራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" ።ማር 8:34 አለ። ከወጣቱ ሀብታም ጋር ባደረገው ንግግርም መስቀሉን ተሸክመህ ና ተከተለኝ ።ማር 10:21 በማለት የመስቀሉን ታላቅነት አስረዳ ። እንዳውም "ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኃላዬ የማይመጣ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም" አለ።/ሉቃ 14:27/ መስቀል የመላዕክትና የሀዋሪያት የአገልግሎታቸው መሰረት ነው። የጌታችንን መነሳት ለሴቶቹ ያበሰረው መልአክ"እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደትሹ አውቃለሁና.../ማቴ 28:5-6/አለ። ጌታ የተነሳ ቢሆንም መልአኩ ጌታችንን "የተሰቀለው" ብሎ ጠራው ።የተሰቀለው የሚለውን ስም ጌታችን ከተነሳ ቡሃላ እንኳ ተጠርቶበታል።ሀዋሪያትም በስብከታቸው ለመስቀሉ ትኩረት ሰጥተዋል።ቅዱስ ጴጥሮስ አይሁድን ሲሰብክ "እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስ .../ሐዋ 2:36/አለ።ቅዱስ ጳዉሎስም የጌታ መስቀል እንደሞኝነት ቢቆጠርም እኛ ግን"የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን ብሏል።1 ቆሮ 1:23 እንዳውም ጳውሎስ" ከጌታ ከኢየሱስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከኔ ይራቅ"/ገላ 6:14/ በማለት መስቀል መመኪያው መሆኑን ተናግሯል።እኛም በማማተብ ፣መስቀልን በአንገታችን በማሰር ፣በጌጣጌጦቻችን በመቅረፅ ፣በልብሳችንና በእምነት ቦታዎቻችን ላይ ከፍ አድርገን በመስቀል ለእኛ የተሰቀለው (የክርስቶስ) መሆናችንን በግልፅ እናውጃለን።ስለ ክርስቶስ መስቀል በሰው ፊት አናፍርም። ነገር ግን በእርሱ እንከብራለን፣ እርሱን የሙጥኝ እንላለን ስለዚህ እኛ በቃላችን ሳንናገር ሰዎች መስቀላችንን በማየት ብቻ ስለ እምነታችን የተሰበኩ ይሆናሉ።ስናማትብ እጃችንን ከላይ ወደ ታች ከግራ ወደ ቀኝ በመውሰድ

እናማትባለን። በዚህም ክርስቶስ ከሰማያት መውረዱን ሰዎችን ከግራ ወደ ቀኝ ፣ ከጨለማ ወደ ብርሀን ማሻገሩን እናስታዉሳለን።

8/ አንደኛው መስቀል

Please Read in PDF

በህይወት የማይስማሙ በሞት ይጣመራሉ።በክርስቶስ የሚካካዱ ለሰይጣን ሊገዙ በአንድ ያብራሉ።በምድረ በዳ ሰው ለመግደል ፣የሰው ንብረት ለመዝረፍ የሚስማሙ ቀራንዮ ላይ መለያየት ይጀምራሉ።በወንበዴነት የሚስማሙ የክርስቶስ በመባል ግን ይለያያሉ።በታጢአት የሚጣበቁ በጽድቅ ይነጣጠላሉ።አይለያዩም የተባሉ የታጢአት ባልንጀሮች ክርስቶስን በማመንና ባለማመን እስከማይተዋወቁ ድረስ ይከፋፋሉ።

ቀራንዮ ድካማችን አይጸድቅባትም።ድካማችንን በመስቀሉ ጠርቀን፤ ክፉ ምኞት አንቂ አሮጌውን ሰው ሰቅለን አዲሱን ሰው የምንለብስባት፤ ለአንዱ ጌታ መገዛታችንን በግልጥ ውሳኔያችንን የምንገልጥባት ስፍራ ናት።ቀራንዮ ላይ ብዙ አማራጮች ብዙ መንገዶች የሉም።ብዙ የመዳን ቀመሮች ፣ከሁለት የዘለሉ የድህነት ስሌቶችም የሉም።ቀራንዮ ላይ ሁለት መንገዶች ብቻ አሉ።አንዱ የሲዖል አንዱ ወደእግዚአብሔር ገነት።ሦስተኛ ምርጫ የለም።ብንፈልግም ፈጽሞ ማግኘት አይሆንልንም።

አንደኛው መስቀል ላይ ዘመኑን በውንብድና የጨረሰ፣ለክፋቱ ዳርቻ ሳያበጅ

ከነክፋቱ የተገኘ ለጥፋቱም ተካካይ ፍርድ በሀጉ የተሰጠው አንድ ደካማ ሰው አለ።አለም ሞት ብትፈርድበትም ክርስቶስ ግን ዛሬም የርህራሔ እጁን ዘርግቶ እስከማታ "ልጄ ሆይ አትሙትብኝ እኔ ልሙትልህ!!!" እያለ ይለምነዋል። ከእግዚአብሔር መዝገብ ፍርድ እስካልወጣ አለም ሞት ፈርዳ ለፍርዱ መፈጸም ብትቻኮልም የህይወት ጥላችንን ማንም አያጥፈውም። አለም ሞት ብትደግስም ክርስቶስ ግን የማይደክም የማዳን እጅ ዘርግቶለታል።

ይህ ሰው ግን የተዘረጋውን እጅ የማያይ ፣ሞቶ የሚያድን አፍቃሪ ጌታውን ማየት የተሳነው ሐኬተኛ ባርያ ነው።የተከደነለትን ነውሩን ፣የበዛ ኃጢአቱን ሳይሆን በሌላው የሚሳለቅ ፌዘኛ ነው።የገረጣ ፊት ፣የቆሰለ ሰውነት፣ የተጋጋጠ አጥንት እያየ ሌላውን ይከሳል።ቁስል አይቶ የማይደነግጥ ፣የደማና የተከሰከሰ አጥንት ተመልክቶ የማይሰቀቅ ስብዕና ምን አይነት ስብዕና ነው?!

ከሳሽ ሁል ጊዜ ዕውር ነው።ነጩን ማጥቆር እንጂ ነጩን ነጭ ነው ማለት አይችልም።የከሳሽ መንፈስ ያለባቸው ሰዎች የገዛ እናታቸው ነውር እንኳ ሲያወሩ ምንም ሐፍረት አይሳልባቸውም።ይህ ወንበዴ የጌታ ኢየሱስን ደምና ቁስል አይቶ አልደነገጠም።ይልቁን ይሳደብና ይሳለቅ ነበር።ከሳሽነት በሰው ስቃይና ሰቆቃ እንደመዝናናት የሚያስቆጥር ክፉ አጋንንታዊ መንፈስ ነው።

የዛሬው ዘመን ከቀደሙት ዘመናት ይልቅ በፖለቲካው፣በማህበረሰቡ፣በሥራ ገበታው፣ከሁሉ ከሁሉ "ኃይማኖተኞች በሚባሉት" መካከል ለቁጥር የሚያሰለቹ ከሳሾች የፈሉበት ዘመን ነው።መጽሐፍ ቅዱስ ጨብጠው ምለው ሰውን በሐሰት የሚከሱና በሰው ላይ በሐሰት የሚመሰክሩ "ታላላቅ"

የተባሉና ለምድር የከበዱ በሰው ፊት የተፈሩ አባቶችንና "ወንጌል" የጨበጡ "ሰባክያንን" አውቃለሁ።ከሳሽነት እንዴት ጎጆ እንደሰራብን ሳስብ የሚቀርበው የሽንገላ አምልኮ የቁስል ያህል ይጠዘጥዘኛል!!!! አምላካችን ምህረትን እንጂ መች መስዋዕትን መረጠ!!!!!??

ባልንጀራችንን ከሰን በገዛ እጃችን የሰማዩን በር በራሳችን ዘግተን "እንደምህረትህ እንጂ እንደበደላችን አይደለም" የሚለው የመዘባበቻ ጸሎት አያዋጣንም።እውነታው አንድ ነው፤ እግዚአብሔር የባልንጀራውን ድካም የሚያወራውን ከንፈር ይጠየፋል።

አዎ! ያ ወንበዴ የሌላውን ድካም እያወራ ወደመቃብር ወረደ።በብዙ ትለምነው የነበረችውን የጌታን የምህረት እጅ ተጠየፈ።ከሳሽ የሰውን እንጂ የራሱን ኃጢአት ማየት ስለማይቻለው የሰውን እንዳየ ፣ የሰውን እንዳወራ የተሰጠውን ዕድል ሳይጠቀም ሞቶ ተቀበረ።የሰውን ነውር የሚገልጡ የራሳቸውን ነውር ሳይከድኑ ወደመቃብር ይወርዳሉ።በሰው ሲፈርድ እርሱ በሚብስ ፍርድ ተወገደ።

እኛ ኃጢአታችንን ብንናዘው ዲያብሎስ ፈንታ ያጣል።እኛ ግን የራሳችንን ሸሽገን የሌላውን ነውር ብናወራ ዲያብሎስ አንዳች ሳይስት ያለመታከት ያወራዋል።እኛ ብዙውን ኃጢአት ነው ይቅር የተባልነው። ታዲያ ትንሹን የባልንጀራችንን ኃጢአት እንገልጥ ፣እናወራ ዘንድ ማን ሾመን? መስቀላችንን ተሸክመን በዝምታ ካልታገስነው ተቸንክረን እንኳ ክብር የለንም።መከራውንም ተቀብለን ዋጋና ሽልማት የለንም።ያ ወንበዴ በመስቀል ተሰቅሏል ግን የመስቀሉን ቃል ክብር አይለብስም።ደምቷል ፣አንብቷል እንባውን ግን ከአይኑ የሚያብስ የለም።ከሳሽነት ዘላለማዊውን ክብራችንን

እንኳ እንዳናይ ዓይናችንን በጨለማ ይጋርደዋል።

ወዳጆቼ! ለምን መከራውን ብቻ ትቀበላላችሁ? ለምንስ እየተሰቀላችሁ እየደማችሁ ዋጋችሁን ታጣላችሁ? በክርስቶስ ርህራሄ ልለምናችሁ ... በመስቀላችሁ ላይ ዝም በሉና ታገሱ!!! የቁስላችሁን ጥዝጣዜ ሳይሆን የተተወላችሁን ኃጢአትና ያበዛላችሁን ይቅርታ እያሰባችሁ ስለባልንጀራችሁ ኃጢአት አንቡ ፤አልቅሱ እንጂ በአንዳች ማንንም አትክሰሱ!!!

ጌታ ክብር ካለበት፣ስለወንጌሉ መዋረድን ከማይታገስ፤ ከከሳሽነት መስቀል ያውርደን።አሜን።

መጽሐፍ ሳነብ እንዲህ የሚል ታሪክ አገኘሁ ላውጋችሁ።

መስቀል

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

9/ ከጌታችንና ከአምላካችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በፊት መስቀል የመቅጫ መሣሪያ ነበር። ሰውን በመስቀል ላይ መቅጣት የተጀመረውም በፋርስ ነው። ፋርስ የዛሬዋ ኢራን ናት። የፋርስ ሰዎች “አርሙዝድ” የተባለ “የመሬት አምላክ” ያመልኩ ነበር። ከዚህም የተነሣ “ወንጀለኛው ቅጣቱን በመሬት ላይ የተቀበለ እንደሆነ አምላካችን ይረክሳል፤” ብለው ስለሚያምኑ ወንጀለኛውን ከመሬት ከፍ አድርገው

በመስቀል ላይ ይቀጡት ነበር። ይህም ቅጣት ቀስ በቀስ በሮማ ግዛት ሁሉ የተለመደ ሕግ ሆነ። ከዚህም ሌላ በኦሪቱ ሥርዓት ቅጣታቸውን በመስቀል ላይ የሚቀበሉ ሰዎች ርጉማንና ውጉዛን ነበሩ። ይህንንም እግዚአብሔር ለሙሴ “ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ኃጢአት ቢሠራ እንዲሞትም ቢፈረድበት፥ በእንጨትም ላይ ብትሰቅለው፥ በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ሬሳው በእንጨት ላይ አይደር፤” ሲል ነግሮታል። ዘዳ.21፥22-23። እዚህ ላይ “በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሚሞት የተረገመ ከሆነ፥ ለምን ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ?” እንል ይሆናል። ይህንንም እንደሚከተለው እናያለን።

“ለምን በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ?”

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶልናል፥ ክቡር ደሙን አፍስሶልናል፥ ክብርት ነፍሱንም በፈቃዱ አሳልፎ ሰጥቶልናል። ይህንንም ያደረገው በቤዛነቱ እኛን ከእርግማን ሊዋጀን ነው። ምክንያቱም የሰው ልጆች በጠቅላላ በመርገመ ሥጋ በመርገመ ነፍስ ተይዘን ነበርና። በመሆኑም በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነም፥ በሞተ ሥጋ ላይም ሞተ ነፍስ ተፈርዶብን ከእርግማን በታች ወድቀን ነበር። ይሁን እንጂ ፈጣሪያችን “እንደ ወጡ ሳይመለሱ፥ እንደወደቁ ሳይነሱ ይቅሩ፤” ሳይል እኛን ለመፈለግ ከሰማየ ሰማያት ወረደ። ማቴ.18፥12-14። በመንፈስ ቅዱስ ግብር በማኅፀነ ድንግል ማርያም ተፀነሰ። ሉቃ.1፥35። ከእመቤታችንም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ ነስቶ በቤተልሔም በከብቶች በረት ተወለደ። ሉቃ.2፥7። በተዋህዶ ሰው አምላክ፥ አምላክ ሰው ሆነ። ማቴ.16፥13፣ 1ኛ ዮሐ.1፥1-2፤

5፥20። ቀስ በቀስም አደገ። ሉቃ.2፥40። ሠላሳ ዓመት በሞላውም ጊዜ በፈለገ ዮርዳኖስ በዕደ ዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሄዶ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾመ። ማቴ.3፥13-17፣ ሉቃ.3፥21-23፣ ማቴ.4፥2። ከዚያም አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ሰባ ሁለቱን አርድዕትና ሠላሳ ስድስቱን ቅዱሳት አንስት መረጠ። የሐዋ.1፥15። አዲስ ሕግ ወንጌልንም ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተማረ። በመጨረሻም ሰለእኛ እርግማን /ኃጢአት/ ተላልፎ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ። ማር.15፥23-37። የሞተውም በፈቃዱ ነው። ዮሐ.10፥11፤ 15፥13። በዚህም የዕለት ፅንስ ሆኖ በእመቤታችን ማኅፀን ጀምሮት የነበረውን የማዳን ሥራ በመስቀል ላይ ፈጸመው። ዮሐ.19፥30።

እንግዲህ ጌታችን ወደዚህ ዓለም መጥቶ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ የሞተው ከላይ እንደተጠቀሰው ስለ እኛ እርግማን ተላልፎ ነው። እርሱ በመስቀል ላይ እርግማናችንን /ኃጢአታችንን/ ሰለተሸከመልንም እኛ ከእርግማን /ከመርገመ ሥጋ፥ ከመርገመ ነፍስ/ ነፃ ሆነናል። ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ “በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፥ ሕመማችንንም ተሸክሟልና ... እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለበደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣፅ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።” ሲል አስቀድሞ የተናገረው ለዚህ ነው። ኢሳ.53፥4-5። ቅዱስ ጳውሎስም ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ “በእንጨት የሚሰቀል ሁል የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና፥ ክርስቶስ ስለ እርግማን ሆኖ /ስለ እኛ ኃጢአት ተላልፎ በመስቀል/ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤” ብሏል። ገላ.3፥13። በቆሮንቶስ መልእክቱም “የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን እኛን ጻድቃን ያሰኘን ዘንድ

ስለ እኛ ኃጢአት ተላልፎ ራሱን ኃጥእ አሰኝቷልና፤" ብሏል። 2ኛ ቆሮ.5፥21። ከዚህም ሌላ ለፊሊጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ "ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ፤" ብሏል። ፊል.2፥7-8። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በበኩሉ "እርሱ ኃጢአት አላደረገም፥ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፥ ኃጢአታችንን /እርግማናችንን/ በእንጨት /በመስቀል/ ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ፤" ብሏል። 1ኛ ጴጥ.2፥22-24። በመሆኑም በመስቀል ላይ በተፈጸመው ቤዛነት ብዙ ነገር አግኝተናል።

1ኛ. ሕይወትን አግኝተናል፤

በኃጢአት ምክንያት ሞት ገዝቶን ሞት ነግሦብን ነበር። ኃጢአት በዘር እየተላለፈም ሁላችንም በአዳም ኃጢአት ምክንያት እንሞት ነበር። በመሆኑም ሞት ከአዳም እስከ ሙሴ /እስከ ክርስቶስ/ ድረስ ነገሠ። ሮሜ.5፥12-14። ከክርስቶስ በኋላ ግን በክርስቶስ ቤዛነት ሞት ስለተሻረ አጥተነው የነበረውን ሕይወት አግኝተናል። ለዚህም ነው "ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና፤" የተባለው። 1ኛ ቆሮ.15፥22። በተጨማሪም "እኛ ሁላችን ደግሞ፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበር እንደሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር /በክርስቶስ ቤዛነት/ ሕይወትን ሰጠን።" ተብሏል። ኤፌ.2፥3-5። ምክንያቱም ጌታችን

በሞቱ ሞትን ሽሯልና። 2ኛ. ጢሞ.1፥10።

2ኛ. የሕይወትን ምግብ አግኝተናልና፤

ኃጢአት ወደ ዓለም ገብቶ ሞትን ያመጣብን በመብል ምክንያት ነው። ዘፍ.3፥1-24። ምክንያቱም አዳምና ሔዋን የዕፀ በለስን ፍሬ በልተው ጐትተው ያመጡት ሞትን ነውና። ኢዮርብአምን እንዲገሥጽ ተልኮ የነበረውም የይሁዳ ሰው አትብላ የተባለውን በመብላቱ ያተረፈው ሞትን ነው። 1ኛ ነገ.13፥20-25። እስራኤል ዘሥጋም በምድረ በዳ የተመገቡት መና ከሞት አላዳናቸውም። ዮሐ.6፥49። ስለዚህ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ሥጋውን የሕይወት እንጀራ አድርጎ በመስቀል ላይ ሰጠን። ይህንንም “እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ /የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስን/ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤” ሲል አረጋግጦልናል። ዮሐ.6፥53-54። በመሆኑም ዕለት ዕለት በቤተክርስቲያን የሚሠዋውና በሃይማኖት የምንቀበለው ቅዱስ ቁርባን አማናዊ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና አማናዊ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው። ምክንያቱም ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆናልና። ማቴ.26፥27-29። ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ሳይገባው ይህንን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና፤” ያለው። 1ኛ ቆሮ.11፥27-30።

3 ኛ. ሰላምን አግኝተናል፤

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ “ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም፤” ብሎ እንደተናገረ ፍጹም የሆነውን ሰላም የሰጠን በመስቀል ላይ ነው። ይህንንም፦ ሞትን በኃይሉ ድል አድርጎ በተነሣ ጊዜ “ሰላም ለእናንተ ይሁን፤” በማለት ለደቀ መዛሙርቱ አረጋግጦላቸዋል። ዮሐ.14፥27፤ 20፥19፣26። ይህንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና፤” በማለት የቆላስይስን ሰዎች አስተምሯል። ቆላ.1፥19-20። የኤፌሶንን ሰዎችም “አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል። እርሱ ሰላማችን ነውና /ሰላማችን የተገኘው በእርሱ ቤዛነት ነውና/፤” ብሏቸዋል። ኤፌ.2፥13።

4 ኛ. አዲስ ሰው ሆነናል፤

በመርገመ ሥጋ በመርገመ ነፍስ አርጅቶ የነበረው ሰውነታችን አዲስ የሆነው በመስቀል ላይ በተፈጸመው ቤዛነት ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን /ሰውነታችን/ ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን።” ያለው ሮሜ.6፥6። ዳግመኛም በቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ “ስለዚህ ማንም ቢሆን በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል፤” ብሏል። 2 ኛ ቆሮ.5፥17። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው፦ ጌታችን እኛን በቤዛነቱ አዲስ አድርጎናል፥ አዲስ

ሕግ ወንጌልንም ሰጥቶናል፥ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር መንግሥት ሰማያትንም አዘጋጅቶልናል። ማር.1፥15፣ 2ኛ ጴጥ.3፥13፣ ራእ.21፥1።

5ኛ. ታርቀናል፤

በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልተን እንኖር ነበር። ይሁን እንጂ እኛ በበደልን እርሱ ክሶ በቤዛነቱ መልሶ ታርቆናል። ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤ ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን፤” ሲል ገልጦታል። ሮሜ.5፥10-11። በተጨማሪም “በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና፤” ብሏል። ቆላ.1፥20። በኤፌሶን መልእክቱም “ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛት ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድ አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፥ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር /ከራሱ/ ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነውና፤” ብሏል። ኤፌ.2፥14-16፣ 2ኛ ቆሮ. 5፥17። በመሆኑም ይህ ሁሉ ነገር የተገኘበት መስቀል፥-

ኃይላችን ነው፤

“የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና፤” 1ኛ ቆሮ.1፥18 ተብሎ እንደተነገረ፥ የእግዚአብሔር

ኃይሉ የተገለጠበት ኃይለ እግዚአብሔር ክርስቶስ የማዳን ሥራውን የፈጸመው በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ነው። በመሆኑም የጌታችን ቅዱስ ሥጋው የተፈተተበትና ክቡር ደሙም የፈሰሰበት መስቀል ስለ ክርስቶስ የከበረ ነው። ለምሳሌ የሆሳዕና አህያ በተጓዘችበት ጐዳና ሁሉ የተነጠፈላትና የተጐዘጐዘላት ስለ ክርስቶስ የከበረች በመሆኗ ነው። ማቴ.21÷8። ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የከበረውና የማዳን ኃይሉም የተገለጠበት መስቀል÷ ወልድ ዋህድ ብለን በኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ አምላክነት ለምናምን ሁሉ ዲያብሎስን የምንቀጠቅጥበት ኃይላችን ነው። ምክንያቱም ጌታችን አስቀድሞ “እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤” ተብሎ እንደተነገረ ዲያብሎስን የቀጠቀጠው በመስቀሉ ነውና። ዘፍ.3÷15። ይህንን በተመለከተ በብሉይ ኪዳን ዘመን የተፈጸመ ምሳሌ አለ። የነቢያት አለቃ ሙሴ እጆቹን በመስቀል አምሳል ግራና ቀኝ ዘርግቶ በሚጸልይበት ጊዜ እስራኤል ኃይል አግኝተው ጠላቶቻቸውን ድል አድርገዋል። እኛም እስራኤል ዘነፍስ የምንባል ምዕመናንም ጠላቶቻችንን አጋንንትን በኃይለ መስቀሉ ድል እናደርጋቸዋለን። የአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አባት ቅዱስ ያዕቆብም እጆቹን ባመሳቀለ ጊዜ ኃይል አግኝቶ በዮሴፍ ልጆች ላይ በረከትን አሳድሯል። ዘፍ.48÷13-20። እኛም በመስቀሉ ኃይል በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን እናገኛለን።

ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ግን ፊት በቀራንዮ ድል የሆነበትን÷ ኋላም እንደ ቀራንዮ ዕለት ዕለት የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ በሚፈተትባት በቤተክርስቲያን ድል የሚሆንበትን መስቀል ከእጃችን ለማስጣል ያልሞከረው ሙከራ የለም። ለልማዱም “እንጨት አይደል? ለምን ትሳለሙታላችሁ? ለምንስ

ትሰግዱለታላችሁ?” እያሰኘ ነው። ይሁን እንጂ በቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኃይል ይታመናል እንጂ “ይህ እንጨት ነው፥ ይህም ጨርቅ ነው፥ ይህ ደግሞ ውሃ ነው፤” ተብሎ አይጠረጠርም። ለምሳሌ፦

- በትረ ሙሴ ኃይለ እግዚአብሔር ተገልጦባት ብዙ ተዓምራት አድርጋለች፤ ከዘፀ.4-14
- የኤልያስ መጐናጸፍያ ኃይለ እግዚአብሔር ተገልጦባት ዮርዳኖስን ከአንዴም ሁለት ጊዜ ለሁለት ከፍላለች፤ 2 ኛ ነገ.2፥7-14
- ፈለገ ዮርዳኖስ ኃይለ እግዚአብሔር ተገልጦባት ንዕማንን ከለምጹ ፈውሳዋለች፤ 2 ኛ ነገ.5፥1-14
- በዘይት /በቀንዲል/ ላይ ኃይለ እግዚአብሔር ተገልጦ በሽተኞች ተፈውሰዋል፤ ማር.6፥13፣ ያዕ.5፥14
- የቤተሳይዳ መጠመቂያ ኃይለ እግዚአብሔር ተገልጦባት ዓይነ ስውሩ ብርሃን አግኝቶባታል፤ ዮሐ.9፥1-12
- ቅዱስ ጳውሎስ የልብሱ ቁራጭ ኃይለ እግዚአብሔር ተገልጦበት ብዙ በሽተኞች ፈውስ አግኝተውባታል፤ ከአጋንንት ቁራኝነትም ተላቀውባታል፤ የሐዋ.19፥11-12
- ቅዱስ ጴጥሮስ ጥላው ኃይለ እግዚአብሔር ተገልጦባት ከመንገድ ዳር የወደቁ በሽተኞች ሁሉ ተፈውሰውባታል። የሐዋ.5፥15። ስለሆነም ስለመስቀሉ ያልሆነ ነገር እየተናገርን ከመስቀሉ ባለቤት ከክርስቶስ እንዳንጣላ መጠንቀቅ አለብን። ምክንያቱም መስቀልን መጥላት የክፉ ትንቢት መፈጸሚያ መሆን ነውና። ይህንንም በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና፤ ብዙ

ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ፥ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ አላለሁ። መጨረሻቸው ጥፋት ነው /ገሃነመ እሳት ነው/፥ ሆዳቸው አምላካቸው ነው /አይጸሙም/፥ ክብራቸው በነውራቸው ነው፥ አሳባቸው ምድራዊ ነው፤" ሲል ተናግሯል። ፊል.3፥18-19።

እንግዲህ ነቢዩ ዳዊት "ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ፥ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው። ወዳጆችህ እንዲድኑ፤" ብሎ አስቀድሞ በትንቢት እንደተናገረ፥ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዲያብሎስ ቀስት /ጦር/ እናመልጥና እንድን ዘንድ በደሙ ቀድሶና አክብሮ የሰጠንን ምልክት መስቀልን አጥብቀን መያዝ አለብን። መዝ.59፥4-5። እንደ ቅዱስ ጳውሎስም "ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት /ዓለም በእኔ ዘንድ ሙት ከሆነበት/ እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት /እኔም በዓለም ዘንድ ሙት ከሆንኩበት/ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።" እያልን በመስቀሉ መመካት አለብን። ገላ.6፥14። መስቀልን በምልክትነቱ ብቻ የሚቀበሉት ሰዎች አሉ፤ ለእኛ ግን መስቀል ኃይላችን፥ መድኃኒታችን፥ የሚያድነን፥ ቤዛችንና የነፍሳችንም መዳኛ ነው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የምናየው በዓለ መስቀልን ለምን እንደምናከብር ነው።

የመስቀልን በዓል ለምን እናከብራለን?

የመስቀል በዓል የሚከበረው መስከረም 17 ቀን ነው። የሚከበርበትም ምክንያት፡- ጌታ በመስቀል ላይ ሙቶ ከተነሣ በኋላ ሕመማን መስቀሉን እየዳሰሱ በመስቀሉ እየታሹ ይፈውሱ ነበር። ይህንን ያዩ አይሁድም በምቀኝነት መስቀሉን ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ ጣሉት። ከብዙ ጊዜም በኋላ ያ ቦታ እንደ ጉብታ ሆነ። ምንም እንኳ ለማውጣት ባይችሉ ክርስቲያኖቹ

ያን ቦታ ያውቁት ነበር። በኋላ ግን በ70 ዓ.ም. በጥጦስ ወረራ ክርስቲያኖቹ ኢየሩሳሌምን ለቀው ስለወጡና የከተማዋም መልክ ስለተለወጠ መስቀሉ የተቀበረበትን ጉብታ ለማወቅ አልተቻለም። በዚህም ምክንያት ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል ተዳፍኖ ቆይቷል። በኋላ ላይ ግን በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የታላቁ ንጉሥ የቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት እሌኒ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ መስቀሉን ለማውጣት ብዙ ደከመች። በመጨረሻም ስሙ ኪርያኮስ የተባለ አረጋዊ በነገራት መሠረት ደመራ አስደምራ ዕጣን አፍስሳበት በእሳት ብትለኩሰው ጢሱ እንደ ቀስተ ደመና መስቀሉ ከተቀበረበት ጉብታ ላይ ተተክሎ በጣት ጠቅሶ የማሳየት ያህል አመልክቷታል። ሳትውል ሳታድር መስከረም 17 ቁፋሮ አስጀምራ መጋቢት 10 መስቀሉን አግኝታለች። ቅዳሴ ቤት /ቤተመቅደስ/ ተሠርቶ የተፈጸመው በመስከረም 17 ነው። እንደወጣም ብዙ ተዓምራትን አድርጓል።

እንግዲህ በሀገራችን በኢትዮጵያ የመስቀልን በዓል ደመራ በመደመርና ችቦ በማብራት÷ ቅዳሴ በመቀደስና ማኅሌት በመቆም የምናከብረው ለዚህ ነው። በዚሁም ላይ ይህን ታላቅ ዕፀ መስቀል በወቅቱ የነበሩ ታላላቅ ነገሥታት የሚያደርጋቸውን ተዓምራት በማየት ለእያንዳንዳቸው ይደርሳቸው ዘንድ ከአራት ክፍል ሲከፍሉት ከአራቱ አንዱ የቀኝ እጁ ያረፈበት ግማድ /ክፋይ/ ብቻ በደብረ ከርቤ ግሸን ማርያም ሲገኝ ሌሎች ሦስቱ ግን የት እንደደረሱ አይታወቅም። ይህም ግማደ መስቀል የመጣው በአፄ ዳዊት በ14 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ የማስቀመጫ መቅደስ ለማሠራት መሬቱ እየተንቀጠቀጠ አልረጋ ብሏቸው በርካታ አድባራትን

ካዳረሱ በኋላም እግዚአብሔር “አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል /መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ አስቀምጥ/” ብሎ ስለነገራቸው ተፈልጋ ግሸን ደብረ ከርቤ በተባለው ቦታ የመስቀል ቅርጽ ስለተገኘች ዛሬም ድረስ በዚሁ ታላቅ ቦታ ይገኛል። በዚህ ታላቅ ጸጋ የተጠቀሙት ብዙዎች ናቸውና እኛንም ከዚህ ረድኤት እንዲከፍለን በዓሉን በአግባቡና በሥርዓት ልናከብረው ያስፈልጋል። መልካም በዓል አክብረን የመስቀሉ ክብርና ጸጋ ረድኤት ይድረሰን። አሜን።

10/ ስለ መስቀል በመጽሐፍ ቅዱስ:-

ማቴ 10:38 ማቴ 16:20

ማር 8:34 ሐዋ 5:30

1 ኛ ቆሮ 1:18 ገላ 3:13

ገላ 6:13 ፊል 2:8

ፊል 3:18

"የምናስተውል ካለን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል"፤

በሚሞት ስጋችሁ ሐጢያት አይንገስ

ብልቶቻችሁን የፅድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ (ሮሜ 6፥12-14)

 ከሴት ጋር አለመገናኘት መልካም ነው ካልተቻለ ዝሙትን ለመከላከል በአንድ ይፅና ከዚህ ውጭ ጉዞ ወደ እሳት ነው (1 ኛ ቆሮ 7፥1)

 ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱ ያፈርሰዋል ቤተ መቅደሱም እናንተው ናችሁ (1 ኛ ቆሮ 3፥17)

 ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእረፍትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸፍኑ (1 ኛ ጢሞ 2፥9)

 የወንድ ልብስ የለበሰች ሴት በአምላክ ዘንድ የተጠላች ናት (ዘዳ 22፥5; ዘፀ 39፥28)

 ፀጉሯን ሳትሸፍን የምትፀልይ ሴት እራሷን ያዋረደች ናት(1 ኛ ቆሮ 11፥5)

 የወይን ጠጅ ከሚጠጣ ጋር አትቀመጥ (ምሳ 23፥20)

 ዘፈን የሰነፎች ዜማ ነው (መክ 7፥5)

 በዛም አጋንንት ይዘፍናሉ (ኢሳ 13፥21)

Orthodox and Bible

11/ መስቀሉ የት ነው ያለው? ክፍል 1

ከዲ/ን ዳንኤል ክብረት

በእምነት ታሪክ ውስጥ የታሪክ፣ የአርኬዎሎጂ እና የቅርስ ጥናት ሰዎችን ያስጨነቁ ሁለት ጥያቄዎች አሉ። ታቦተ ጽዮን እና ጌታ የተሰቀለበት መስቀል የት ነው ያሉት? የሚሉት ጥያቄዎች። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ አሰሳዎች፣ ቁፋሮዎች፣ መዛግብትን የማመሳከር ሥራዎች፣ አሉ የተባሉ የይዞታ ጥያቄዎችን የመመርመር ፍተሻዎች በመካሄድ ላይ ናቸው። በጣም የሚገርመው ነገር ግን የዓለም ቅርሶች መናኸርያ የሆነችው ኢትዮጵያ ሁለቱንም በተመለከተ ለዓለም የምትገልጣቸው ነገሮች አሏት።

ሰሞኑን በሀገራችን ኢትዮጵያ የመስቀል በዓል በመከበር ላይ በመሆኑ «ለመሆኑ ጌታ የተሰቀለበት መስቀል የት ነው ያለው?» የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ያሉ

መረጃዎችን እንቃኝ።

የመስቀሉ መጥፋት

በአብያተ ክርስቲያናት ከሚነገረው ትውፊት በስተቀር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ተሰቅሎት የነበረው መስቀል እንዴት ሊጠፋ እንደቻለ የተመዘገበ ታሪክ እኔ አላገኘሁም። አብዛኞቹ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ግን አይሁድ በመስቀሉ

ላይ ይደረግ የነበረውን ተአምራት በመቃወም ከክርስቲያኖች ነጥቀው እንደ ቀበሩት ይተርካሉ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ የቆስጠንጢኖስ

የሕይወት ታሪክ /Life of Constantine/ በተሰኘው መጽሐፉ ላይ

በክርስቲያኖች ዘንድ ታላቅ ሥፍራ የነበረው የጌታ መቃብር ተደፍኖ በላዩ ላይ

የቬነስ ቤተ ጣዖት ተሠርቶ እንደ ነበር ይናገራል። አውሳብዮስ በዝርዝር አይግለጠው እንጂ ይህ የቬነስን ቤተ መቅደስ በጎልጎታ ላይ የመሥራቱ ጉዳይ

የሮሙ ንጉሥ ሐድርያን በ135 ዓም ኢየሩሳሌምን Aelia Capitolina አድርጎ

እንደ ገና ለመገንባት የነበረው ዕቅድ አካል ነው።

አይሁድ በሮማውያን ላይ እስከ ዐመጹበት እና ኢየሩሳሌም ከክርስትና በኋላ ለመጀመርያ ጊዜ እስከ ጠፋችበት እስከ 70 ዓም ድረስ መስቀሉ በክርስቲያኖች

እጅ እንደ ነበር ይታመናል። በኋላ ግን ክርስቲያኖቹ የሮማውያንን እና የአይሁድን

ጦርነት በመሸሽ ከኢየሩሳሌም ወጥተው ወደ ሌሎች ሀገሮች ሲሰደዱ፤ በኋላም

በባር ኮባ ዐመፅ ጊዜ /132-135 ዓም/ ኢየሩሳሌም ፈጽማ በሮማውያን

ስትደመሰስ የመስቀሉ እና የሌሎችም ክርስቲያናዊ ንዋያት እና ቅርሶች ነገር

በዚያው ተረስቶ ቀረ። ንጉሥ ሐድርያንም የኢየሩሳሌም ከተማን ነባር መልክ

በሚለውጥ ሁኔታ እንደ ገና ሠራት። ያን ጊዜ ነው እንግዲህ የቬነስ ቤተ መቅደስ

በጌታችን መቃብር ላይ የተገነባው። ቆስጠንጢኖስ ለኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ

ለአቡነ መቃርዮስ በጻፈው እና ሶቅራጥስ እና አውሳብዮስ መዘግበው ባቆዩን

ደብዳቤ ላይ ይህ ታሪክ ተገልጧል።

ቀጣዮቹ 300 ዓመታት ለክርስቲያኖች የመከራ ጊዜያት ነበሩ። የሮም ቄሳሮች

ክርስትናን እና ክርስቲያኖችን የሚያሳድዱባቸው ዓመታት በመሆናቸው መስቀሉን

የመፈለግ ጉዳይ በልቡና እንጂ በተግባር ሊታሰብ አይችልም። ዓመታት እያለፉ

ሲሄዱም ኢየሩሳሌም እየተዘበራረቀች እና የጥንት መልኳ እየተቀየረ

በመሄዱ

በጌታ መቃብር ላይም የሮማ አማልክትን ለማክበር ቤተ መቅደስ በመሠራቱ ነገሩ

ሁሉ አስቸጋሪ እየሆነ ሄደ።

የመስቀሉ እንደገና መገኘት

ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች መስቀሉን እንደገና ያገኘችው

ንግሥት ዕሌኒ መሆንዋን ይናገራሉ። በ 380 ዓም አካባቢ የተወለደው ታሪክ

ጸሐፊው ሶቅራጥስ Ecclesiastical History በተሰኘው መጽሐፉ ላይ

በምእራፍ 17 መስቀሉ እንዴት እንደ ተገኘ ዝርዝር መረጃ ይሰጠናል። ንግሥት

ዕሌኒ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛ በጎልጎታ የጌታ መቃብር ላይ የተሠራውን የቬነስ

ቤተ መቅደስ አፈረሰችው፤ ቦታውንም በሚገባ አስጠረገችው። በዚያን ጊዜም

የጌታችን እና የሁለቱ ሽፍቶች መስቀሎች ተገኙ። ከመስቀሎቹም ጋር ጲላጦስ

የጻፈው የራስጌው መግለጫ አብሮ ተገኘ።

ሶቅራጥስ ከሦስቱ መስቀሎች አንዱ የክርስቶስ መሆኑን እንዴት ሊታወቅ እንደቻለ

ሲገልጥ እንዲህ ይላል «አቡነ መቃርዮስ በማይድን በሽታ ተይዛ ልትሞት
የደረሰችን አንዲት የተከበረች ሴት አመጡ። ሁለቱን መስቀሎችንም
አስነኳት፤
ነገር ግን ልትድን አልቻለችም፤ በመጨረሻ ሦስተኛውን መስቀል ስትነካ ድና
እና
በርትታ ተነሣች። በዚህም የጌታ መስቀል የትኛው እንደሆነ ታወቀ» ይላል።
ከዚያም ንግሥት ዕሌኒ በጌታ መቃብር ላይ ቤተ ክርስቲያን አሠራች። ከመስቀሉ
የተወሰነውን ክፍል ከፍላ ከችንካሮቹ ጋር ወደ ቁስጥንጥንያ ስትወስደው ዋናውን
ክፍል በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ተወችው።
ይህንን ታሪክ ሄርምያስ ሶዞሜን የተባለው እና በ450 ዓም አካባቢ ያረፈው ታሪክ
ጸሐፊም Ecclesiastical History, በተሰኘው ጥንታዊ መጽሐፉ በክፍል ሁለት
ምእራፍ አንድ ላይ ይተርከዋል። ዞሲማን እንደሚለው በ325 ዓም የተደረገው
ጉባኤ ኒቂያ ሲጠናቀቅ የቆስጠንጢኖስ ትኩረት ወደ ኢየሩሳሌም ዞረ።
ምንም እንኳን ሶዞሜን ባይቀበለውም መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ያመለከተው
ከከተማዋ በስተ ምሥራቅ ይኖር የነበረ አንድ አይሁዳዊ መሆኑን እና እርሱም

ይህንን መረጃ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ከነበረ መዝገብ ማግኘቱን እንደ
ሰማ ጽፏል። ንግሥት ዕሌኒ ባደረገችው አስቸጋሪ ቁፋሮ መጀመርያ ጌታ
የተቀበረበት ዋሻ፤ ቀጥሎም ከእርሱ እልፍ ብሎ ሦስቱ መስቀሎች መገኘታቸውን
ሶዞሜን ይተርካል። ከመስቀሎቹም ጋር የጲላጦስ ጽሑፍ አብሮ መገኘቱን እና
የጌታ መስቀል ከሌሎች የተለየበትን ሁኔታ ከሶቅራጥስ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ
ይተርከዋል።
ንግሥት ዕሌኒ በጎልጎታ፣ በቤተልሔም፣ በደብረ ዘይት፣ አብያተ ክርስቲያናትን
አሠርታ በሰማንያ ዓመቷ እንዳረፈች ሶዞሜን ይተርካል። ብዙ የታክ ጸሐፊዎች
ዕረፍቷን በ328 ዓም አካባቢ መስቀሉ የተገኘ በትንም በ326 ዓም ያደርጉታል።
በ457 ዓም አካባቢ ያረፈው ቴዎዶሮት የተባለው ታሪክ ጸሐፊም የመስቀሉን
የመገኘት ታሪክ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ያቀርበዋል።
መስቀሉ በኢየሩሳሌም
ንግሥት ዕሌኒ ለበረከት ያህል የተወሰነ ክፍል ወደ ቁስጥንጥንያ ከመውሰዷ
በቀር አብዛኛውን የመስቀሉን ክፍል በብር በተሠራ መሸፈኛ አድርጋ

በጎልጎታ ቤተ

ክርስቲያን እንዲቀመጥ ለአቡነ መቃርዮስ ሰጥታቸዋለች። ይህ መስቀል

በየተወሰነ ጊዜ እየወጣ ለምእመናኑ ይታይ እንደ ነበር አንዳንድ መረጃዎች

ያመለክታሉ። በ 380 ዓም ኤገርያ የተባለች ተሳላሚ መነኩሲት ቅዱስ

መስቀሉ

ወጥቶ በተከበረበት በዓል ላይ ተገኝታ ያየችውን ለመጣችበት ገዳም ጽፋ

ነበር። /M.L. McClure and C. L. Feltoe, ed. and trans. The

Pilgrimage of Etheria, Society for Promoting Christian

Knowledge, London, (1919)/

አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የመስቀሉ ክፍልፋዮች ወደ ተለያዩ

ሀገሮች

መወሰድ የጀመሩት በዚህ ጊዜ ነው። በሞሪታንያ ቲክስተር በተባለ ቦታ

የተገኘውና

በ 359 ዓም አካባቢ የተጻፈው መረጃ የመስቀሉ ክፍልፋዮች ቀደም ብለው ወደ

ሌሎች ሀገሮች መግባት እንደ ጀመሩ ያሳያል። ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም መስቀሉ

ከተገኘ ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ በ 348 ዓም በጻፈው አንድ ጽሑፍ ላይ

«ዓለሙ በሙሉ በጌታችን መስቀል ክፍልፋዮች ተሞልቷል» በማለት ገልጦ

ነበር። ከዚህም ጋር «ዕጸ መስቀሉ እየመሰከረ ነው። እስከ ዘመናችንም ድረስ
ይኼው እየታየ ነው። ከዚህ ተነሥቶም በመላው ዓለም እየተሠራጨ ነው።
በእምነት ክፍልፋዮቹን እየያዙ በሚሄዱ ሰዎች አማካኝነት» ብሏል።/On the
Ten Points of Doctrine, Colossians II. 8./
ዮሐንስ አፈ ወርቅም የመስቀሉን ቅንጣቶች ሰዎች በወርቅ በተሠራ መስቀል
ውስጥ በማድረግ ምእመናን በአንገታቸው ላይ ያሥሩት እንደ ነበር ጽፏል።
በዛሬዋ አልጄርያ በቁፋሮ የተገኙ ሁለት ጽሑፎች የመስቀሉ ክፍልፋዮች በ 4 ኛው
መክዘ የነበራቸውን ክብር ይናገራሉ። /Duval, Yvette, Loca sanctorum
Africae, Rome 1982, p.331-337 and 351-353/። በ 455 ዓም
በኢየሩሳሌም የነበረው ፓትርያርክ ለሮሙ ፖፕ ለልዮን የመስቀሉን ቁራጭ እንደ
ላከለት ተመዝግቧል።
በአውሮፓ ምድር የተዳረሰው አብዛኛው የመስቀሉ ክፍልፋይ የተገኘው
ከባዛንታይን ነው። በ 1204 ዓም በአራተኛው የመስቀል ጦርነት ጊዜ የዘመቻው
ተካፋዮች በዓረቦች ጦር ድል ሲመቱ ፊታቸውን ወደ ቁስጥንጥንያ አዙረው

ከተማዋን፣ አድባራቱን እና ገዳማቱን ዘረፏቸው። በዚያ ጊዜ ተዘርፈው ከሄዱት

ሀብቶች አንዱ ዕሌኒ ከኢየሩሳሌም ያመጣችው የመስቀሉ ግማድ ነበር። ይህንን

ግማድ እንደ ገና በመከፋፈል አብዛኞቹ የአውሮፓ አብያተ ክርስቲያናት ሊዳረሱት

ችለዋል። የወቅቱን ታሪክ ከመዘገቡት አንዱ ሮበርት ዲ ክላሪ «በቤተ መቅደሱ

ውስጥ አያሌ ውድ ንዋያት ይገኙ ነበር። ከእነዚህም መካከል ከጌታ መስቀል

የተቆረጡ ሁለት ግማዶች ነበሩ። ውፍረታቸው የሰው እግር ያህላል፤

ቁመታቸውም ስድስት ጫማ ይህል ነበር» ብሏል። /Robert of Clari's

account of the Fourth Crusade, chapter 82: OF THE MARVELS

OF CONSTANTINOPLE/

የመስቀሉ ለሁለተኛ ጊዜ መጥፋት

እስከ ስድስተኛው መክዘ ድረስ በኢየሩሳሌም ጎልጎታ የነበረው መስቀል በ614

ዓም በፋርሱ ንጉሥ ክሮስረስ 2ኛ /Chrosroes II/ ተወሰደ። የፋርሱ ንጉስ

ኢየሩሳሌምን በወረረ መስቀሉን እና ፓትርያርክ ዘካርያስን ማርኮ ወደ ፋርስ

ወሰዳቸው። እንደ ገና ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰው ሕርቃል በ 627 ዓም ባደረገው ጦርነት ክሮስረስ ድል ሲሆን ነው። ሕርቃል በመጀመርያ ወደ ቁስጥንጥንያ ካመጣው በኋላ እንደ ገና ወደ ኢየሩሳሌም ወስዶ በቀድሞ ቦታው

በጎልጎታ አስቀምጦት ነበር።

እስከ አሥረኛው መክዘ ድረስ በኢየሩሳሌም በቀድሞ ክብሩ ቢቆይም በረቦች

አካባቢውን እየተቆጣጠሩ ሲመጡ በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ክርስቲያኖች መስቀሉን በ 1009 ዓም አካባቢ ሠወሩት። ለ 90 ዓመታት ያህል ያለበት ቦታ

ተሠውሮ ከኖረ በኋላ በመጀመርያው የመስቀል ጦርነት ጊዜ በ 1099 ዓም

ከተሠወረበት ወጥቶ እንደ ቀድሞው መታየት ጀመረ።

ለሦስተኛ ጊዜ መጥፋት

በ 1187 ዓም በሐቲን ዐውደ ውጊያ ሳላሕዲን የተባለው የዓረቦች የጦር መሪ

የመስቀል ጦረኞችን ድል አድርጎ ኢየሩሳሌምን ሲቆጣጠር በዚያ የነበረውን መስቀል መውሰዱን አንዳንድ የታሪክ መዛግብት ይገልጣሉ። ከዚያ በኋላ ግን

መስቀሉ የት እንዳለ እስካሁን ማረጋገጥ አልተቻለም። በወቅቱ የነበሩት የሮም

ነገሥታት መስቀሉን ለማግኘት ከሳላሕዲን ጋር ብዙ ድርድር አድርገው

ሳይሳካላቸው ቀርቷል።

በአብዛኞቹ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የመስቀሉ ክፍልፋይ እንዳለ

ሁሉም ይናገራሉ። አንዳንዶቹ አለ የሚባለው ክፍልፋይ ከመብዛቱ የተነሣ

የሚያነሡት ትችት አለ። ጆን ካልቪን «ሁሉም ክፍልፋዮች ከመስቀሉ የወጡ

ከሆነ፤ እነዚህን ሁሉ ብናሰባስባቸው አንድ መርከብ የሚድ ያስፈልጋቸዋል።

ወንጌል ግን ይህንን መስቀል አንድ ሰው እንደ ተሸከመው ይነግረናል» ብሎ

ነበር።

ይህንን የካልቪንን ሂስ በተመለከተ መልስ የሰጠው ራውል ዲ ፈሌውሪ /

Rohault de Fleury,/ በ 1870 ዓም በዓለም ላይ አሉ በሚባሉት የመስቀል

ክፍልፋዮች ላይ ጥናት አድርጎ ነበር። ራውል መጀመርያ የት ምን ያህል መጠን

እንዳለ ካታሎግ አዘጋጀ፤ ከዚያም መጠናቸውን አንድ ላይ ደመረ። በታሪክ

እንደሚነገረው የመስቀሉ ክብደት 75 ኪሎ፣ ጠቅላላ መጠኑም 178 ኪዩቢክ

ሜትር ነው። ራውል ያገኛቸውና አሉ የተባሉት ክፍልፋዮች አንድ ላይ

ቢደመሩ .004 ኪዩቢክ ሜትር /3.,942,000 ኪዩቢክ ሚሊ ሜትር/ ነው።

በዚህም መሠረት ቀሪው 174 ኪዩቢክ የሚያህለው ሜትር የመስቀሉ ክፍል

ጠፍቷል ማለት ነው ብሏል። /Mémoire sur les instruments de la
Passion, 1870/

ግማደ መስቀሉ በኢትዮጵያ እንዴት መጣ ይቀጥላል.....

ከዲ/ን ዳንኤል ክብረት

ሼር በማድረግ ለሁሉም እንዲደርስ እናድርግ! —

Like . Natnael Muluneh Man

እናመሰግናለን ዲ/ን ዳንኤል....እኔም ትንሽ ልጨምር...

ንግስት ሄሌና/ዕሌኒ በኋላ ቅድስት ሄሌና በላቲንኛ ደግሞ ፍላቪያ ኢዮሊያ ሄሌና

አውጉስታ በመባል የምትጠራ ሲሆን የታላቁ ቆስጠንጢኖስ እናት

ናት። የትውልድ ቦታዋ “ከመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች ነው” ይባላል።

(ማስታወሻ፦ በሀገራችንም በመካከለኛው ዘመን እሌኒ የምትባል

ኢትዮጵያዊት ንግስት እንደነበረች ታሪክ ያስረዳል። በታላቁ

ቆስጠንጢኖስ እናትና በኢትዮጵያዊቷ ንግስት እሌኒ መካከል

ያለው የዘመን ልዩነት ግን እጅግ የተራራቀ ነው። ምክንያቱም

ኢትዮጵያዊቷ በ 16 ኛው ክ.ዘ፣ ቅድስት እሌኒ ደግሞ በ 3 ኛው

ክ.ዘ መጨረሻና በ 4 ኛው ክ.ዘ መጀመሪያ ላይ የኖሩ ናቸውና።)

ንግስት እሌኒ(ሄሌና)፣ የሮማ ጄኔራል የነበረውንና በኋላ ንጉስ የሆነውን

ክሎረንስን አግብታ፣

በ 274 ዓ.ም ቆስጠንጢኖስ የተባለ ወንድ ልጅ ወለደች።

ስለታላቁ ቆስጠንጢኖስ

አንድ የታሪክ ሁነት መግለጽ የግድ ነው። ይህ ሁኔታ ለመስቀሉ መገኘት ትልቅ ፋይዳ አለውና! ንጉስ ቆስጠንጢኖስ እንደነገሰ ከሶስት አቅጣጫ ከሶስት የተለያዩ ወገኖች ጋር ጦርነቶች ሊያደርግ ተነሳ። ውጊያውን ከማድረጉ በፊት ግን ስለማሸነፉ ልቡን ጥርጣሬ ወረረው። እንዲህ የልቡ ጥርጣሬ ከፍ ባለበት በሙሉ የቀትር ሰአት ግን አንድ በብርሃን የተሞላ መስቀል ከሰማይ ወደ ንጉሱ ቀረበ። በዚህ በከዋክብት ብርሃን በተሞላ መስቀል ላይም "በዚህ ምልክት ተዋጋ" የሚል ጽሁፍ ተመለከተ። በዚህ ጊዜ ንጉሱ ፈጥኖ በሰማይ ላይ የተመለከተውን መስቀል የሚመስልና የሚያክል እንዲሰራ በማዘዝ ከሰራዊቱ ቀድሞ እንዲመራ አደረገ። በመስቀሉ ኃይልም በቁጥር ከሱ ሰራዊት የሚበልጥ ጦር የነበራቸውን ጠላቶቹን አሸነፈ። በሌላ በኩል ንጉሱ በስጋ ደዌ በሽታ ይሰቃይ ስለነበር ወደአቡነ ሲልቨስተር (Bishop Sylvester) ቀርቦ ሲያማክራቸው፣ በክርስቲያን ወግ መሰረት አጥምቀውት ተፈወሰ። ከዚህ በኋላ ነው በ 325 ዓ.ም በቤተክርስቲያን ላይ የተነሳውን ክርክር ተመልክቶ ከአለም ዙሪያ 318 ሊቃነ ጳጳሳትን በመጥራት "ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ፍጡር ነው፤ ሁለት ባህርይ እንጅ አንድ አይደሉም" ብሎ የተነሳውን አርዮስን በኒቂያ ጉባኤ ላይ አስወግዞ ከቤተክርስቲያን እንዲለይ ያደረገውና ስርአትንና ኃይማኖትን የሚመለከቱ ሃያ ያህል ቀኖናዎች እንዲሰሩ ያደረገ ነው።

ንግስት እሌኒ(ሄሌና) ኢየሩሳሌምን ለመጎብኘት ተጓዘች። በዚያም
ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል አስቆፍራ በማውጣት
(በጎልጎታ) ዕውነተኛውን መስቀል በሰራው ተአምራት፣ ከሁለቱ
ወንጀለኞች ከተሰቀሉባቸው መስቀሎች በመለየት የክርስትና ምልክት
የሆነውን
መስቀል ለአለም ክርስቲያኖች አበረከተች። በዚህም ሳታበቃ
መስቀሉን ባገኘችበት ጎልጎታና በሌሎቹ የተቀደሱ ቦታዎች ላይ
ቤተጣኦቶችን አፈራርሳ ቤተክርስቲያን ለማሳነጽ የበቃች፤
በዚህም የቅድስና ክብር የተሰጣት ናት።

Like ·Hamid Awol

ጆን ካልቪን ትክክል ነው ማለት እንችላለን።

ይኸውም~ 174m³ ማለት እኮ 2 ትልቁ ኮንቴነር ከ 1 ትንሹ ጋር
እኩል ይመጣል ይህ ከሆነ ደግሞ መስቀሉ ይህን ያህል ነበር ለማለት
ይቻላልን?

1 big container = 68.5m³

1 small container= 28.5m³

2 big container + 1small container
(2×68.5m³ + 1×28.5m³) = 165.5m³

ያውም አልሞላም ገና የተባልነው 174m³ ሰለሆነ።

a×b×c=m³

a×b×c=174m³

Approximately

የመስቀሉ ውፍረት 0.5m

ቁመት 5m

እጆች የተዘረጋበት ደግሞ 3m ብናደርገው የሚሰጠን

~~ 0.5m × 5m × 3m = 7.5m³

So can u imagine 174m³ To 7.5m³?

ግልፅ ለማድረግ ወይም በቀላል አነጋገር ከቦታው የተነሳው የጀግናው አቡነ ጴጥሮስ ሀውልት የያዘው ቦታ በግምት 1m×1.5m×3m=4.5m³ ይሰጠናል

174m³ ማለት እኮ 40 ጊዜ እጥፍ የአቡኑን ሀውልት ያክል ነበር እነደማለት ነው። ወይም 40 ተመሳሳይ ሀውልትን ለመጫን 2 ትልቁ ኮንቴነር ከ 1 ትንሹ ኮንቴነር ያስፈልጋል።

ለክርስቲያን የሀገሬ ልጆች መልካም በዓል ይሆንላቹህ ዘንድ ልባዊ ምኞቴ ነው

Miko ZE Ethiopia

12/ ቅዱስ መስቀል ፍቅር ነው

መስከረም 14 ቀን 2007 ዓ.ም.

አባ ዘሚካኤል

የመስቀል በዓል ሲከበር ከትውፊታዊው ውብና ደማቅ አከባበር ባሻገር

መሠረታዊ ትርጉሙን፣ የትመጣውን ከነ ጎይለ ቃሉ ጥቅሙን መረዳት ዋናው ጉዳይ መሆን ይገባዋል። እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ልብዋ በመሰቀሉ ፍቅር የነደደ እሌኒ አምላኳ በመሰቀል እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሰሎ እንደ ኢየሩሳሌም ሴቶች ከድንግል ጋር ሆነው እነሆ እናታችሁ እንዳላቸው ሁሉ እሌኒም ከሦስት መቶ ዘመን በኋላ በረከቱን ታገኝ ዘንድ መስቀሉን ከተደበቀበት ለማውጣት ተነሣች። የመስቀሉን ማንነት የተረዳች ቅድስት እሌኒ እንዳሰበችው ተሳክቶላት፣ በመስቀሉ ተመክታ መስቀሉን ለዓለም ሁሉ ብርሃን ይሆን ዘንድ ከተቀበረበት እንዲወጣ አድርጋለች፤ በመስቀሉ የሚመካ አያፍርምና። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልኩበት ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ" (ገላ. 6: 14) እንዲል። ገና ሳታገኘው በልብዋ እያሰበችው ሳለ ልጅዋ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በሰማይ ላይ የመስቀል ምልክት የተጻፈ ሆኖ "በዚህ ምልክት ድል ታደርጋለህ" ተብሎ የአምላክ ፈቃድ ተገልጾለታል። ምክንያቱም ቅድስት እሌኒ በዘመኑዋ ሁሉ መስቀሉ በአይሁድ ክፉ ቅናትና ተንኮል ተሰውሮ በመኖሩ ሁል ጊዜ ስታዝን ስለኖረችና ከተሰወረበት ለማውጣት በብርቱ ምኞት ከትጋሃ ጸሎት ጋር ለአምላኳ ተስላ ስለነበር የድሉ ምሥራች በመስቀል ምልክት ጎይል ተገለጠ። ይህ ድል በዓለም ላሉ ክርስቲያኖች ሁሉ የድል ትምክህት ነበርና።

በጊዜው የኢየሩሳልም ከተማ በሮማዊው ጥጦስ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ 70 ዓመት መጥፋት ተያይዞ ሮማውያን ክርስቲያኖችን እያጠፉ ስለነበር፤ በተለይ ዲዮቅልጢያኖስ በነገሠ ጊዜ ያወጣቸው አዋጆች፣ አብያተ

ክርስቲያናት ይዘጉ የጣዖት ቤቶች ይከፈቱ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ይቃጠሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ንብረት ይወረስ፣ ክርስቲያን የሆነ ከሥራ ይባረር፣ ክርስቲያኖች በደል ቢደርስባቸው በፍርድ እንዳይታይላቸው ወዘተ የሚሉ ነበሩ። ለቆስጠንጢኖስ በሰማይ ላይ የታየው የድል ምልክት መስቀል ከላይ የተጠቀሰው የግፍ አዋጅ የተጫናቸውን ክርስቲያኖች ሁሉ ነጻነትን ያጎናጸፈ ነው። ቆስጠንጢኖስ በሮም ግዛት ከርሱ ጋር በዙሪያው ነግሠው የነበሩትን ሌሎች የአሕዛብ ነገሥታት በመስቀሉ ኀይል አሸንፎ የጥፋት አዋጅን በነጻነት አዋጅ ሽሮ ከላይ በጠቀስነው የርኩሰት አዋጅ ተቃራኒ የምሥራች ቃል የቤተ ክርስቲያንን ክብር ከመለሰ በኋላ በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን ከግብር ነጻ እንድትሆንና ከመንግሥት ገቢ ድርሻ እንዲኖራት፣ ዕለተ እሑድ ክብረ በዓል ሆና እንዲከበር፣ ቤተ ክርስቲያን ከተናዘዙ የመውረስ መብት እንዲኖራት፣ ኤጲስ ቆጶሳት በክርስቲያኖች ላይ ሙሉ ዳኝነት በመሥጠት ቤተ ክርስቲያን ነጻነቷን አግኝታ እንድትኖር አድርጓት ነበር።

ቅድስት እሌኒ ደግሞ በመስቀል ፍቅር ተስባ እንደ እመቤታችንና እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ወደ ቀራንዮ በማቅናት፣ ኪራኮስ በተባለው ሰው የእግዚአብሔር መልእክት

1. ደመራ እንድታስደምር፣
2. እጣን በደመራው እሳት ውስጥ እንድታስጨምር፣
3. ጸሎተ ምህላ እንዲደርስ፣
4. በደመራው ጭስ ስግደት ምልክት እንድታስቆፍር ተነግሯታል። በመሆኑም የተባለችውን በማከናወን የቦታውን ጥቆማ መስከረም 16 በደመራው ጭስ አመልካችነት ተረድታ የፍለጋው ቁፋሮ ከመስከረም 17 እስከ መጋቢት

10 ተከናውኖ መስቀሉን ለዓለም አብስራለች። ከዚያ ቀጥሎም ከመስቀሉ ተያያዥ የሆኑ ብዙ ተአምራዊ ሥራ እንደተደረገ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንረዳለን።

አገራችንም የመስቀሉ ብርሃን ታሪክ ተካፋይ ናትና ግማደ መስቀሉም ወደ ኢትዮጵያ በአፄ ዳዊት ዘመን ከጌታችን የሾህ አክሊልና ሉቃስ ከሣላት ከእመቤታችን ሥእለ አድህኖ ጋር መስከረም 10 ቀን ገብቷል፤ በዚህም ቀን የተቀጸል ጽጌ በዓል ይከበራል። (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አቡነ ጎርጎሪዎስ ካልዕ)

ከላይ ባጭሩ እንዳየነው የመስቀሉ ፍቅርን የተረዱ እንደ እሌኒ ያሉ መስቀሉን በልዩ ሁኔታ ያውም መሥዋዕትነትን በሚጠይቅ መልኩ አይሁድ ሦስት መቶ ዓመት ቆሻሻ በላዩ በመጣል ከሸሸጉበት ለማግኘት ለስድስት ወር እልክ አስጨራሽ የቁፋሮ ፍለጋ በኋላ በማግኘት ዛሬ እኛ በደስታ እንድንዋብበት ልዩ ሽልማት አድርገው አቆይተውልናል። በዚህ ወቅት የክርስትና ባለቤት ሆነን ክርስትናን የተረከብን ክርስቲያኖች ሁሉ ይህንን ጥልቅ ፍቅር ተረድተን ይሆን የምናከብረው? ወይስ ሌላውን ለማጀብ ይሆን? እዚህ ላይ ነው ወቅቱ የሚጠይቀንን የክርስትና ዋጋ ልብ ልንለው የሚገባን። አሁንም እስቲ ቆም ብለን እናስተውል፤ ምንአልባት የዚህ ዓለም አዚም አፍዝዞን በትክክል እንደ እነ ቅድስት እሌኒ በመስቀሉ ፍቅር ተሰበን እዳልሆነ ወይም እንደሆን እንመርምር። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይለናል "... ሰዎች ሆይ በዐይኖቻችሁ ፊት ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተስሎ ነበር ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?" (ገላ. 3፥1) ቅዱስ ጳውሎስ ለእውነት እንዳትታዘዙ ሲል

የመስቀሉን ፍቅርን እውነት ብሎታል፣ ከዚህ ዓለም እውነት የተለየ ሰማያዊ እውነት በሆነው የመስቀል ፍቅር ስር እመቤታችን ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር ቆመው ነበር፣ እነዲሁም ከዘመናት በኋላ ቅድስት እሌኒ ከሮም ወደ ኢየሩሳሌም በመስቀሉ ፍቅር ተስባ ሄዳ ነበር፣ ብዙዎቹ ቅዱሳን ልባቸው ቀራንዮ ነበር፣ ኢትዮጵያውያን በጎሊና ብቻ ሳይሆን በብዙ መከራ ቀራንዮን ለማየት እንደአሁኑ የአየር መጓጓዣ ሳይኖር የመስቀሉ ፍቅር እየመራቸው ተጉዘው ስእለታቸውን እንደ ቅድስት እሌኒ ይፈጽሙ ነበር።

ያልተቻላቸው እዚያው ከሩቅ በበዓታቸው ሆነው ነገር ግን በመንፈስ ተጉዘው ቀራንዮን ዳሰው እንደ እመቤታችንና እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ከእነርሱ ጋር እንዳሉ ሆነው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደተሰቀለ ሆኖ ተሰሎ በጎሊና ያዩታል፤ አንቺ ሆይ ልጅሽ ይርዳሽ ያጽናናሽ እንደ አላት እንደ ሰሙ ሆነው በመንፈስ ይሰሙታል። ልጆችሽ ሲል ነውና በዮሐንስ ተገብተው እነሱን ለእርስዋ መስጠቱ ነውና እንደ ነበሩ ሆነው ቃሉን በመመርመር ያስተውሉታል። ደቀ መዝሙሩንም እነኋት እናትህ ታጽናህ እንደ አለው ሁሉ ለእነርሱም እናታችሁ ሲል በመሆኑ በተመስጦ እንደ ዮሐንስ አጠገብዋ እንዳሉ ሆነው እናቴ ሆይ ይሏታል። በዮሐንስ እርሷን ለእነርሱ ለእኛም መስጠቱ ነውና እኛም ልብ ልንለው ይገባናል። አዚምን መንጥቀው ጥለው ፍጹም ፍቅሩን የተረዱ ሁለት ሺውን ዘመን እደሌለ ሁሉ ወደ ኋላ ተጉዘው ከድንግል ጋር ዛሬም ቀራንዮ መስቀሉ ስር በመንፈስ አንድ ሆነው ይገኛሉ። ዛሬም ትኩስ ፍቅሩን ለመጋራት በትኩስ እንባቸው ደመና ተመስጦ ወደ ቀራንዮ ተጉዘው እንደ ዮሐንስ ድንግል እመቤታችንን በእንባ የሃዘኗ ተካፋይ በመሆን እናትነትዋን ይጋሩታል።

በዚህ በዓላችን እኛም እንደ ቅዱሳኑ በአካል ባይሆንልን በአንቃእድዎ ልቡና በሰቂለ ጎሊና ሆነን ሁለት ሺህ ዘመን ወደ ኋላ ተጉዘን፣ ርቀቱን በተመስጦ አቅርበነው ከድንግል ጋር እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ቀራንዮ በመንፈስ እንሆን ዘንድ ልብ ልንለው ይገባል። በዘመኑ ባንኖርም በመልካም ምኞታችን እንደ ኖርን ይቆጠርልን ዘንድ፣ ተጉዘን ቀራንዮ ባንገኝ፣ ርቀት ቢወስነንም ስለመሻታችን እንደተጓዝን ይደረግልን ዘንድ፣ አንድም ባለንበት አምነን ስላከበርነው በረከቱን ያድለን ዘንድ። ኑ ቀራንዮ እንሂድ በእግራችን አይደለም በመንፈስ እንጂ፣ ኑ በበዓላችን ቀን መስቀሉን እንዳሰው በእደ ሥጋ አይደለም በዕደ ጎሊና እንጂ፣ የመስቀሉ ፍቅር ምሥጢር ቀራንዮ እንዲገኝ ዛሬም ያዘጋጀነው ይህ የመስቀል በዓል የቀራንዮ አካል ነው። አንድም ግሸን ደብረ ከርቤ እንሂድ የእውነተኛው መስቀል አካል ከእኛው ዘንድ አለና። ክርስቶስ ተሰቅሎ ዓለምን ያዳነበት፣ ደሙ የነጠበበት እውነተኛው መስቀል ለዓለም ብርሃኑን ያበራበትን የምናከብርበት ይህ ቀን ነውና። ምክንያቱም፦

- መስቀል የፍቅር ዙፋን ነውና፤ ቅዱስ ዮሐንስ ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ እስከመጨረሻው ሳይለይ የፍቅሩን መጠን ተረድተዋል። ማን ያርዳ የቀበረ እንዲሉ የጌታን ሕማሙን በዚያች ሌሊት የአዳሩንና የውሎውን ለሰው ልጆች ፍቅር ሲል በሰው ልጆች እጅ የተቀበለውን ጽኑ መከራውን አይተዋልና፤ በመልእክቱም "ፍቅርም እንደዚህ ነው፣ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለ ኀጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዝአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም" (1 ዮሐ. 4: 10) ያለው። የሰቀሉትን እንኳ ወደዳቸው፣ ይቅርም አላቸው።

በመስቀሉ ዙፋን በፍቅሩም ድነዋልና "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው " እንዲል።

• መስቀል የጥበብ ቤት ነውና፤ ጠቢቡ ሰሎሞን " ጥበብ ቤትዋን ሠራች ... ፍሪዳዋን አረደች ... ማድጋዋን አዘጋጀች ... ሁሉን ጠራች ... ኑ እንጀራዬን ብሉ ... አላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ፣ በማስተዋል መንገድ ሂዱ ... "(ምሳሌ 9፥ 1-10) ሲል፤ በቅዳሴ መጽሐፍ ላይ ጥበብ መድኀኒታችን ነው በማለት የሚሥጢሩን ባለቤትን ያመሠጥራል፤ በመስቀል ላይ ጥበብ የተባለ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ ሆኖ ዓለም ሁሉ ተመግቦት ድኖአልና። ለእኛ በመስቀል ጥበብ ቤት ላይ የተሰቀለው ጥበብ መድኀኔዓለም በዛሬው በምናከብረው የጥበብ ምሥጢር መገኛ በሆነው የመስቀል በዓል ራስ እርሱ ክርስቶስ ነው። በዚህም እርሱን የዓለምን መድኀን እንሰብክበታለንና። "አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፣ የግሪክ ሰዎች ጥበብን ይሻሉ፣ እኛ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" (1 ቆሮ. 1፥22-23) እንዲል።

• መስቀል የክርስቲያኖች ሁሉ አርማ ነውና፤ በምድራውያን ልማድ የሀገር ነጻነት በሰንደቅ ዓላማ አርማነት መውለብለብ እንዲታወቅ ሁሉ፣ ዛሬ የሰማያውያን ተስፋና የሕይወት አርማ በዓለም ላሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ መውጣት በክርስቶስ የታወጀበት ሰንደቅ ዓላማ መስቀል ነው። በሀገራችን ከአደይ አበባ ውበት ጋር አንድ ሆኖ የሚውለበለብበት መስከረም 16 ና 17 ልዩ ክብረ በዓሉ ነው። ልዩ የሚያደርገው ከአርማ ጋር የእግዚአብሔር ኀይል መሆኑ ነው። ቅዱስ መስቀል ምንኛ ድንቅ ነው? ዕፅነት/መስቀሉ የተቀረጸበት እንጨት/

ከመለኮት ጎይል ጋር አንድነት፣ ድንቅ ተዋሕዶ፣ አጋንንት የሚርዱለት የክርስቲያኖች ቤዛ ልዩ ምልክት፣ ለመረጣቸው ብቻ ጎይልን ያደርጉበት ዘንድ የታደሉት ግርማ ሞገስ ቅዱስ መስቀል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነው፣ ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ጎይል ነው (1 ቆሮ 1፥18) እንዲል።

የመስቀል ፍቅር ሰው፣ ልዩ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ "ወሶበ ርእዮሙ እግዚእ ኢየሱስ ለእሙ ወለረድኡ ዘያፈቅር ይቀውሙ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወደውን ደቀ መዝሙርና እመቤታችንን ከእግረ መስቀል ቁመው ባያቸው ጊዜ ሲል፣ ድንግል ልብዋ በሀዘን ጦር ተወግቶ የልጅዋን መከራ መቻል ጭንቅ በሆነባት ጊዜ ልጅዋ መሪር ሃዘንዋን ተመለከተ፤ እንዲሁም ከአጠገቧ ካሉት በእንባ ከሚራጩት የኢየሩሳሌም ሴቶች ጋር ከወንድ ወገን የሚያጽናናት አንድ ሰው ቅዱስ ዮሐንስን አየው። ወይቤላ ለእሙ ኦ ብእሲቶ ነዋ ወልድኪ፤ አንች ሆይ ልጅሽ ይርዳሽ ያጽናናሽ አላት። ውሉድኪ ሲል ነው በዮሐንስ እናን ለእርስዋ መስጠቱ ነውና። ወይቤሎ ለውእቱኒ ረድ ነያ እምክ፣ ደቀ መዝሙሩንም እነኋት እናትህ ታጽናህ አለው እምክሙ ሲል ነው። በዮሐንስ እርስዋን ለእኛ መስጠቱ ነውና"። (ዮሐ.19፥26-27)ብሎዋል። እነሆ ተመልከቱ፣ ለቅዱስ ዮሐንስ የባሕሪያችን መመኪያ የሆነችውን የተወደደች ድንግል እመቤት እናት ትሆነው ዘንድ ከአምላኩ ፈጽሞ ተሰጠችው። ድንግልን ከመስቀሉ ፍቅር ለይቶ ማየት ከቶ አይቻልም።

መስቀል ፍጹም ፍቅር፣ ርኅራሄ፣ የዋህነት እንደሆነ ሁሉ፣ ድንግልም እንዲሁ ፍጹም ፍቅርን የተሞላች የፍጡር ሁሉ ፍቅር ቢደመር የእርስዋን ፍቅር

ይደርስ ዘንድ ሊታሰብ አይችልም፤ ርኅራሄዋ እንኳን ለሰው ልጅ ለፍጡር ሁሉ የምታዝን አዛኝት ናት እንጂ፤ በየዋህነትዋ የዋሂት ርግብ የተባለች ፍጹም ናት እንጂ።ድንግል በዚህ ዓለም ሳለች ልጅዋ እንደተሰቀለ ሆኖ በኅሊናዋ ተስሎ፣ ልብዋ በሕማሙ ጦር ተወግቶ፣ ሃዘንዋ ጸንቶ፣ በሰቆቃ ተውጣ፣ እጅዋን ወደ ላይ ዘርግታ አንድም ስለልጅዋ ኀዘን እንባዋን ስታዘራ በሌላም ልጅዋ ይምረን ዘንድ ስለእኛ ስለ ሰው ልጆች ምልጃ ታደርግ ዘንድ ከቀራንዮ ከስቅለቱ ቦታ እንዲሁም ከመቃብሩ ጎልጎታ አንድም ቀን ተለይታ አታውቅም ነበር። ሕማሙን እንደ እርስዋ ማን ተረዳ? ድንግልን የመስቀሉ ፍቅር እንዲገባን አማልጂን ብለን እንማጸናት፣ በአምስቱ ኀዘናትሽ ቃል ኪዳን አስቢን እንላት ዘንድ የዚህ ዓለም ፈተና ግድ ይለናልና። ልጅዋን ወዳጅዋን፣ እስዋንም ደስ እናሰኝ ዘንድ ፍቅርዋን፣ ርኅራሄዋን፣ የዋህነትዋን እንምሰል። ወገኖቼ ቂም በቀል፣ ክፋት፣ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ዘረኝነት፣ወዘተ እንተው፣ ለዚህ ዓለምም ለወዲያኛውም አይጠቅሙምና።

እኛም ዛሬ ቅዱስ ዮሐንስን የመስቀሉ ፍቅር አብነት እናድርገው፣ ይኸውም ልዩ የሚያደርገው መለኮታዊ ፍቅሩን መረዳቱ፣ የመስቀሉ ሥር የፍቅረ ሰው መሆኑ፣ የጌታን የሕማሙን ጥልቀት መጠን ማስተዋሉ፣ ሁል ጊዜ ነገረ መስቀሉን በማሰብ ቁጽረ ገጽ መሆኑ። ከዚህ ዓለም ልዩ በሆነ ፍቅር ጌታውን የመውደዱ፣ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" በማለት አምላክ የሰው ልጅን ከመውደዱ ጋር ሰው ወንድሙን ቢጠላ እግዚአብሔርን እንዳያውቅ በሚለው ጎይለ ቃልና ረቂቅ ምሥጢር ከተግባራዊ ሕይወት ጋር አቅርቦቱን ልብ ልንለው ግድ ይለናል።

በነገረ መስቀሉ አንጻር፣ የድንግል እመቤታችንና የቅዱስ ዮሐንስ ፍቅረ

መለኮት ሕይወታቸው ቅድስናን አጎናጽፏቸው ተገኝቷል። እኛም ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ ለሁላችንም "ዓለምንና በዓለም ያሉትን አትውደዱ ... የአባት ፍቅር በውሰጡ የለም፣ ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል" (1ዮሐ. 2፥15.17) በማለት የሕይወቱን ተግባራዊ ትምህርት እንዳስተላለፈልን ሁሉ፤ በዚህ ዓለም ስንኖር ነፍስና ሥጋችንን በፍቅረ መለኮት ተጸምዶ፣ በሕማማተ መስቀል ውስጥ ተገብቶ በፍቅር ውስጥ መኖርን፣ መንፈሳዊ አገልግሎታችን በፍቅረ መስቀል አንጻር ብቻ ሆኖ መሰለፍን፣ መሰባሰባችን በፍቅረ እግዚአብሔር ግብዣ ማድረግን፣ ሥራችንን በፍቅር ውስጥ ማከናወንን ያመለክተናል። ትዳራችን የመስቀል ፍጹም ፍቅር፣ ርኅራሄ፣ የዋህነት የተሞላ ሁል ጊዜ ለይቅርታ ዝግጁ የሆነ በዘለዓለም ሕይወት ተስፋ የተሞላ ሊሆን ይገባዋል። ባጠቃላይም ሕይወታችን በመንፈሳዊ ጎሊና የተዋበና የመስቀሉን ፍቅር የሚያዘክር ይሆን ዘንድ፣እግዚአብሔር እርሱን በመውደድና በማይዝል በመንፈሳዊ የፍቅር ወላፈን ይጸምደን ዘንድ ፈቃዱ ይሁን። አሜን!!!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር! አሜን!!!

13/ የመስቀል በዓል ክርስቲያናዊ አከባበር

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከምታከብራቸው ዘጠኙ የጌታችን ንዑሳን በዓላት አንዱ መስከረም 17 የሚከበረው የመስቀል በዓል ነው። መስቀል የሰላማችንና የድኅነታችን የመቀደሳችን አርማ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጆች ለማዳን፥የዘላለም ሕይወትን ለመስጠት መስዋዕትነት የከፈለበት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ያፈሰሰበት መንበር፥ ሲሆን አምላካችንን የመንመለከትበት መስታወት ነው።

ይህ ዕለት ከ300 ዓመታት በላይ ጠፍቶ የነበረውን ቅዱስ መስቀል በንግሥት ዕሌኒ አማካኝነት መገኘቱን የምንዘክርበት በዚህም ደስ የምንሰኝበት ዕለት ነው። በዓሉ በምን ምክንያት እንደሚከበር ታሪኩን፣ በቅድሰት ቤተ ክርስቲያን ካህናቱና ምእመናን በአንድነት በመሆን እንዴት እንደሚያከብሩት፣ ምእመናን በየአካባቢያቸው በየቤታቸው እንዴት እንደሚያከብሩት ቀጥለን እንመልከት።

የቅዱስ መስቀሉ መዳፈን /መቀበር/ እና መገኘት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን የተሰቀለበት ቅዱስ መስቀል ሕመማንን በመፈወሱ ምክንያት በርካታ አሕዛብ ክርስቲያን እንዲሆኑ አስችሏል። ይህን የተመለከቱ አይሁድ ቅዱስ መስቀሉን በአንድ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ እንዲቀበር አደረጉ። የአካባቢው ነዋሪዎች በየቀኑ ቆሻሻ ስለሚጥሉበት ቦታው ወደተራራነት ተቀየረ። ምንም እንኳን መስቀሉን ለማውጣት ባይችሉም በኢየሩሳሌም የነበሩ ክርስቲያኖች ቦታውን ያውቁት ነበር። በሰባ ዓመተ ምሕረት በጥጦስ ወረራ ኢየሩሳሌም ስለጠፋች በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖች ተሰደዱ። የተቀበረበትን ቦታ የሚያውቅ ባለመገኘቱ

መስቀሉ ከ 300 ዓመታት በላይ ተዳፍኖ /ተቀብሮ/ ኖሯል።

በ 326 ዓ.ም. የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት ዕሌኒ ቅዱስ መስቀሉን ለመፈለግ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ አደረገች። እዚያም ደርሳ ጉብታ የሆነውን ሁሉ ብታስቆፍር መስቀሉ ያለበትን ቦታ ማግኘት አልቻለችም፤ ሰውም ብትጠይቅ የሚያውቅ አልተገኘም። በመጨረሻም የመስቀሉ መገኘት የእግዚአብሔር ፈቀድ ነበርና አንድ ይሁድ(ኪራዮስ) የተባለ አረጋዊ አግኝታ ቅዱስ መስቀሉ የተቀበረበትን አካባቢ አመለከታት። ይህ ሰው በኋላ በክርስቶስ አምኖ ተጠምቋል፤ ስሙም ኪራኮስ ተብሏል።

ንግሥት ዕሌኒ ዕንጨት ደምራ በዚያ ላይ ዕጣን ጨምራ በእሳት ለኮሰችው፤ ቅዱስ ያሬድ በድጓው «ዘዕጣን አንጸረ ፣ሰገደ ጢስ» እንዳለ የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ወደ ታች ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በጣት ጠቅሶ እንደማሳየት ያህል በማመልከቱ። ንግሥት ዕሌኒም ጢሱ ያረፈበት ቦታ ቅዱስ መስቀሉ የተቀበረበት እንደሆነ አመነች።

በዚህም መሠረት ከመስከረም 17 ጀምሮ ሌሊትና ቀን የጉድፍን ኮረብታ ቆፍረው ካስወገዱ በኋላ ሦስት መስቀሎች የተገኙ ሲሆን። የጌታም መስቀል ሙት በማስነሣቱ ተለይቶ ታውቋል። መስቀሉ የተገኘው መጋቢት 10 ቀን 326 ዓ. ም. ነበር። ቅድስት ዕሌኒ ይህን ተአምር በማየቷ እጅግ ደስ አላት። ሕዝቡም ሁሉ መስቀሉን እየዳሰሱ ኪርያላይሶን እያሉም በመዘመር ደስታና ሐሴት አደረጉ። ቀኑ መሸቶ ጨለማ በሆነ ጊዜም የኢየሩሳሌም ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስና ንግሥት ዕሌኒ፣ ሠራዊቱና ሕዝቡ በሰልፍ በችቦ መብራት መዝሙር እየዘመሩ ቅዱስ መስቀሉን ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደው በአንድ የጸሎት ቤት አኖሩት። በኋላም ለመሰቀሉ መታሰቢያ

ቤተክርስቲያን ተሰርቶ ተመርቆ የገባው /ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው/ መስከረም 17 ቀን 326 ዓ. ም. ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ሁለቱም ዕለታት ይከበራሉ፤ በደማቅ ሁኔታና በመጀመሪያ ደረጃ የሚከበረው ግን መስከረም 17 ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት መጋቢት ዐሥር ቀን ሁልጊዜም በዐቢይ ጾም ወቅት የሚውል መሆኑና ለመስቀሉ የተሠራው ቤተ መቅደስ የከበረው መስከረም 17 መሆኑ ነው። ይህንንም ስንክሳር «የከበረ መሰቀልም ዳግመኛ የተገለጠበት መጋቢት ዐሥር ቀን ነው። ዜናውንም በዚሁ ቀን ጽፈናል። ምእመናንም በታላቁ ጾም መካከል በዓሉን ማክበር ስላልተቻላቸው በዓሉን ቤተ ክርስቲያኑ በከበረችበት ቀን አደረጉ። ይህም መስከረም 17 ቀን ነው። በዚህም ቀን አስቀድሞ ከከበረ መቃብር በንግሥት ዕሌኒ እጅ የተገለጠበት ነው» በማለት ያስረዳል።

ስንክሳሩ እንደሚገልጸው ክርስቲያን ሁሉ የትንሣኤውን በዓል በኢየሩሳሌም ተሰባስበው ያከብሩ እንደነበሩ ሁሉ የመስቀሉንም በዓል ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በአንድነት ያከብሩ ነበር።

በዓሉ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይከበራል?

ትልቁ የበዓል ማክበር ሥርዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ በቤተ ክርስቲያን መሰባሰብ ነው። ሊቃውንቱ በፍትሐ ነገሥት «ተጋብኡ ኩሎ ዕለት ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወፈድፋደሰ በዕለተ ሰንበት ወበበዓላት ወበዕለተ ትንሣኤ ዘውእቱ ዕለተ እሑድ። ወናሁ ንሬእዮሙ ለአሕዛብ ከመ ኢይደኅሩ እምተጋብኦ በዕለተ በዓሎሙ፤ ሁልጊዜ በቤተ ክርስቲያን ተሰብሰቡ፤ ይልቁንም በዕለተ እሑድ፣ በዕለተ ቀዳሚት፣ በጌታ በዓላት ወደ ቤተ ክርስቲያን ተሰብሰቡ። እንኳን ክርስቲያን አሕዛብም በዓል በሚያደርጉበት

ቀን ከመሰብሰብ ወደኋላ እንዳይሉ እነሆ እናያቸዋለን።» ያሉት ለዚህ ነው። /ፍትሐ ነገሥት ገጽ 254/ በዓሉን ማክበር የሚጀመረው በዋዜማው በመስከረም 16 ነው። ምእመናን ከየቤታቸው ዕንጨቱን ችቦውን ይዘው ለደመራ በተዘጋጀው ቦታ እያመጡ ይደምራሉ። ካህናቱ፣ ምእመናኑ ሁሉ በአንድነት ይሰበሰባሉ። ካህናቱም በደመራው ፊት ለፊት ጸሎት አድርሰው «መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሰርገዎ ሰማየ እምኩሉሰ ፀሐየ አርአየ» እያሉ ደመራውን ይዞራሉ ትርጉሙም «መስቀል በክዋክብት አበራ፤ ሰማይን አስጌጠ፤ከሁሉም በላይ ፀሐይን አሳየ» ማለት ነው። በገጠር ሕዝቡ ችቦውን በማብራት «ኢዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ» እያለ ደስታውን ይገልጣል። በከተማ አካባቢ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስለ መስቀል የተዘመሩ መዝሙራትን በመዘመር እግዚአብሐርን ያመሰግናሉ።

ቅዱስ መስቀሉ በተገኘበት ዘመን የምሥራች ዜና ከቦታ ወደ ቦታ የሚሸጋገረው እሳት በማንደድ ስለነበር በዘመኑ የነበሩ ክርስቲያኖች ደስታቸውን የገለጡት፣ የምሥራቹንም እስከ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ያደረሱት ችቦ በማብራትና መዝሙር በመዘመር ስለሆነ ይህን ለመዘከር በመሸ ጊዜ ሕዝበ ክርስቲያኑ በየደጁ ችቦውን እያበራ ደስታውን ሲገልጥ እግዚአብሔርንም በመዝሙር ሲያመሰግኑ ያመሻሉ።

በገጠሩ የሀገራችን ክፍል ደመራው የሚለኮሰው በ17 ጠዋት ሲሆን በአዲስ አበባና በአካባቢው ግን ደመራው የሚለኮሰው ጸሎቱ እንዳለቀ ነው። ደመራው የተጸለየበትና የተባረከ ስለሆነ ሕዝቡ አመዱንና ትርኳሹን እየተሻማ ወደየቤቱ ይዛ ይሄዳል። አመዱን ቢቀቡት፣ ቢተሻሹት፣ በጥብጠው ቢጠጡት ይፈውሳል፤ ለከብት እንኳን ሳይቀር መድኃኒት

ይሆናል። ባላገሩ ከብቱን ሁሉ በትርኳሹ ይተኩሳል ጤና እንዲሆንለት።

የበዓሉ ዕለት ምእመናን በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው የነግህ ጸሎት ያደርሳሉ። በዓላት በዚህ ምድር ሳለን ተድላ ነፍስ ተድላ ሥጋ ያለባትን፣ ፍጹም የሆነ ሰላም፣ ረፍት፣ ደስታ የምትሰጠውን መንግስተ ሰማያትን መቅመሻ ናቸው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይህን ከምትፈጽምባቸው ሕይወቶቿ ዋናው ቅዳሴ ነው። ስለዚህ ምእመናን በዚህ ዕለት ቅዳሴ አስቀድሰው ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ተቀብለው ደስ ብሏቸው በዓሉን ያከብሩታል። በዕለቱ የሚቀደሰው ቅዳሴ ስለ ነገር መስቀል አብዝቶ የሚናገረው ቅዳሴ ዘዮሐንስ አፈወረቅ ነው። በዚህ ቅዳሴ ከሚነበበው የነገረ መስቀል ንባብ መካከል ለመጥቀስ ያህል፦

«ኦ አዕዳው እለ ለሐኳሁ ለአዳም ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል፤ ኦ አእጋር እለ አንሶሰዋ ውስተ ገነት ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል፤ ኦ አፍ ዘነፍሐ ውስተ ገጹ ለአዳም መንፈስ ሕይወት ብሒዐ መጺጸ ዘምስለ ሐሞት ሰረበ፤አይ አፍ ወአይ ከናፍር ወአይ ልሳን ዘይትናገር ሕማማቲሁ ለወልድ፤ ልብ ይትከፈል ፣ወሕሊና ይዘበጥ ፣ወነፍስ ትርዕድ፣ ወሥጋ ይደክም ሶበ ይትነገር ሕማማቲሁ ለፍቁር፤አዳምን የፈጠሩ እጆች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ፣ ወዮ፤ በገነት የተመላለሱ እግሮች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ፣ ወዮ፤ በአዳም ፊት የሕይወት መንፈስን እፍ ያለ አፍ ከሐሞት ጋራ የተቀላቀለ መጻጻን ጠጣ፣ ወዮ፤ የወልድን መከራውን የሚናገር ምን አፍ ነው፣ ምን ከንፈር ነው፤ ምን አንደበት ነው፤የፍቁር የጌታ ሕማማት በተነገረ ጊዜ ልብ ይለያል፤ ሕሊናም ይመታል፤ ነፍስም ትንቀጠቀጣለች፤ ሥጋም ይደክማል፣ /ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወረቅ/ በዋዜማው /በደመራ ዕለት/፣ በዕለቱ በጸሎተ ነግህ እና

በጸሎተ ቅዳሴ የሚሰበኩት ምስባካት የሚከተሉት ናቸው።

«ወረከብናሁ ውስተ ያመ ገዳም። ንበውዕ እንከሰ ውስተ አብያቲሁ ለእግዚአብሔር። ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ። በዱር ውስጥም አገኘነው፤ ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን፤ እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን» /መዝ. 131 6/ «ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ፤ ከመ ያምሥጡ እሞገጸ ቅስት፤ ወይድኅኑ ፍቁራኒከ ፤ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው፤ ወዳጆችህ እንዲድኑ» /መዝ. 59 4/ የሚነበቡት የወንጌልና የመልእክታት ክፍሎችም /ዮሐ. 19 25-28 ዮሐ. 3 14-22፣ ማቴ. 8 16-28፣ ሐዋ. 5 26-33 1ኛ ጢሞ. 5 9-16፣ያዕ 3፡11/ ፍጻሜ ናቸው።

ቅዳሴው፣ መዝሙራቱ፣ ምንባባቱ ስለ ቅዱስ መስቀል በርካታ ትምህርት ይሰጣሉ። እነዚህንም ነገሮች ቅዱስ ያሬድ «መስቀል በኩል ጊዜ፣ ወለኩሉ ሰዓት፤ መስቀል በጊዜው ሁሉና በሰዓቱ ሁሉ ነው» እንዳለው ስለ ቅዱስ መስቀል ዘወትር ስናስብ በተለይም ይህን በዓል ስናከብር እነዚህን ነገሮች እያሰብን ደስ ልንሰኝ እግዚአብሔርንም ልናመሰግን ይገባል።

መስቀል ብርሃን ነው

ጨለማ የተባለ ኃጢአትና ሞት በሞትም ላይ ሥልጣን ያለው የጨለማው አበጋዝ ዲያብሎስ ድል የተነሳበት፤ ሥልጣኑ የተሻረበት በመሆኑ መስቀል ብርሃን ተብሏል። በጌታችን የመስቀል ሞት ብርሃን የተባለውን ሰማያዊ ሕይወት አግኝተናል። «ሕይወትም በእርሱ ነበረ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበር፤ ብርሃንም በጨለማ ያበራል፤ ጨለማም አላሸነፈውም።» እንዲል።

/ዮሐ. 1 4-5/

ከዚህ በተጨማሪ የመስቀል ብርሃን መባል ከበዓሉ ጋር የተያያዘ ታሪካዊ ይዘትም አለው። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ከመክስምያኖስ ጋር በተዋጋ ጊዜ በሰማይ በፀሐዩ ብርሃን ላይ «በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን ድል ታደርጋለህ» የሚል የመስቀል ምልክት አየ። የመስቀል ምልክትን በፈረሱና በበቅሎ ልጓም፣ በጦር መሣሪያውና በጦር ልብሱ፣ በባንዲራው ላይ አድርጐ ጠላቱን አሸንፏል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ይህን ታሪክ መሠረት አድርጋ «መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሰርገው ሰማየ እምኩሉሰ ፀሐየ አርአያ» እያለች ትዘምራለች። በሌላም በኩል ቅዱስ መስቀል ከተዳፈነበት ቦታ መገኘቱና መታየቱ «መስቀል አበራ» አስብሎታል። ምክንያቱም ጨለማ መሰወር ፤ብርሃን ደግሞ መገለጥ ነውና።

መስቀል የድኅነት፣ የሰላም ምልክት ነው።

ጌታችን የፈጸማቸው የማዳን ሥራዎች ሁሉ ፍጻሜ መስቀል ነው። ራሱ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ «ሁሉ ተፈጸመ» ብሏል። /ዮሐ. 19፡30/ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ «መስቀል መልዕልተ ኩሉ ነገር፤ ያድኅነነ እምፀር መስቀል ከሁሉ በላይ ነው፤ ከጠላት /ዲያብሎስ/ ያድነናል»፣ «አድኅነ ሕዝቦ በመስቀሉ፣ ሕዝቡን በመስቀሉ አዳነ» በማለት ዘምሯል። ዲያብሎስ የመስቀል ምልክትን ይፈራል፤ በመስቀል ፊት መቆም አይችልም። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በጦር ሠራዊቱና በጦር መሣሪያዎቹ ሁሉ ላይ የመስቀል ምልክት አድርጎ በመክስምያኖስ ላይ ያደረ ርኩስ መንፈስን በማራቁ አላዊውን ንጉሥ በቀላሉ መሸነፍ ችሏል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያን ነገሥታት በዘውዳቸው ላይ፣ በጦር

መሣሪያዎቻቸው ላይ የመስቀሉን ምልክት ይጠቀሙበታል። ምእመናን የመስቀል ምልክትን በሰውነታቸው ላይ በተለያየ ቦታ ይነቀሱታል፤ ልቡናቸውን ይባርክ ዘንድ በደረታቸው ላይ ያንጠለጥለታል፤ በደነገጡ፣ የሕሊና ሰላም ባጡ ጊዜ ቅዱስ ያሬድ «መስቀል ትእምርተ ሰላምነ፤ መስቀል የሰላማችን ምልክት ነው።» እንዳለ በትእምርተ መስቀል አማትበው የሰላም ፀር የሆነውን ዲያብሎስን ያርቁበታል።

ታዲያ ይህ የሚሆነው፣ ትእምርተ መስቀል የተሰጠው እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ለወዳጆቹ ነው እንጂ እንዲያው ዝም ብለው ለጌጥ ለሚያንጠለጥሉት አይደለም። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ «ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ፤ ከመ ያምሥጡ እምገጸ ቅስት፤ ወይድኅኑ ፍቁራኒከ። ለሚፈሩህ ምልክትን /መስቀል/ ሰጠሃቸው ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ። ወዳጆችህም እንዲድኑ።» እንዳለ። /መዝ. 59 4-5/ ለሚፈሩህና ለመዳጆችህ አለ እንጂ ለሁሉም አላለም።

ስለዚህ ዘወትር በጸሎታችን «መስቀል ኃይልነ፣ መስቀል ጽንዕነ፣ መስቀል ቤዛነ፣ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ። አይሁድ ክሕዱ ንሕነሰ አመነ ወእለ አመነ በኃይለ መሰቀሉ ድኅነ።» እንላለን። በእያንዳንዷ ዕለታዊ ሕይወታችን።

የመስቀል ምልክትን እንጠቀማለን፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ከጉልላቷ በላይ መስቀል ታደርጋለች፤ በቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች በርና መስኮት ላይም የመስቀል ምልክት ታደርጋለች። እነዚህ ነገሮች አሁን የመጡ ሳይሆን ሐዋርያት «እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን።» ፣ «ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ» /1 ቆሮ.

1፡23፣ገላ. 6፡14/ እያሉ መስቀል የሞት ምልክት ሳይሆን የድኅነት ምልክት መሆኑን ካስተማሩ በኋላ የተጀመረ ነው። ከሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስከ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የኖረው ጠረጡሊስ በዘመኑ ክርስቲያኖች በመስቀል እንዴት ይጠቀሙ እንደ ነበር የሚከተለውን ተናግሮአል። «በተግባራችን ሁሉ በምንገባበትና በምንወጣበት ጊዜ፣ ልብሶቻችንን ከመልበሳችን በፊት፣ ከመታጠባችን በፊት፣ በቀንና በማታ ወደ ምግብ ገበታ በምንቀርብበት ጊዜ፣ ማታ መብራታችንን በምናበራበት ጊዜ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ በምንጀምርበትና በምንፈጽምበት ጊዜ፣ በዕለታዊ ሕይወታችን መደበኛ ሥራችንን በምንጀምርበት ጊዜ በትእምርተ መስቀል ፊታችንን እና መላ ሰውነታችንን እናማትባለን።»

መስቀል አንድ የሆንበት ነው

ቅዱስ ጳውሎስ «እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በእርሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእረሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው። መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምስራች ብሎ ሰበከ በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና።» /ኤፌ. 2 14-18/

ብሎ እንዳስተማረ በቅዱስ መስቀል እግዚአብሔርና ሰው ታርቀዋል፤ ህዝብና አህዛብ አንድ ሆነዋል። በዚህ ምክንያት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን

ልጆቿን ሰብስባ በጸሎት፣ በመዝሙር ይልቁንም የአንድነት መገለጫ በሆነው በጸሎተ ቅዳሴ ታከብረዋለች። ምእመናንም በአንድነት ሆነው አብረው በመብላት ፤አብረው በመጠጣት በዓሉን ያከብሩታል። ምግበሥጋ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። በልተን ጠጥተን በሕይወት እንድንኖር እግዚአብሔርንም እንድናመሰግን አምላካችን መብልና መጠጥን ሕይወት አድርጎ ሰጥቶናል። በበዓላትም ተድላ ሥጋ ማድረግ የተገባ ስለሆነ ምእመናን አብሮ በመብላትና በመጠጣት ያከብሩታል። ይህ ሲባል ግን አብዝቶ በመብላትና በመጠጣት ከእግዚአብሔር ተለይቶ የሥጋን መሻት፤ የዓይንን አምሮት ለመፈጸም እስክንደርስ መሆን የለበትም። ይልቁንም የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት መንፈሳዊ ደስታን በመደሰት በዓሉን ማሳለፍ ይገባናል።

ማጠቃለያ

ስለ ቅዱስ መስቀል እነዚህን ለምሣሌ ያህል ጠቀስን እንጂ የነገረ መስቀል ትምህርት በዚህ የሚወሰን አይደለም። በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የዘመን አቆጣጠር ከመስከረም 17-25 ያለው ጊዜ ዘመነ መስቀል ይባላል። በዚህ ጊዜ ነገረ መስቀል ይነገራል፤ መዝሙረ መስቀል ይዘምራል። ምእመናን በዚህ ጊዜ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በመገኘት ነገረ መስቀሉን ልንሰማ እግዚአብሔርንም በመዝሙር ልናመሰግን ይገባል። ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንዱ የነበሩት መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ስለ ቅዱስ መስቀል ያስተማሩትን ትምህርት ጠቅሰን ጽሑፋችንን እናጠቃልላለን።

«ቅዱስ መስቀል በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሁሉ በሁሉ ነው። ቅዱስ መስቀል የወንጌል መሠረትና ልብ ነው። ቅዱስ መስቀል በቤተ ክርስቲያን

ከቀረ የወንጌል ፍሬ ነገር ቀረ ማለት ነው። የመስቀሉ ነገር በብዙዎች ዘንድ የጥበብ ተቃራኒ የሆነ ሞኝነትን መስሎ መሰናክል ሆኗል። ለሚያምኑት ግን የእግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ ነው። ዓለም በጥበቡና በዕውቀቱ፣ በኀይሉም አልዳነም። ምክንያቱም እግዚአብሔር የዓለምን ኀይል፣ ጥበብና ዕውቀት ሞኝነት በመሰለው በመስቀል ነገር ከንቱ አድርጎታል። ስለሆነም በድካምና በሞኝነት ማለት በመስቀል ስብከትና በእምነት ዓለምን ለማዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኗል። ስለ መስቀልና በመስቀል ስለተሰቀለው ክርስቶስ መሰበክ በማያምኑት ዘንድ ሞኝነት፣ ድካምና መሰናክል ቢመስልም በምእመናን ዘንድ ግን የእግዚአብሔር ኀይል ሆኖ ይታያል። ምክንያቱም በሰው ዘንድ ሞኝነት ሆኖ የታየው የእግዚአብሔር ሥራ ከሰው ጥበብ ይልቅ ስለሚጠበብ ነው። በሰው ዘንድ ድካም ሆኖ የታየው የእግዚአብሔር ሥራም ከሰው ኀይል ይልቅ ስለሚበረታ ነው። እንግዲህ ቅዱስ መስቀል በሚያምኑና በማያምኑ መካከል መለያ ምልክት ነው፤ መለኪያ ሚዛንም ነው። ለእኛ ለምናምን ቅዱስ መስቀል ወደ ሰማይ የምንደርስበት መሰላል ነው። ለማያምኑ ግን ወደ ሰማይ እንዳይደርሱ የሚሰናከሉበት እንቅፋት ነው።

በክርስቶስ አምናለሁ የሚል ሁሉ እንደ አይሁድ «መስቀሉን አይግፉ» ነገር ግን እንደ ቅድስት ዕሌኒ መስቀሉን ይፈልግ፤ መስቀል ከሁሉ ነገር በላይ ነውና።»

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

መስቀል =>

14/ ዘመነ ሰማዕታት ተፈጸመ፤ መክስምያኖስና ዲዮቅልጥያኖስ ተጣሉ ደገኛ ንጉሥ ''ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ'' ነገሰ።

የከበረ መስቀል ዳግመኛ የተገለጠበት መጋቢት 10 ቀን ነው፤ ዜናውን በዚህ ዕለት ፅፈነዋል።

መስቀሉ የተገኘው በመጋቢት 10 ቀን ቢሆንም በታላቁ በዐቢይ ጾም ተድላ ደስታ ማድረግ በሥርዓተ ቤተክርስቲያን የተከለከለ በመሆኑ የመስቀሉን በዓል ማክበር የማይቻል ሆነ። በአበው ውሳኔም ቁፋሮው የተጀመረበትና ቅዳሴ ቤቱ የከበረበት መስከረም 17 በደስታና በተድላ እንዲከበር ተደረገ።

የቅድስት ዕሌኒ ባለቤቷ ተርቢኖስ ይባላል፤ በቅድስና ተፋቅረው ነበር የሚኖሩት፤ ተርቢኖስ የሚል ጽሁፍ ያለበት የአንገት ሀብል አሰርቶላት ነበር። ተርቢኖስ ነጋዴ ስለነበር ከጓደኞቹ ጋር በመርከብ ተሳፍረው እሩቅ አገር ሄደው ከ 3 ዓመት በኋላ ይመለሳሉ፤ታዲያ መርከብ ላይ እንዲህ እያሉ ይጫወታሉ፤ እኛስ በሰላም ወደ አገራችን ተመለስን ሚስቶቻችን ግን በሰላም ይጠብቁን ይሆን ሌላ ወንድ ወደውና ለምደው እንዳይጠብቁን አሉ፤ ተርቢኖስ ደግሞ የኔ ሚስት ዕሌኒ ከኔ ሌላ ማንንም አትወድም አትለምድም ይላቸዋል፤ ያንተ ሚስት ከሐዋን ሴቶች ትለያለችን እኔ ሄጄ ወድጃት ወዳኝ ለምጃት ለምዳኝ ብመጣ ምን ትሰጠኛለህ ይለዋል ንብረቴ ሁሉ ላንተ ይሁን ይለዋል በወረታቸው ተወራርደው ይሄዳል፤ የዕሌኒን ገረድ አስጠርቶ 20 ወቄት ወርቅ እሰጥሻለሁ ሁለቱ ብቻ የሚተዋወቁበትን አንድ ነገር ስጪኝ ይላታል፤ እርሷም እሺ አንተ ነጋዴዎች መጡ የብስ እረገጡ እያልክ ለፍፍ ትለዋለች፤ እንዳለችው እየዞረ ለፈፈ፤ ገረዲም ወደ ዕሌኒ ቀርባ እመቤቴ

ነጋዴዎች መጡ የብስ እረገጡ እየተባለ ነው ገላሽን ታጠቢ ሽቶም ተቀቢ ትላታለች፤ዕሌኒም የአንገት ሀብሏን አስቀምጣ ገላዋን ልትታጠብ ትገባለች ይህን ጊዜ ገረድዋ ወስዳ ትሰጠዋለች፤ እርሱም ተርቢኖስ ጋር ሄዶ እየው አፍቅራኝ ውድ ስጦታ ሰጠችኝ ብሎ ያሳየዋል፤ ሀብሉን ተመለከተው ተርቢኖስ የሚል ፅሁፍ አለበት አመነው፤ እያዘነ 3 ዓመት የደከመበትን ንብረት አስረክቦ እየተበሳጨ ወደ ቤቱ ገባ፤ምን ሆነሃል አለችው ንብረቴን ማእበል ወሰደብኝ አላት፤አትዘን አንተም እኔም ብዙ ወዳጆች አሉን ተበድረን ትነግዳለህ ትለዋለች፤ እርሱም በአሽሙር ልክ ነሽ ያንቺ ወዳጆች ብዙ ናቸው እኔ ግን ወዳጅ የለኝም ደግሞም ባበደርኩበት አገር ተበድሬ በከበርኩበት አገር ተዋርጄ አልኖርም ወደ ሌላ አገር እሄዳለሁ ይላታል፤ ባልና ሚስት አንድ አካል ናቸው ካንተ አልለይም ትለዋለች፤ በመርከብ ተሳፍረው ይሄዳሉ በህሩ መሀል ሲደርሱ ሀብሉን አውጥቶ ያሳያታል ስወድሽ ጠላሽኝ ሳምንሽ ካድሽኝ ይላታል፤ ልታስረዳው ሞከረች አላመናትም በብረት ሳጥን ውስጥ አድርጎ ሰራሽ ያውጣሽ ብሎ ከባህር ጣላት ቅዱስ ሚካኤል እየጠበቃት ሳጥኑ ተንሳፎ ሄዶ ባህር ዳርቻ ያርፋል አገሩ ሮም ነው ቆንስጣ የተባለ አገር ገዢ ሳጥኑን ሲከፍተው እጅግ የምታምር ሴት አገኘ፤የኢየሱስ እናት ማርያም የምትባይው አንቺ ነሽን ይላታል፤እኔ የእርሷ ገረድ ነኝ እንጂ እርሷን አይደለሁም፤ ጊዜ ያዋረደኝ ወቅት የጣለኝ ሴት ነኝ ትለዋለች፤ወደ ቤተመንግስቱ ይዟት ገባ፤ በክብር እስከ 6 ወር ጠበቃት ከዚያም አገባት በግብርም አወቃት፤መስከረም 12 ቆስጠንጢኖስ ተወለደ፤ በድብቅ የሃይማኖት ትምህርት አስተማረችው ምክንያቱም ባለቤቷ ጣኦት አምላኪ ነበርና፤ ልጇ በ 25 ዓመቱ በሮም ነገሰ ክርስትናንም ተቀበለ፤

ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ

በ272 ዓ.ም ሰርብያ ውስጥ አሕዛብ ከነበረው አባቱ ከቄንስጣና አይሁዳዊት ከነበረችው እናቱ እሌኒ የተወለደው ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በሮማ ነገሥታት በመክስምያኖስና በዲዮቅልጥያኖስ ስር የምስራቁ ክፍል በነበረው አካባቢ አገረ ገዥ ነበር። ዲዮቅልጥያኖስና መክስምያኖስ የተባሉት የሮማ ነገሥታት በክርስቲያኖች ላይ ሲያደርሱት የነበረው አሰቃቂ ግፍ ሲያሳዝነው ይኖር ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ''በዝንቱ ትእምርተ መስቀል ትመውእ ፀርከ=በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን መክስምያኖስን ድል ማድረግ ትችላለህ'' የሚል ራእይ በግሪክ ቋንቋ ተጽፎ በሰማይ ላይ ታየው። ወዲያውኑ በሠራዊቱ ትጥቅና መለዮ ልብስ ላይ የመስቀል ምልክት በማድረግ መክስምያኖስን በሮም አካባቢ በሚገኘው ትቤር ወንዝ ሚልብያን ከተባለው ድልድይ ላይ በ312 ዓ.ም ገጥሞ ድል አደረገው። ከዚያም በ313 ዓ.ም ሚላን ከምትባል ከተማ ላይ ሁኖ ለክርስቲያኖች የማምለክ ነፃነታቸውን በግዛቱ ሁሉ ያለምንም ፍርሐት እንዲፈጽሙ በአዋጅ አጸደቀላቸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ፥ ማለት እግዚአብሔር ወልድ ፍጡር እንጅ ፈጣሪ አይደለም ያለዉን የሊብያውን ተወላጅ አርዮስን ኒቂያ ላይ 318 ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን በ325 ዓ.ም ሰብስቦ አስወግዞ ከቤተክርስቲያን እንዲለይ አድርጎታል። በዚህ ጉባኤም የቤተክርስቲያን ዶግማና ቀኖና በግልጽ እንዲቀመጥ ተደርጓል። የጉባኤው መግለጫም ዛሬ በቅድዳሴ ጊዜ እምነታችንን የምናረጋግጥበት ''ጸሎተ ሐይማኖት'' ነው። እምነቱም ''ኦርቶ-ዶክስ=ቀጥተኛ እምነት'' እንዲባል ተወሰነ። (ፍትሐ

ነገሥትንና ሐይማኖት አበውን ይመልከቱ።)

ወደ አርስቱ ስንመለስ ፤ የኒቂያ ጉባኤ በተደረገ በ 2 ኛው ዓመት ማለት በ 327 ዓ.ም የቆስጠንጢኖስ እናት እሊኒ የክርስትናን እምነት ከተቀበለች በኋላ ብዙ ሠራዊት አስከትላ መስቀሉን ፍለጋ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘች። መድኅኒታችን ክርስቶስ የተሰቀለበት ክቡር መስቀል ብዙ ታምራትን እየሠራ አይሁድን ስላበሳጫቸው መስቀሉን ጉድጓድ አስቆፍረው እንዲቀበር ካደረጉ በኋላ የከተማው ቆሻሻ በዚያ ላይ እንዲጣልበት አድርገው ለ 294 ዓመት አቆይተውት ነበር። ይህም በመሆኑ መስቀሉ የት እንደተቀበረ ለማወቅ አስቸጋሪ ነበር። ብዙ የእድሜ ባለፀጋ የነበሩትን የአይሁድ ሽማግሌዎች እሌኒ እያስጠራች በመጠየቅ ብዙ ሙከራ አድርጋ ነበር። በመጨረሻ አንድ ኪርያኮስ የተባለ ሺማግሌ ''ከእኛ የቀደሙ አባቶች መስቀሉ ከዚህ አካባቢ እንደተቀበረ ሲናገሩ እሰማ ነበር ፥ ነገር ግን መቃብሩን ለይተው አላሳዩንም አላት። እሌኒም ራሱ ክርስቶስ እንዲገልጥላት ጸለየች። ክርስቶስም ልመናዋን ሰምቶ መላኩ ቅዱስ ራጉኤልን ላከላት። መላኩ ራጉኤልም በሺማግሌ አምሳል ቁሞ ደመራ ኣስደምራ ምህላና ጸሎት አድርጋ እጣን ጨምራ እንድታቃጥልና ጢሱ ሂዶ የሚያርፍበት ቦታ ላይ እንድታስቆፍር ነገራት። ንግሥት እሌኒም መላኩ እንዳዘዛት ደመራዉን መስከረም 16 ቀን 327 ዓ.ም አስደምራ በበነገው መስከረም 17 ቀን እንዲቃጠል አድርጋ ጢሱ ካረፈበት ቦታ ላይ ማስቆፈሩን ጀመረች። ቁፋሮው 6 ወር ፈጀቶ መጋቢት 10 ቀን መስቀሉ ከተቀበረበት ወጣ። ንግሥት እሌኒም ጎልጎታ ላይ ቤተክርስቲያን አሰርታ በክብር በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲቀመጥ አደረገች።

ይህ በሆነ ከ287 ዓመት በኋላ ፀሐይ አምላኪ የነበረው ቾስሮኤስ የተባለው የፋርስ ጀኔራል በ614 ዓ.ም ኢየሩሳሌምን ወሮ መስቀሉን ከሌላ ንብረት ጋር ማርኮ ወደ ሀጋሩ ወሰደው። 9 ዓመት በምርኮ ፋርስ ውስጥ ከቆየ በኋላ የቪዛንታዩኑ ንጉሥ ሕርቃል በ614 ዓ.ም ወደ ፋርስ ዘምቶ መስቀሉን እንደገና ማርኮ ወደነበረበት ቤተመቅደስ አስገባው። ሕርቃል ይህን በማድረጉ ለስሙና ለድርጊቱ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የቤተክርስቲያን አባቶች ከ40 ጾም ጋር አንድ ሳምንት ጨምረው የመጀመሪያውን ሳምንት ''ጾመ ሕርቃል'' ብለውታል።

ከ1374—1406 የኢትዮጵያ ንጉሥ በነበሩት በአፄ ዳዊት ዘመን መስከረም 10 ቀን መዳኅኒታችን ክርስቶስ ቀኝ እጁ የተቸነከረበት ግማደ መስቀሉ በግብጽ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ገባ። አፄ ዳዊት ከብዙ ሠራዊታቸው ጋር ሥናር (ሱዳን) ድረስ ሂደው ተቀበሉት። ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ሲዘዋወር ከቆየ በኋላ የአፄ ዳዊት ልጅ ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዘራያዕቆብ (1434—1468) ''አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል=መስቀሌን የመስቀል ምልክት ባለበት ቦታ ላይ አስቀምጥ '' የሚል ራዕይ ስላየ ግሸን ማርያም ላይ እንዲቀመጥ አድርጎታል። እስከዛሬ ድረስ በዚያው በግሸን ይገኛል።

በመስቀሉ ላዳነን ለእግዚአብሔርም ምስጋና ይሁን በመስቀሉ ሀይልም ሁላችን የክርስቲያን ወገኖች የተብቀን ለዘላለሙ አሜን።

Fere-Haymanot Sunday-school

15/ የመስቀል በዓል ክርስቲያናዊ አከባበር

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከምታከብራቸው ዘጠኙ የጌታችን ንዑሳን በዓላት አንዱ መስከረም 17 የሚከበረው የመስቀል በዓል ነው። መስቀል የሰላማችንና የድኅነታችን የመቀደሳችን አርማ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅች ለማዳን÷የዘላለም ሕይወትን ለመስጠት መስዋዕትነት የከፈለበት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ያፈሰሰበት መንበር÷ ሲሆን አምላካችንን የመንመለከትበት መስታወት ነው።

ይህ ዕለት ከ300 ዓመታት በላይ ጠፍቶ የነበረውን ቅዱስ መስቀል በንግሥት ዕሌኒ አማካኝነት መገኘቱን የምንዘክርበት በዚህም ደስ የምንሰኝበት ዕለት ነው። በዓሉ በምን ምክንያት እንደሚከበር ታሪኩን፣ በቅድሰት ቤተ ክርስቲያን ካህናቱና ምእመናን በአንድነት በመሆን እንዴት እንደሚያከብሩት፣ ምእመናን በየአካባቢያቸው በየቤታቸው እንዴት እንደሚያከብሩት ቀጥለን እንመልከት።

የቅዱስ መስቀሉ መዳፈን /መቀበር/ እና መገኘት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅችን ለማዳን የተሰቀለበት ቅዱስ መስቀል ሕሙማንን በመፈወሱ ምክንያት በርካታ አሕዛብ ክርስቲያን እንዲሆኑ አስችሏል። ይህን የተመለከቱ አይሁድ ቅዱስ መስቀሉን በአንድ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ እንዲቀበር አደረጉ። የአካባቢው ነዋሪዎች በየቀኑ

ቆሻሻ ስለሚጥሉበት ቦታው ወደተራራነት ተቀየረ። ምንም እንኳን መስቀሉን ለማውጣት ባይችሉም በኢየሩሳሌም የነበሩ ክርስቲያኖች ቦታውን ያውቁት ነበር። በሰባ ዓመተ ምሕረት በጥጦስ ወረራ ኢየሩሳሌም ስለጠፋች በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖች ተሰደዱ። የተቀበረበትን ቦታ የሚያውቅ ባለመገኘቱ መስቀሉ ከ 300 ዓመታት በላይ ተዳፍኖ /ተቀብሮ/ ኖሯል።

በ 326 ዓ.ም. የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት ዕሌኒ ቅዱስ መስቀሉን ለመፈለግ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ አደረገች። እዚያም ደርሳ ጉብታ የሆነውን ሁሉ ብታስቆፍር መስቀሉ ያለበትን ቦታ ማግኘት አልቻለችም፤ ሰውም ብትጠይቅ የሚያውቅ አልተገኘም። በመጨረሻም የመስቀሉ መገኘት የእግዚአብሔር ፈቀድ ነበርና አንድ ይሁድ(ኪራዮስ) የተባለ አረጋዊ አግኝታ ቅዱስ መስቀሉ የተቀበረበትን አካባቢ አመለከታት። ይህ ሰው በኋላ በክርስቶስ አምኖ ተጠምቋል፤ ስሙም ኪራኮስ ተብሏል።

ንግሥት ዕሌኒ ዕንጨት ደምራ በዚያ ላይ ዕጣን ጨምራ በእሳት ለኮሰችው፤ ቅዱስ ያሬድ በድጓው «ዘዕጣን አንጸረ ፣ሰገደ ጢስ» እንዳለ የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ወደ ታች ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በጣት ጠቅሶ እንደማሳየት ያህል በማመልከቱ። ንግሥት ዕሌኒም ጢሱ ያረፈበት ቦታ ቅዱስ መስቀሉ የተቀበረበት እንደሆነ አመነች።

በዚህም መሠረት ከመስከረም 17 ጀምሮ ሌሊትና ቀን የጉድፍን ኮረብታ ቆፍረው ካስወገዱ በኋላ ሦስት መስቀሎች የተገኙ ሲሆን። የጌታም መስቀል ሙት በማስነሣቱ ተለይቶ ታውቋል። መስቀሉ የተገኘው መጋቢት 10 ቀን 326 ዓ. ም. ነበር። ቅድስት ዕሌኒ ይህን ተአምር በማየቷ እጅግ ደስ አላት። ሕዝቡም ሁሉ መስቀሉን እየዳሰሱ ኪርያላይሶን እያሉም በመዘመር

ደስታና ሐሴት አደረጉ። ቀኑ መሸቶ ጨለማ በሆነ ጊዜም የኢየሩሳሌም ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስና ንግሥት ዕሌኒ፣ ሠራዊቱና ሕዝቡ በሰልፍ በችቦ መብራት መዝሙር እየዘመሩ ቅዱስ መስቀሉን ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደው በአንድ የጸሎት ቤት አኖሩት። በኋላም ለመሰቀሉ መታሰቢያ ቤተክርስቲያን ተሰርቶ ተመርቆ የገባው /ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው/ መስከረም 17 ቀን 326 ዓ. ም. ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ሁለቱም ዕለታት ይከበራሉ፤ በደማቅ ሁኔታና በመጀመሪያ ደረጃ የሚከበረው ግን መስከረም 17 ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት መጋቢት ዐሥር ቀን ሁልጊዜም በዐቢይ ጾም ወቅት የሚውል መሆኑና ለመስቀሉ የተሠራው ቤተ መቅደስ የከበረው መስከረም 17 መሆኑ ነው። ይህንንም ስንክሳር «የከበረ መሰቀልም ዳግመኛ የተገለጠበት መጋቢት ዐሥር ቀን ነው። ዜናውንም በዚሁ ቀን ጽፈናል። ምእመናንም በታላቁ ጾም መካከል በዓሉን ማክበር ስላልተቻላቸው በዓሉን ቤተ ክርስቲያኑ በከበረችበት ቀን አደረጉ። ይህም መስከረም 17 ቀን ነው። በዚህም ቀን አስቀድሞ ከከበረ መቃብር በንግሥት ዕሌኒ እጅ የተገለጠበት ነው» በማለት ያስረዳል።

ስንክሳሩ እንደሚገልጸው ክርስቲያን ሁሉ የትንሣኤውን በዓል በኢየሩሳሌም ተሰባስበው ያከብሩ እንደነበሩ ሁሉ የመስቀሉንም በዓል ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በአንድነት ያከብሩ ነበር።

በዓሉ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይከበራል?

ትልቁ የበዓል ማክበር ሥርዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ በቤተ ክርስቲያን መሰባሰብ ነው። ሊቃውንቱ በፍትሐ ነገሥት «ተጋብኡ ኩሎ ዕለት ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወፈድፋደሰ በዕለተ ሰንበት ወበበዓላት ወበዕለተ ትንሣኤ

ዘውእቱ ዕለተ እሑድ። ወናሁ ንሬእዮሙ ለአሕዛብ ከመ ኢይደኅሩ እምተጋብኦ በዕለተ በዓሎሙ፤ ሁልጊዜ በቤተ ክርስቲያን ተሰብሰቡ፤ ይልቁንም በዕለተ እሑድ፣ በዕለተ ቀዳሚት፣ በጌታ በዓላት ወደ ቤተ ክርስቲያን ተሰብሰቡ። እንኳን ክርስቲያን አሕዛብም በዓል በሚያደርጉበት ቀን ከመሰብሰብ ወደኋላ እንዳይሉ እነሆ እናያቸዋለን።» ያሉት ለዚህ ነው። /ፍትሐ ነገሥት ገጽ 254/ በዓሉን ማክበር የሚጀመረው በዋዜማው በመስከረም 16 ነው። ምእመናን ከየቤታቸው ዕንጨቱን ችቦውን ይዘው ለደመራ በተዘጋጀው ቦታ እያመጡ ይደምራሉ። ካህናቱ፣ ምእመናኑ ሁሉ በአንድነት ይሰበሰባሉ። ካህናቱም በደመራው ፊት ለፊት ጸሎት አድርሰው «መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሰርገዎ ሰማየ እምኩሉሰ ፀሐየ አርአየ» እያሉ ደመራውን ይዞራሉ ትርጉሙም «መስቀል በክዋክብት አበራ፤ ሰማይን አስጌጠ፤ከሁሉም በላይ ፀሐይን አሳየ» ማለት ነው። በገጠር ሕዝቡ ችቦውን በማብራት «ኢየሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ» እያለ ደስታውን ይገልጣል። በከተማ አካባቢ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስለ መስቀል የተዘመሩ መዝሙራትን በመዘመር እግዚአብሐርን ያመሰግናሉ።

ቅዱስ መስቀሉ በተገኘበት ዘመን የምሥራች ዜና ከቦታ ወደ ቦታ የሚሸጋገረው እሳት በማንደድ ስለነበር በዘመኑ የነበሩ ክርስቲያኖች ደስታቸውን የገለጡት፣ የምሥራቹንም እስከ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ያደረሱት ችቦ በማብራትና መዝሙር በመዘመር ስለሆነ ይህን ለመዘከር በመሸ ጊዜ ሕዝበ ክርስተያኑ በየደጁ ችቦውን እያበራ ደስታውን ሲገልጥ እግዚአብሔርንም በመዝሙር ሲያመሰግኑ ያመሻሉ።

በገጠሩ የሀገራችን ክፍል ደመራው የሚለኮሰው በ17 ጠዋት ሲሆን

በአዲስ አበባና በአካባቢው ግን ደመራው የሚለኮሰው ጸሎቱ እንዳለቀ ነው። ደመራው የተጸለየበትና የተባረከ ስለሆነ ሕዝቡ አመዱንና ትርኳሹን እየተሻማ ወደየቤቱ ይዛ ይሄዳል። አመዱን ቢቀቡት፣ ቢተሻሹት፣ በጥብጠው ቢጠጡት ይፈውሳል፤ ለከብት እንኳን ሳይቀር መድኃኒት ይሆናል። ባላገሩ ከብቱን ሁሉ በትርኳሹ ይተኩሳል ጤና እንዲሆንለት።

የበዓሉ ዕለት ምእመናን በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው የነግህ ጸሎት ያደርሳሉ። በዓላት በዚህ ምድር ሳለን ተድላ ነፍስ ተድላ ሥጋ ያለባትን፣ ፍጹም የሆነ ሰላም፣ ረፍት፣ ደስታ የምትሰጠውን መንግስተ ሰማያትን መቅመሻ ናቸው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይህን ከምትፈጽምባቸው ሕይወቶቿ ዋናው ቅዳሴ ነው። ስለዚህ ምእመናን በዚህ ዕለት ቅዳሴ አስቀድሰው ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ተቀብለው ደስ ብሏቸው በዓሉን ያከብሩታል። በዕለቱ የሚቀደሰው ቅዳሴ ስለ ነገር መስቀል አብዝቶ የሚናገረው ቅዳሴ ዘዮሐንስ አፈወረቅ ነው። በዚህ ቅዳሴ ከሚነበበው የነገረ መስቀል ንባብ መካከል ለመጥቀስ ያህል፦

«ኦ አዕዳው እለ ለሐኳሁ ለአዳም ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል፤ ኦ አእጋር እለ አንሶሰዋ ውስተ ገነት ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል፤ ኦ አፍ ዘነፍሐ ውስተ ገጹ ለአዳም መንፈስ ሕይወት ብሒዐ መጺጸ ዘምስለ ሐሞት ሰረበ፤አይ አፍ ወአይ ከናፍር ወአይ ልሳን ዘይትናገር ሕማማቲሁ ለወልድ፤ ልብ ይትከፈል ፣ወሕሊና ይዘበጥ ፣ወነፍስ ትርዕድ፣ ወሥጋ ይደክም ሶበ ይትነገር ሕማማቲሁ ለፍቁር፤አዳምን የፈጠሩ እጆች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ፣ ወዮ፤ በገነት የተመላለሱ እግሮች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ፣ ወዮ፤ በአዳም ፊት የሕይወት መንፈስን እፍ ያለ አፍ ከሐሞት ጋራ የተቀላቀለ መጻጻን

ጠጣ፣ ወዮ፤ የወልድን መከራውን የሚናገር ምን አፍ ነው፣ ምን ከንፈር ነው፤ ምን አንደበት ነው፤የፍቁር የጌታ ሕማማት በተነገረ ጊዜ ልብ ይለያል፤ ሕሊናም ይመታል፤ ነፍስም ትንቀጠቀጣለች፤ ሥጋም ይደክማል፣ /ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወረቅ/ በዋዜማው /በደመራ ዕለት/፣ በዕለቱ በጸሎተ ነግህ እና በጸሎተ ቅዳሴ የሚሰበኩት ምስባካት የሚከተሉት ናቸው።

«ወረከብናሁ ውስተ ዖመ ገዳም። ንበውዕ እንከሰ ውስተ አብያቲሁ ለእግዚአብሔር። ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ። በዱር ውስጥም አገኘነው፤ ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን፤ እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን» /መዝ. 131 6/ «ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ፤ ከመ ያምሥጡ እሞገጸ ቅስት፤ ወይድኅኑ ፍቁራኒከ ፤ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው፤ ወዳጆችህ እንዲድኑ» /መዝ. 59 4/ የሚነበቡት የወንጌልና የመልእክታት ክፍሎችም /ዮሐ. 19 25-28 ዮሐ. 3 14-22፣ ማቴ. 8 16-28፣ ሐዋ. 5 26-33 1ኛ ጢሞ. 5 9-16፣ያዕ 3፡11/ ፍጻሜ ናቸው።

ቅዳሴው፣ መዝሙራቱ፣ ምንባባቱ ስለ ቅዱስ መስቀል በርካታ ትምህርት ይሰጣሉ። እነዚህንም ነገሮች ቅዱስ ያሬድ «መስቀል በኩል ጊዜ፣ ወለኩሉ ሰዓት፤ መስቀል በጊዜው ሁሉና በሰዓቱ ሁሉ ነው» እንዳለው ስለ ቅዱስ መስቀል ዘወትር ስናስብ በተለይም ይህን በዓል ስናከብር እነዚህን ነገሮች እያሰብን ደስ ልንሰኝ እግዚአብሔርንም ልናመሰግን ይገባል።

መስቀል ብርሃን ነው

ጨለማ የተባለ ኃጢአትና ሞት በሞትም ላይ ሥልጣን ያለው የጨለማው

አበጋዝ ዲያብሎስ ድል የተነሳበት፤ ሥልጣኑ የተሻረበት በመሆኑ መስቀል ብርሃን ተብሏል። በጌታችን የመስቀል ሞት ብርሃን የተባለውን ሰማያዊ ሕይወት አግኝተናል። «ሕይወትም በእርሱ ነበረ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበር፤ ብርሃንም በጨለማ ያበራል፤ ጨለማም አላሸነፈውም።» እንዲል። /ዮሐ. 1 4-5/

ከዚህ በተጨማሪ የመስቀል ብርሃን መባል ከበዓሉ ጋር የተያያዘ ታሪካዊ ይዘትም አለው። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ከመክስምያኖስ ጋር በተዋጋ ጊዜ በሰማይ በፀሐዩ ብርሃን ላይ «በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን ድል ታደርጋለህ» የሚል የመስቀል ምልክት አየ። የመስቀል ምልክትን በፈረሱና በበቅሎ ልጓም፣ በጦር መሣሪያውና በጦር ልብሱ፣ በባንዲራው ላይ አድርጐ ጠላቱን አሸንፏል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ይህን ታሪክ መሠረት አድርጋ «መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሰርገው ሰማየ እምኩሉሰ ፀሐየ አርአያ» እያለች ትዘምራለች። በሌላም በኩል ቅዱስ መስቀል ከተዳፈነበት ቦታ መገኘቱና መታየቱ «መስቀል አበራ» አስብሎታል። ምክንያቱም ጨለማ መሰወር ፤ብርሃን ደግሞ መገለጥ ነውና።

መስቀል የድኅነት፣ የሰላም ምልክት ነው።

ጌታችን የፈጸማቸው የማዳን ሥራዎች ሁሉ ፍጻሜ መስቀል ነው። ራሱ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ «ሁሉ ተፈጸመ» ብሏል። /ዮሐ. 19፡30/ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ «መስቀል መልዕልተ ኩሉ ነገር፤ ያድኅነነ እምፀር መስቀል ከሁሉ በላይ ነው፤ ከጠላት /ዲያብሎስ/ ያድነናል»፣ «አድኅነ ሕዝቦ በመስቀሉ፣ ሕዝቡን በመስቀሉ አዳነ» በማለት ዘምሯል። ዲያብሎስ የመስቀል ምልክትን ይፈራል፤

በመስቀል ፊት መቆም አይችልም። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በጦር ሠራዊቱና በጦር መሣሪያዎቹ ሁሉ ላይ የመስቀል ምልክት አድርጎ በመክስምያኖስ ላይ ያደረ ርኩስ መንፈስን በማራቁ አላዊውን ንጉሥ በቀላሉ መሸነፍ ችሏል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያን ነገሥታት በዘውዳቸው ላይ፣ በጦር መሣሪያዎቻቸው ላይ የመስቀሉን ምልክት ይጠቀሙበታል። ምእመናን የመስቀል ምልክትን በሰውነታቸው ላይ በተለያየ ቦታ ይነቀሱታል፤ ልቡናቸውን ይባርክ ዘንድ በደረታቸው ላይ ያንጠለጥለታል፤ በደነገጡ፣ የሕሊና ሰላም ባጡ ጊዜ ቅዱስ ያሬድ «መስቀል ትእምርተ ሰላምነ፤ መስቀል የሰላማችን ምልክት ነው።» እንዳለ በትእምርተ መስቀል አማትበው የሰላም ፀር የሆነውን ዲያብሎስን ያርቁበታል።

ታዲያ ይህ የሚሆነው፣ ትእምርተ መስቀል የተሰጠው እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ለወዳጆቹ ነው እንጂ እንዲያው ዝም ብለው ለጌጥ ለሚያንጠለጥሉት አይደለም። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ «ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ፤ ከመ ያምሥጡ እምገጸ ቅስት፤ ወይድኅኑ ፍቁራኒከ። ለሚፈሩህ ምልክትን /መስቀል/ ሰጠሃቸው ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ። ወዳጆችህም እንዲድኑ።» እንዳለ። /መዝ. 59 4-5/ ለሚፈሩህና ለመዳጆችህ አለ እንጂ ለሁሉም አላለም።

ስለዚህ ዘወትር በጸሎታችን «መስቀል ኃይልነ፣ መስቀል ጽንዕነ፣ መስቀል ቤዛነ፣ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ። አይሁድ ክሕዱ ንሕነሰ አመነ ወእለ አመነ በኃይለ መሰቀሉ ድኅነ።» እንላለን። በእያንዳንዷ ዕለታዊ ሕይወታችን።

የመስቀል ምልክትን እንጠቀማለን፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ከጉልላቷ

በላይ መስቀል ታደርጋለች፤ በቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች በርና መስኮት ላይም የመስቀል ምልክት ታደርጋለች። እነዚህ ነገሮች አሁን የመጡ ሳይሆን ሐዋርያት «እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን።» ፣ «ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ» /1 ቆሮ. 1፡23፣ገላ. 6፡14/ እያሉ መስቀል የሞት ምልክት ሳይሆን የድኅነት ምልክት መሆኑን ካስተማሩ በኋላ የተጀመረ ነው። ከሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስከ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የኖረው ጠረጡለስ በዘመኑ ክርስቲያኖች በመስቀል እንዴት ይጠቀሙ እንደ ነበር የሚከተለውን ተናግሮአል። «በተግባራችን ሁሉ በምንገባበትና በምንወጣበት ጊዜ፣ ልብሶቻችንን ከመልበሳችን በፊት፣ ከመታጠባችን በፊት፣ በቀንና በማታ ወደ ምግብ ገበታ በምንቀርብበት ጊዜ፣ ማታ መብራታችንን በምናበራበት ጊዜ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ በምንጀምርበትና በምንፈጽምበት ጊዜ፣ በዕለታዊ ሕይወታችን መደበኛ ሥራችንን በምንጀምርበት ጊዜ በትእምርተ መስቀል ፊታችንን እና መላ ሰውነታችንን እናማትባለን።»

መስቀል አንድ የሆንበት ነው

ቅዱስ ጳውሎስ «እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በእርሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእረሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው። መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን

የምስራች ብሎ ሰበከ በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና።» /ኤፌ. 2 14-18/

ብሎ እንዳስተማረ በቅዱስ መስቀል እግዚአብሔርና ሰው ታርቀዋል፤ ህዝብና አህዛብ አንድ ሆነዋል። በዚህ ምክንያት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን ሰብስባ በጸሎት፣ በመዝሙር ይልቁንም የአንድነት መገለጫ በሆነው በጸሎተ ቅዳሴ ታከብረዋለች። ምእመናንም በአንድነት ሆነው አብረው በመብላት ፤አብረው በመጠጣት በዓሉን ያከብሩታል። ምግበሥጋ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። በልተን ጠጥተን በሕይወት እንድንኖር እግዚአብሔርንም እንድናመሰግን አምላካችን መብልና መጠጥን ሕይወት አድርጎ ሰጥቶናል። በበዓላትም ተድላ ሥጋ ማድረግ የተገባ ስለሆነ ምእመናን አብሮ በመብላትና በመጠጣት ያከብሩታል። ይህ ሲባል ግን አብዝቶ በመብላትና በመጠጣት ከእግዚአብሔር ተለይቶ የሥጋን መሻት፤ የዓይንን አምሮት ለመፈጸም እስክንደርስ መሆን የለበትም። ይልቁንም የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት መንፈሳዊ ደስታን በመደሰት በዓሉን ማሳለፍ ይገባናል።

ማጠቃለያ

ስለ ቅዱስ መስቀል እነዚህን ለምሳሌ ያህል ጠቀስን እንጂ የነገረ መስቀል ትምህርት በዚህ የሚወሰን አይደለም። በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የዘመን አቆጣጠር ከመስከረም 17-25 ያለው ጊዜ ዘመነ መስቀል ይባላል። በዚህ ጊዜ ነገረ መስቀል ይነገራል፤ መዝሙረ መስቀል ይዘምራል። ምእመናን በዚህ ጊዜ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በመገኘት ነገረ መስቀሉን ልንሰማ እግዚአብሔርንም በመዝሙር ልናመሰግን ይገባል። ከቤተ ክርስቲያን

ሊቃውንት አንዱ የነበሩት መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ስለ ቅዱስ መስቀል ያስተማሩትን ትምህርት ጠቅሰን ጽሑፋችንን እናጠቃልላለን።

«ቅዱስ መስቀል በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሁሉ በሁሉ ነው። ቅዱስ መስቀል የወንጌል መሠረትና ልብ ነው። ቅዱስ መስቀል በቤተ ክርስቲያን ከቀረ የወንጌል ፍሬ ነገር ቀረ ማለት ነው። የመስቀሉ ነገር በብዙዎች ዘንድ የጥበብ ተቃራኒ የሆነ ሞኝነትን መስሎ መሰናክል ሆኗል። ለሚያምኑት ግን የእግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ ነው። ዓለም በጥበቡና በዕውቀቱ፣ በኀይሉም አልዳነም። ምክንያቱም እግዚአብሔር የዓለምን ኀይል፣ ጥበብና ዕውቀት ሞኝነት በመሰለው በመስቀል ነገር ከንቱ አድርጎታል። ስለሆነም በድካምና በሞኝነት ማለት በመስቀል ስብከትና በእምነት ዓለምን ለማዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኗል። ስለ መስቀልና በመስቀል ስለተሰቀለው ክርስቶስ መሰበክ በማያምኑት ዘንድ ሞኝነት፣ ድካምና መሰናክል ቢመስልም በምእመናን ዘንድ ግን የእግዚአብሔር ኀይል ሆኖ ይታያል። ምክንያቱም በሰው ዘንድ ሞኝነት ሆኖ የታየው የእግዚአብሔር ሥራ ከሰው ጥበብ ይልቅ ስለሚጠበብ ነው። በሰው ዘንድ ድካም ሆኖ የታየው የእግዚአብሔር ሥራም ከሰው ኀይል ይልቅ ስለሚበረታ ነው። እንግዲህ ቅዱስ መስቀል በሚያምኑና በማያምኑ መካከል መለያ ምልክት ነው፤ መለኪያ ሚዛንም ነው። ለእኛ ለምናምን ቅዱስ መስቀል ወደ ሰማይ የምንደርስበት መሰላል ነው። ለማያምኑ ግን ወደ ሰማይ እንዳይደርሱ የሚሰናከሉበት እንቅፋት ነው።

በክርስቶስ አምናለሁ የሚል ሁሉ እንደ አይሁድ «መስቀሉን አይግፉ» ነገር ግን እንደ ቅድስት ዕሌኒ መስቀሉን ይፈልግ፤ መስቀል ከሁሉ ነገር በላይ ነውና።»

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

የባ/ዳር ካቴድራል መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ሰ/ት/ቤት ገጽ ፔጁን ላይክ በማድረግ መንፈሳዊ እውቀትዎን ያጎልብቱ

16/ (<u>በመስቀል ዙሪያ የሚነሡ ጥያቄዎች)፤ መስቀሉን ስታከብሩ የተሰቀለውን ለምን ትረሳላችሁ?</u>

+++++++ከህሊና በለጠ ተግፊ

ጥያቄ፡- ብዙ ኦርቶዶክሳዊያን የመስቀል ቅርጽ በጣታቸው በማማተብ ወይም የተቀረጸ መስቀልን በአንገታቸው በማድረግ ሲያከብሩት እናያለን። ይህ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ አይደለም። ይህን ማድረግ ታዲያ ለምን ያስፈልጋል? ትእምርተ መስቀል ክርስቶስን የሚያስረሳ በእርሱም ፋንታ እያከበራችሁት ይመስለኛል፤ ይህ ለምን ይሆናል?

በክብረ መስቀል፤ በበዓሉ እና በማዕተብ ዙሪያ በርካታ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። እንደዚኽኛው ጥያቄም የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓተ አምልኮ በመንቀፍ ክርስቶስን የዘነጋች አድርገው የሚያቀርቡም ብዙዎች ናቸው። ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን በበዓለ መስቀል፤ በክብረ መስቀልና በማዕተብ ዙሪያ ለሚነሱት ጥያቄዎች

ከላይ የተጠቀሰውን ጥያቄ በመለሰበት ጽሑፉ በሐመር መጽሔት 18 ኛ ዓመት ቁጥር 6፤ የመስከረም 2003 ዓ.ም. የመስቀል በዓል ልዩ ጎትም ላይ እንደሚከተለው ምላሽ ሰጥቷል።

...ትእምርተ መስቀል ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ የሰው ልጆችን ማዳኑን የምናስብበት ምልክት ነው። ክርስቶስን ማሰብ ደግሞ የሚገባ ነው። ራሱ ጌታችን ይህንን ባደረጋችሁ ጊዜ ሞቴን መከራዬን ታስባላችሁ ብሎናል። እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙሩን ጢሞቴዎስን “በወንጌል እንደምሰብከው ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን ከዳዊት ዘር የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስበው” ብሎታል። /2 ጢሞ. 2፡8/። ክርስቶስን ደግሞ በነገር ሁሉ ማሰብ የሚገባ ነው። ለእርሱ ምስጋና ይግባውና እርሱ ከተናገረው ካደረገውም ስለሰው ልጆችም ከሆነውም ሁሉ እርሱ ደስ ለማይሰኝባቸው ነገሮች ምልክት የሆኑ ነገሮች የሉም። ከተናገረው፤ ካደረገውም በላይ ስለኛ የሆነው፤ ይልቁንም ስለኛ የተቀበለው መከራ፤ ውርደትና ሞት ግን ዋጋው ከምንም በላይ ነው። ይህ ለእርሱ ጥበቡም ኃይሉም ፍቅሩም ትሕትናውም የተገለጠበት ነው። “ስለወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ያለ እንደሆነ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር የለም።” /ዮሐ. 15፡13/ ብሎ ጌታችን እንደተናገረ እኛ ወዳጆቹ ሳይሆን ጠላቶቹ ሆነን ሳለ ስለኛ ቤዛ አድርጎ ራሱን

ያቀረበበት የመስቀል ሞት ከምንም በላይ የክርስትና
ሕይወት መሠረት ነው።
የሃይማኖታችን ማእከል ደግሞ እርሱ ከሆነ ምልክታችንም
ያንን የሚያስታውሰን የመስቀል ምልክት ሊሆን
እንደሚገባው ቤተ ክርስቲያን ታምናለች። ክርስቶስንና
የማዳን ሥራውን የምናስታውስበት ምልክት ደግሞ
የቤተክርስቲያንም ምልክት ነው። እሱ ጌታዋ፤ ራሷ፤ እረኛዋ፤
ተስፋዋ፤ ጠባቂዋ ኃይሏ ነውና።
መስቀል ክርስቶስንና ክርስቶስ ለሰዎች ያደረገውን የፍቅር
ሥራ ከማስታወሱም ሌላ የምንማርበት፤ የምናስተምርበት
ነው። በትእምርተ መስቀል የተሰፋውን ቃል /በነቢያት
የተነገረውን ትንቢት፤ የተመሰለውን ምሳሌ/ መፈጸሙን፤
የክርስቶስን የማዳን ጥበብና ምስጢር የምናስተምርበት
ነው።
ትእምርተ መስቀል ጥሪም ነው። ክርስቲያኖች ክርስቶስን
በማመን በክርስቶስ ስም ስለ እውነት መከራን መቀበልን
ሳይሰቀቁ በጽናት እንዲቆሙ የሚቀርብ የሃይማኖት ጥሪ
ነው።
ትእምርተ መስቀል ምስክርነትም ነው። ጌታችን ለሐዋርያቱ
“ምስክሮቼ ትሆናላችሁ” እንዳለ በትእምርተ መስቀልም
የሰማዕትነት /የምስክርነት/ ተግባርን እንፈጽማለን።
ምስክርነት ደግሞ ከፍተኛው ሐዋርያዊ አገልግሎት ነው።

በመሆኑም ክርስቲያኖች በካዱ በአይሁድ ፊት፤ በማያምኑም አረማውያን ፊት በክርስቶስ መስቀል፥ ሞትና ትንሣኤ እንደማያፍሩበት ይመሰክራሉ። ይህ ደግሞ ያለማፈር እንድንፈጽመው ጌታችን “በሰው ፊት የሚመሰክርልኝን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መላእክቱ ፊት ይመሰክርለታል።” ብሎ የተናገረን ተግባር እንጂ የግብዝነት አካሔድ አይደለም /ሉቃ. 10፥28/። በተለይ በዘመነ ሐዋርያት አይሁድ “እኛ ገርፈን በሰቀልነው ያምናሉ” እያሉ ይዘብቱ ስለነበር፤ “እርሱ ሞቷል እንጂ አልተነሣም” የሚሉ፤ መስቀሉንም “እርሱ የተዋረደበት መቅጫ ነው” የሚሉ፤ እርሱን ዙፋን አድርጎ የሰው ልጆችን ሁሉ ያዳነበት መሆኑን የማያምኑ፤ “በሞት ሞት አይሸነፍም” የሚሉ ዘባኞችና መስተሳልቃን ስለነበሩ የክርስቶስን መከራና ሞት ማሰብ፤ በዚያም መዳናችንን ማመን ሞኝነት የሚመስላቸው ነበሩ። በዚያ የጸኑ ክርስቲያኖችንም ያሳድዱ ነበር። ስለዚህ በመስቀሉ ስላገኘነው ሕይወት በግልጽ መመስከር አስፈላጊ ነው። ለዚያም ነው ቅዱስ ጳውሎስ “የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው” ያለው /1 ቆሮ 1፥18/። በዚህ ቃሉ መሠረት ስለ ነገረ መስቀሉ መመስከር የሰማዕትነት ፍጻሜ ነበር። ስለዚህ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ያላቸውን ፍጹም ፍቅር አይሁድና ተረፈ አይሁድ የሚጠሉትን፤ ነገረ መስቀሉን በሰዎች ሁሉ ፊት

ሳናፍር ልንመሰክር የምንችልበትን ትእምርተ መስቀል መጠቀማቸው የሚያስነቅፍ ሊሆን አይችልም። ለዚህም ነው የዓለም ክርስቲያኖች ከዕፅ ወይም ከወርቅ ወይም ከብር የመስቀል ቅርጽ ሠርተው ክርስቶስን በማያምኑ ወገኖች ፊት የሚቆሙት።

በተለይ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሁሉም ሊያየው በሚችል መልክ መስቀልን በአንገታቸው በማንጠልጠል፤ በግንባርና በእጆቻቸው በመነቀስ፤ በልብሶቻቸው ላይ በመጥለፍ፤ በጣቶቻቸውም በማማተብ፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶ አድኖናል፤ በዚያም አድኖናል እያሉ በምስክርነት ሕይወት ውስጥ ጸንተው የምናገኛቸው። በተናጠል ብቻ ሳይሆን በጋራም ደመራን በመሰሉ የመስቀል በዓላት እንደ ሐዋርያው "አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርቶስን እንሰብካለን" እያሉ በአደባባይ ያከብራሉ /1 ቆሮ. 1፡22/። ስለዚህ ትእምርተ መስቀልም ይሁን የመስቀል በዓላት ለዚህ አይነት ሃይማኖታዊ ዓላማ ሚና ያላቸው በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም ማለት አይቻልም። ትእምርትን ወይም ምልክትን መጠቀምም በራሱ የሚያስነቅፍ አይደለም። ምልክትን ለመታሰቢያም ለምስክርነትም የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲጠቀም እንደኖረ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ እናገኛለን። "ኢያሱ ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው ከእስራኤል

ልጆች የታወቁትን በሥራ ሁለት ሰዎች ጠራ። ኢያሱም
አላቸው በኔና በእግዚአብሔር ፊት ወደ ዮርዳኖስ መካከል
ዕለፉ፤ እያንዳንዱ ሰው በዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ቁጥር
በትከሻው ላይ አንድ አንድ ድንጋይ ከዚያ ይሸከም፤ እነዚህ
ምልክት ይሆኑላችኋል፤ ልጅህ ነገ እነዚህ ድንጋዮች
ምንድናቸው ብሎ በጠየቀህ ጊዜ ልጅህን እንዲህ ትለዋለህ፤
አንተ በምድር ሁሉ ጌታ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት
ፊት ስንሻገር የዮርዳኖስ ወንዝ ስለደረቀ ነው፤ እነዚህ
ድንጋዮች ለእስራኤል ልጆች ለዘላለም መታሰቢያ ይሆናሉ”
የሚል ቃል ተጽፏል /ኢያ. 4፡4/። ይህ ምልት
የእግዚአብሔርን ሥራና ክብር ያስታውሳል እንጂ ሊያስረሳ
የሚችልበት ምንም እድል የለም። እስራኤል ዮርዳኖስን
የተሸገሩበት የምስክርነት ምልክት እንዲህ ዋጋ ካለው እኛ
ከባሕረ እሳት ወደ ቀደመ ርስታችን ገነት መንግሥተ ሰማያት
የተሸገርንበት የክርስቶስ መስቀል ምልክትማ ምን ያህል
ዋጋና ክብር ይኖረው!
በኢያሪኮ ስለነበረችው ረዓብም ስናስብ “እኔ ለእናንተ ቸርነት
እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ለአባቴ ቤት ቸርነት እንድታደርጉ
በእውነት ምልክት ስጡኝ” ማለቷን በመጽሐፍ ተጽፎ
እናነባለን። ኢያሱ የላካቸው ጎልማሶችም “እነሆ እኛ ወደ
ሀገሩ በገባን ጊዜ ሀን ቀይ ፈትል እኛን ባወረድሽበት መስኮት
በኩል እሰሪው” ብለዋት ነበር። “ኢያሱም ምድሪቱን የሰለሉ

ሁለቱን ሰዎች ወደ ዘማይቱ ቤት ግቡ፤ ከዚያም ሴቲቱንና ያላትን ሁሉ እንደማላችሁላት አውጡ” አላቸው /ኢያ. 2፡ 12/። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለረዓብ የሰጣት ምልክት እርሷንና ያላትንም ሁሉ ለማዳን የበቃ እንደሆነ ካየን ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ምልክትማ ምእመናንን አንድ በማድረግ ድኅነታችንንም ለማሰብ፤ እንዴት የከበረ አይሆን! በታሪክ እንደሚታወቀው ከንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመን በፊት ክርስቲያኖች የመስቀልን ምልክት ማሳየት ወይም መጠቀም አይፈቀድላቸውም ነበር። ያንን ሲያደርግ የተገኘም በመስቀል ተሰቅሎ ይቀጣ ነበር። እስከዚያም ዘመን ድረስ መስቀል መቅጫ ሆኖ ያገለግል ነበር። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን ከሆነበት እ.ኤ.አ. ከ 337 ዓ.ም. ጀምሮ ግን ክርስቲያኖች የመስቀልን ምልክት በግልጽ ለምስክርነት የመጠቀም ነፃነት አግኝተዋል። ከዚያን ጊዜም ጀምሮ መስቀል የመቅጫ መሣሪያ መሆኑ ቀረ። በመሆኑም ቅዱስ ጳውሎስ “ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ” የሚለውን ቃሉን እያሰቡ ትእምርተ መስቀልን ያለፍርሃት፤ ያለ ሐፍረት ይጠቀማሉ / ገላ. 6፡14/።

ትእምርት ሐሳብን፤ ድርጊትን፤ ፈቃድን የሚያሳይ የሚመሰክር ነው። በወንጌል እንዲሁም ጌታችን ለፍርድ ወደዚህ ዓለም

ሲመጣ “የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል” ተብሎ ተጽፏል /ማቴ. 24፡30/። ሊቃውንት የሰው ልጅ ምልክት የተባለው መስቀል እንደሆነ ያስተምራሉ። በመሆኑም ትእምርተ መስቀል ክርስቶስ ለሰዎች የሠራውን መልካም ነገር የሚያስታውስ እንጂ የሚያስረሳ የሚሆንበት ምንም እድል የለም።

መስቀል መከበርም ይገባዋል። የመስቀሉን ምልክት ሰዎች ሲያዩ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልንን የፍቅር ሥራ በሚያዩት ሰዎች ልብ ስለሚሥል ክፉን ሐሳብ ለማራቅ መልካሙንም ለማድረግ ኃይል ይሆናል። ርኩሳን መናፍስትም የዲያቢሎስ ሥልጣኔ የተሻረው ክርስቶስ በመስቀሉ ለሰዎች በሠራው ሥራ መሆኑን ስለሚያውቁ ባዩት ቁጥር ይሸሻሉ፤ ይሸነፋሉ፤ ይቃጠላሉም። ያንን በሚያሳዩ በዚያም በሚመሰክሩ ምእመናን ልቡና ያለው በክርስቶስ የማመን ሐሳብ በእነርሱ ፊት ኃይልን ያደርጋል። ለዚህም ነው “መስቀል ኃይላችን ነው፤ መስቀል መጽናኛችን ነው፤ መስቀል ቤዛችን ነው፤ መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው፤ አይሁድ ይክዱታል እኛ ግን እናምነዋለን” የምንለው። የምናምነውም ኃይል አድርጓል ያደርጋልም። ክርስቶስ ከተሰቀለበት ሌላ የከበረ መስቀል የለም። ስለዚህ መስቀል የተሰቀለውን ክርስቶስን ያሳስበናል እንጂ ሊያስረሳ የሚችልበት መንገድ የለም።

ትእምርተ መስቀል ክርስቶስ ከመሰቀሉም ቀድሞ ኃይልና

በረከትን አባቶች ይሰጡበት የነበረ፤ እግዚአብሔርም በዚያ ትእምርት ላይ አድሮ ሲባርክና ኃይልን ሲሰጥ ነበር። ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች በባረከ ጊዜ ያደረገውን ማስታዎስ ይቻላል። “እስራኤልም ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረው፤ እርሱም ታናሽ ነበረ፤ ግራውንም በምናሴ ራስ ላይ አኖረ፤ እጆቹንም አስተላለፈ /አመሳቀለ/” ተብሎ ተጽፏል። / ዘፍ.48፡13/። ሌላም ተጨማሪ ቃል እንይ፤ ክርስቶስ እጆቹን ዘርግቶ በተሰቀለበት መስቀል አምሳል ወይም ምልክት ሊቀ ነቢያት ሙሴ የእስራኤልን ጠላቶች ድል ያደርግ ነበር። ስለዚህም መጽሐፍ እንዲህ ይላል፣ “ሙሴ እጁን ባነሣ ጊዜ እስራኤል ድል ያደርግ ነበር፤ እጁንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር፤ የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር... አሮንና ሖርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር፤ ፀሐይም እስክትገባ ድረስ እጆቹ ተዘርግተው ነበር” በዚህ ጊዜም ህ ትእምርት ኃይል ነበር። ጠላት የተባለ አማሌቅን ድል አድርጎበት ነበርና /ዘጸ. 10፡7-11/። ያለሐርና አሮን ድጋፍ ብቻውን እጆቹን ዘርግቶ፤ ስለ እስራኤል ብቻ ሳይሆን ስለዓለም ለተሰቀለውና ጠላት የተባለ የዲያቢሎስን ኃይልና ሥልጣን ለሻረበት የክርስቶስ መስቀል ምሳሌ ብቻ ሳይሆን የትእምርቱን ኃይልም የሚመሰክር ነው። ያ ትእምርት እንደዛ ኃይልና ክብር ካለው የክርስቶስ መስቀል ምልክትማ ምን ያህል ይከብር! ምንስ ያህል ኃይልን

ያደርግ! የሙሴን ትእምርት አሮንና ሐር እንደዚያ
ከተሸከሙት የክርስቶስን መስቀል ምልክትማ ካህናትና
ምእመናን በጠላት ፊት ሊሸከሙት እንዴት አይገባ! በመጽሐፍ
“ከባላጋራችን የተነሣ በትእዛዝ የተጻፈውን የእዳችንን ደብዳቤ
ደመሰሰልን፤ ከመካከላችንም አራቀው፤ በመስቀሉም
ቸነከረው” እንዲል የክርስቶስ መስቀል ጠላት ዲያቢሎስ
በእውነት የተሸነፈበት ጥበብና ኃይሉ ነውና /ቆላ 2፡14/።
ሙሴ በሰውነቱ የሠራው ትእምርት በጠላቶቹ ፊት ኃይልን
እንዳደረገለት ለሚያምኑት ሁሉ ከጠላት ፍላጻ ይድኑ ዘንድ
ኃይል የሚሆን ምልክትን እንደሚሰጣቸው ክቡር ዳዊት
“ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን
ሰጠሀቸው” ሲል ተናግሯል /መዝ. 59፡4/። እርሱም
የክርስቶስ የመስቀሉ ምልክት ነው። ያም የሰው ልጅ
ምልክት ተብሎ በወንጌል የተጠቀሰው ነው /ማቴ. 24፡
30/። ስለዚህ የክርስቶስ በሆኑት ነገሮች ሁሉ እንደምንባረክ፤
ኃይልም እንደምናገኝ እናምናለን። ክርስቶስን ከመስቀሉ፤
ክርስቶስን ከእናቱ፤ ክርስቶስን ከነብያቱ ከሐዋርያቱ፤ ወዘተ
ነጥሎ ማሰብ እንደሚገባ ቤተ ክርስቲያን ነጥላ ልታስተምር
አትችልም። ይሄ የእምነትም ጉዳይ ነው። ሃይማኖታችን
ከተራ ፍልስፍና የጸዳ ሊሆን ይገባዋል።
በሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት ልብሱን
ብቻ የዳሰሰሁ እንደሆነ እድናለሁ ማለቷን እናስተውል /ማር.

5፡8/። ይህቺ ሴት ያላትን እምነት እናስብ፡ “ክርስቶስ እጆቹን ጭኖብኝ፡ እግሮቹን ዳስሼ” አላለችም፤ “ልብሱን ብቻ” አለች እንጂ። ልብሱ የክርስቶስ ነውና። እርሱ/አካሉ/ ካልሆነ ኃይልን በእምነት አናገኝም አይባልም። “አካሉን እንጂ ጥላውን አልፈልግም፤ አካሉን እንጂ ልብሱን አልፈልግም፤ የተሰቀለውን እንጂ መስቀሉን አልፈልግም፤ ወልድን እንጂ ወላዲቱን አልፈልግም...” ወዘተ አላለችም። እነዚህ ሁሉ የእርሱ ስለሆኑ ይከብራሉ። ከእርሱም የተነሣ በጸጋ የከበሩ መሆናቸውን እንደዚያች ሴት እናምናለን። ከዚህ በወጣ ለዓለም በሚመች ከንቱ መለፍለፍ ልባችን መድከም አይገባውም። ለምናምን ሰዎች የክርስቶስ በሆነው ነገር ሁሉ በረከት ኃይል እንደምናገኝ እናምናለን። ይህ ማለት የእርሱ የሆኑት ሁሉ እርሱን ናቸው ማለት አይደለም። የእርሱ የሆኑት ግን ከእርሱ የተነሣ የከበሩ መሆናቸውን እናምናለን። አስቀድሞም በትንቢት ስለእርሱ ብቻ ሳይሆን ከእርሱ የተነሣ ስለሚከብሩ ሁሉ ተናግሯል። ስለለበሳቸው ልብሶች እንኳን “ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፡ በቀሚሴም ላይ እጣ ተጣጣሉ” /መዝ.21፡18/ ማለቱን እናነባለን። የተሰቀለበት መስቀልና የመስቀሉ ምልክትም እርሱን የሚያሳይና ስለእርሱ የምንመሰክርበት በመሆኑ የከበረ ነው። አንዳንዶቹ የምታከብሩት ክርስቶስ የተሰቀለበትን ዋናውን መስቀል ሳይሆን ክፋውም ደጉም ሰው የቀረጸውን ምልክቱን

በመሆኑ አግባብ አይደለም ሲሉ ይሰማሉ። ለዚህ ግን ብዙ
ሳንል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኖዳ ሣልሳዊ ክሌዎፓ ዘሩማኒያ
የተባሉ ክርስቲያን በአንድ ወቅት ለዚህ ዓይነት ጥያቄ
የሰጡትን መልስ ይህንን ጥያቄ ላነሡላቸው ወገኖች መልስ
ሲሰጡ የጠቀሱትን ንግግር በዚህ አጋጣሚ እናንሣው፤
ክሌዎፓ ዘሩማኒያ እንዲህ ብለው ነበር “ይህንን በቅዱሳት
መጻሕፍትም ዘንድ እናደርገዋለን፤ በዛሬ ዘመን ቆጥረን
የማንጨርሳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች በዓለም ላይ
አሉን፤ በእናንተ ሐሳብ ከሆነ እነዚህን በክፉዎችም በደጎችም
ማተሚያ ቤቶች ወይም አሳታሚዎች ታትመው የሚሰራጩ
ቅጂዎች በመሆናቸው ማክበር የለብንም ማለት ነው፤
ዋናውን /በነብያት በሐዋርያት እጅ የተጻፉ/ ቅጂ ብቻ
መያዙ /እርሱን ብቻ ማክበር፤ በዚያም ብቻ መባረክ/ አለብን
ማለት ነው። ስለዚህ የቀረበው ይህ አስተሳሰብ ግን
ለምክንያታዊ ሰው የሚያሳምን አይደለም” ብለው ነበር።
በመሆኑም ጠያቂያችን በትእምርተ መስቀል ላይ
ኦርቶዶክሳውያን ያለን እምነት ከላይ ከጠቀስናቸው
የመጻሕፍት ምስጢር የተገኙ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ የሠራልንን የፍቅር ሥራ /ነገረ ድኅነት/ ወይም
ወንጌልን የምንመሰክርበት የምናስተምርበት በዚያም ኃይል
የምናገኝበት በመሆኑ መጽሐፋዊ መሠረት ያለውና
ክርስቶስንም በማሰብ የሚያጸና ነው።

Long Life to Memhir Girma

17/ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል መሬት ላይ ሊረገጥ አይገባም!!!

"ስለ ክርስቶስ መስቀል የሚመለከተው ሁሉ ሼር ያድርግ"

መስቀል የእግዚያብሔር ታላቅ ሀይሉ የተገለፀበት ዲያብሎስን ያዋረደበት መእምናንን የታደገበት የሰላም ዙፋን ከመሆኑም በላይ በዕለተ አርብ ቅዱስ ስጋው የዋለበት፣ካሳ የተከፈለበት፣ወርቅ ደሙ የፈሰሰበት ስለሆነ እናከብረዋለን። እንሳለመዋለን፣ እንመካበታለን። የፀጋ ስግደት እንሰግድለታለን።

ሆኖም ግን ይህን ክቡርና ቅዱስ መስቀል አምሳል የያዘ የመሬት ምንጣፍ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ውስጥ ሀገርን እንመራለን ህዝብን እናስተዳድራለን ከሚሉት ባለስልጣን የቢሮ ወለል ላይ ተነጥፎ በእግር ሲረገጥ ማየት ለህዝበ ክርስትያን በተለይም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መእምናን ትልቅ ውርደት ነው።

ስለሆነም ይህንን ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል የያዘ የወለል ምንጣፍ ባስቸኳይ ከምኒስትሩ ቢሮ እንዲነሳ እና ይህንንም አስነዋሪ ድርጊት ያከናወኑ ግለሰቦች ህዝበ ክርስትያኑን ይቅርታ እንዲጠይቁ እናሳስባለን።

ከዚህ በታች ያለው ፎቶ የአልጀዚራ ጋዜጠኛ የኢትዮጵያ የህዝብ ግንኙነት

ሚንስተር የሆኑትን አቶ ጌታቸው ረዳን በቢሯቸው ተገኝቶ በኦሮምያ የተከሰተውን ግጭት አስመልክቶ ቃለመጠየቅ ሲቀርብ ያሳያል!

"መስቀል ሀይላችን ነው"

ይህንን ፎቶ የያዘውን ቪዲዮ ለመመልከት ያህንን ሊንክ ይጫኑ

http://youtu.be/7jN0PawlakM

ምንጭ: በትረ ሙሴ